## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የትምህርት ሚኒስቴር

# የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012 ዓ.ም)

ግንቦት 2007 ዓ.ም

1. መግቢያ ........ 4
2. የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ከከፍተኛ ትምህርት አንፃር ሲታይ ........ 6
2.1. የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋፋት ........ 6
2.2. ሀብትን የሚንከባከቡና በተገቢው መንገድ የሚጠቀሙ በልዩ ልዩ ተክህኖ የሠለጠኑ ዜጎችን ማፍራት ........ 8
2.3. ዲሞክራሲያዊና የተሟላ ስብዕና ያለቸውን ዜጎች ማፍራት ........ 10
2.4. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያላቸውን ዜጎች ማፍራት ........ 11
2.5. አካባቢያቸውን ለማወቅና ለመለወጥ ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት ........ 12
3. የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሁኔታ ግምገማ 13
3.1. ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ........ 14
3.1.1. የትምህርት ተደራሽነት ........ 14
3.1.2 ፍትሃዊነት ........ 18
3.1.2.1. ሥርዓተ-ፆታ ........ 19
3.1.2.2 ክልላዊ ሁኔታ ........ 21
3.1.2.3. የማህበረ-ኢኮኖሚ ደረጃ ሁኔታ ........ 22
3.1.2.4. የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ሁኔታ ........ 23
3.1.3. አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት ትንበያ ........ 25
3.2. የትምህርት አግባብነትና ጥራት ........ 32
3.2.1. የትምህርት ግብዓትና ሂደት ........ 33
3.2.2. የትምህርት አግባብነት ........ 35
3.2.3. የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማረጋገጫ ስርዓት ........ 37
3.3. የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ........ 39
3.3.1. የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ምንነት ........ 39
3.3.3. የዓለም አቀፋዊነት ጥቅሞችና ስትራቴጂዎች ........ 40
3.3.3. የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ያለበት ደረጃ ........ 42
3.4. የመምህራን ልማት ........ 48
3.4.1. የመምህራን አቅርቦት ........ 49
3.4.2. የመምህራን ጥራት ........ 54
3.4. የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ........ 59
3.4.1. የምርምር አቅም ........ 61
3.4.1.1. የሰው ሀይል አቅም ........ 61

3.4.1.2 የምርምር በጀት ....... 63
3.4.1.3. የምርምር መሰረተ ልማት ....... 64
3.4.2. የምርምር ጥራትና አግባብነት ....... 64
3.4.3 የምርምር ውጤቶች ተደራሽነትና ስርፀት ....... 67
3.5. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር፣ አደረጃጀትና አሰራር ....... 70
3.5.1. የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስ ሥርዓት ....... 75
3.5.2. የበጀት ውጤታማነት ....... 78
3.5.3. የበጀት ምንጮች ....... 79
4. የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዕቅድ፣ ....... 82
4.1. የዩኒቨርሲቲዎች ማስፋፋት እና ማጠናከር ....... 82
4.1.1. የፕሮግራሙ ግቦችና ዓላማዎች ....... 82
4.1.2. የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች ፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ፈጻሚ አካላት ....... 84
4.2. የከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊነትን ማሳደግ ....... 87
4.2.1. ግቦችና ዓላማዎች ....... 87
4.2.2. የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ፈጻሚ አካላት ....... 89
4.3. የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ማሳደግ ....... 91
4.3.1. ግቦችና ዓላማዎች ....... 91
4.3.2. ማስፈጸሚያ አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ፈጻሚዎች ....... 93
4.4. ምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ....... 97
4.4.1. ግቦችና ዓላማዎች ....... 97
4.4.2. የፕሮግራሙ የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ፈጻሚ አካላት ....... 99
4. 5 ተቋማዊ ትብብር፣ አመራርና አስተዳደር ....... 102
4.5.1. ግቦችና ዓላማዎች ....... 102
4.5.2. የማስፈጸሚያ አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ተግባራትና ፈጻሚ አካላት ....... 104
5. ማጠቃለያ ....... 107
5. ዋቢ ማጣቀሻዎች ....... 110
6. አባሪዎች ....... 115

## 1. መግቢያ

አገራችን በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ ያስቀመጠችውን ራእይ  እውን ለማድረግ እና በረዥም ጊዜ የተሃድሶ ጉዞ ግብ የሆነውን የከፍተኛ መካከለኛና የብልፅግና ደረጃ ለመድረስ የሚያስችላትን ጎዳና  እየተራመደች ትገኛለች፡፡ ሃገራዊ ራዕዩን ለማሳካት በዲሞክራሲያዊና ልማታዊ አቅጣጫ መመራት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በኢኮኖሚና ማሕበራዊ ልማት መስክ ግልፅና ታላላቅ ዓላማዎችና አቅጣጫዎች በማስቀመጥና በመተግበር እስካሁን ድረስ በርካታ ስኬቶች ተመዝግበዋል፡፡ ከአንድ የልማት ምዕራፍ ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ ስንሸጋገር ያለፈውን ገምግመን የወደፊቱንም አልመን እሴቶችን በመጨመር ስኬቶቻችንን በጥራትና በአስተማማኝነት ማስቀጠል ይኖርብናል፡፡

በአሁኑ ወቅት የአንደኛውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ዕ.ት.ዕ) አጠናቅቀን ወደ ሚቀጥለው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በመሸጋገር ላይ ነን፡፡ የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማዘጋጀት የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን በመዳሰስ፣ የመጀመሪያውን ግቦች አፈፃፀም ስኬቶችና መልካም ተሞክሮዎችና ተግዳሮቶች ከሃገራዊ ራዕይ ጋር በማስተሳሰር ማየት ይጠበቅብናል፡፡ በሚቀጥሉት ሁለት የእድገትና ትራንስፎርማሽን ዕቅድ ዘመናት የምናስቀምጣቸው ግቦችና አቅጣጫዎች የፖሊሲውን አፈፃፀም  እንዲሁም ያለፉትን አምስት አመታት ስኬቶችና ተግዳሮቶች ታሳቢ ማድረግ እንዳለባቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ቀጣዩ መዳረሻ በ2017 ዓ.ም በዓለም አቀፍ መለኪያ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ የመካከለኛ ገቢ ያላት አገር መገንባት ነው፡፡ አገራችን ወደ መካከለኛ ገቢ ምድብ የምታደርገው ሽግግር ከከፍተኛ ቴክኖሎጂ አቅም የሚመነጭ የግብርና ምርታማነት እድገትና በማኑፋክቸሪንግ  የሚመራ ኢኮኖሚ የመገንባት አቅጣጫ መከተል እንደሚያስፈልጋት የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መስመራችንና በሂደቱ ያለፉ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮዎች ያሳያሉ፡፡

የዚህ አቅጣጫ ስኬት መመዘኛ እና መገለጫ በመጀመሪያ ደረጃ የመካከለኛ ገቢ ምድብ የደረሰ የነፈሰ ወከፍ ገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተጠቀሰው የልማት አቅጣጫ ስኬት የሚወስነው ቁልፍ ግብአትና መመዘኛ የሰው ሃይል ልማት ነው፡፡ የሃገራችን የሰው ሀይል ልማት አሁን ያለበት ደረጃ ዝቅተኛ እንደሆነ መስኩን የሚተነትኑ የዓለም አቀፍ ተቋማት ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ባልተሻሻለበት ሁኔታ የኢኮኖሚ ምርታማነትና መዋቅራዊ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫችን ስኬት እንደሚገደብ ግልፅ ነው፡፡ ትምህርትና ስልጠና የሰው ሃይል ደረጃችን ለማሳደግ የሚያስችለን ቁልፍ መሳርያ ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ሀይል ልማት ከሚወስኑ አማላካቾች ውስጥ የሁለተኛ

ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ውስንነት የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ እድገትን ይገድባል፡፡ የሰው ሃይል ልማት ከአጭር ጊዜ አኳያ የመጀመሪያ ደረጃ  መካከለኛ ገቢ ያላት አገር ለመገንባት የሚያስችሉ የልማት ግቦች ለማሳካት እንደ መሣሪያ ከሚጫወተው ሚና ባሻገር በሂደት የበለፀገች አገር ግንባታ ራዕይ እውንነት የምናረጋግጥበት ቁልፍና የማይተካ አስቻይ ሁኔታ ነው፡፡ ይህም በላቀ ምርታማነት ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ እድገት የእውቀት ማህበረሰብና የቴክሎኖጂ አቅም ግንባታን ይጠይቃል፡፡

በጥቅሉ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው  ከከፍተኛ ትምህርት አንፃር ሲታይ ሁሉ አቀፍ፣ ግልፅና የሚያሰራ ሲሆን አፈፃፀሙ ግን ሲታይ ብዙ ክፍተት ተስተውሎበታል፡፡ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ሲቀረፅ ዋና ግብ የነበረውን የሀገርና የሕዝብ ችግሮችን ለመፍታት የተዘጋጀ፣ ሰብአዊና አገራዊ ኃላፊነት የሚሰማው፣ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ አመለካከቱ የተስተካከለ፣ ከተፈጥሮ ተጽዕኖ በተግባር ለመላቀቅ የተዘጋጀ የማምረትና የመመራመር አቅሙ የዳበረ ዜጋ ማፍራት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አሁንም ብዙ ክፍተት አለበት፡፡

በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የተገነቡ ለሁለንተናዊ ፈጣን ልማት መረጋገጥ ድርሻቸውን የሚወጡ ብቁ ዜጎችን ለማፍራት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በከፍተኛ ትምህርት  ዘርፍ የትምህርት ተሳትፎን፣ ፍትሀዊነትን፣ ጥራትና አግባብነትን የሚያሳድጉ ግቦችና አቅጣጫዎች በማስቀመጥና በመተግበር ከፍተኛ ውጤቶች የተገኙ ሲሆን በቀጣይ ልንፈታቸው የሚገባን ተግዳሮቶች ተለይተዋል፡፡ ከአፈፃፀም አኳያ የከፍተኛ ትምህርት በተሳትፎ፣ ጥራትና አግባብነት ከማሳደግ አንፃር የሄድንበት እርምጃ ጥሩ ሲሆን በፍትሃዊነት በተለይም በሴቶች ተሳትፎ ማረጋገጥ ላይ ግን ከፍተኛ ክፍተት አለብን፡፡ ከዚህም ባሻገር ሃገራዊ ራዕያችንን ለማሳካት የሚጠይቀውን ሰፊ በእውቀት የዳበረና ተወዳዳሪ የሰው ሀይል ከመገንባት አንፃር ገና ብዙ ርቀት መሄድ ይኖርብናል፡፡ በሚቀጥለው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የእቅድ ዘመን ተደራሽነትንና ፍትሃዊነትን የማሳደግ አቅጣጫችን  ተጠናክሮ የሚቀጥል ሆኖ የትምህርት ጥራትና አግባብነት በቀጣይነት የማጎልበት ጉዳይ ግን ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ፣ ፍትሃዊነት፣ አግባብነትና ጥራትን ለማረጋገጥ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የምናስቀምጣቸው ግቦችና አቅጣጫዎች ለማሳካት በአንድ በኩል ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ መመደብ እንደሚያስፈልግ የሚታወቅ ሲሆን ከሁሉም በላይ ግን ከፍተኛ ቁርጠኝነትና ብቃት ያለው አመራር መገንባት ላይ ቀዳሚ ትኩረት በመስጠት ብርቱ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የትምህርትና ቴክኖሎጂ ልማት ሰራዊት በመገንባት በቀረቡት

ግቦችና አቅጣጫዎች ግልፅነት በመፍጠር የአሰራር፣ የአደረጃጀት፣ የግብዓት አቅርቦት፣ የክህሎትና በተለይም የአመለካከት ማነቆዎች በመፍታት ስኬታማ ንቅናቄ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

የሁለተኛው የእድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን በመዳሰስ ከከፍተኛ ትምህርት ጋር አስተሳስሮ በማየት፣ ባለፉት አምስት አመታት ያስቀመጥናቸው ግቦችና አቅጣጫዎች የአፈፃፀም መልካም ተሞክሮዎችና ፈተናዎች በመገምገም እንዲሁም ሀገራዊ ራዕያችንን መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን ይህንንም መነሻ በማድረግም የዘርፉን ቀጣይ ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ አቅጣጫዎችና ፈጻሚ አካላት ቀርበዋል፡፡

## 2. የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ከከፍተኛ ትምህርት አንፃር ሲታይ

የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲያችን በ1986 ዓ.ም ፀድቆ ስራ ላይ መዋል ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ዘርፉ ያለበትን የአግባብነት፣ ጥራት፣ ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ችግሮች በመፍታት በየደረጃው በቂ፣ ብቁና ተፈላጊ የሰው ሀይል ለማፍራት እንዲቻል አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን በማስቀመጥ እንደዚሁም እነዚህን ዓላማዎች ማሳካት የሚያስችሉ የተለያዩ አበይት ስትራቴጂዎች በግልፅ ተቀይሰዋል፡፡ ባለፉት ሃያ ዓመታት ሲተገበሩ የነበሩት የትምህርት ልማት ፕሮግራሞቻችን (ESDP I- IV) በየአምስት ዓመቱ ግቦችንና የማስፈፀሚያ ስልቶችን በመቅረፅና በመተግበር የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን ዓላማዎችና ስትራቴጂዎች ለማሳካት ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል፡፡ የዘርፉ የአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀምም የፖሊሲው ትግበራ አንዱ አካል ነው፡፡ የሚቀጥለው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማዘጋጀት ሲታሰብም ረዘም ላለ ጊዜ ያገለገለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ያለበትን ሁኔታና የመጀመሪያውን ዕ.ት.ዕ አፈፃፀም ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው እና የአንደኛው ዕ.ት.ዕ አፈፃፀም ከከፍተኛ ትምህርት ጋር በማስተሳሳር ተገምግሟል፡፡ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ሲቀረፅ ዋናው ግብ የነበረው የሀገርና የሕዝብ ችግሮችን ለመፍታት የተዘጋጀ፣ ሰብአዊና አገራዊ ኃላፊነት የሚሰማው፣ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ አመለካከቱ የተስተካከለ፣ ከተፈጥሮ ተጽዕኖ በተግባር ለመላቀቅ የተዘጋጀ የማምረትና የመመራመር አቅሙ የዳበረ ዜጋ ማፍራት ነው፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት ፖሊሲው ያስቀመጣቸውን ዓላማዎችና ስትራቴጂዎች ያሉበት ሁኔታ እንደሚከተለው በጥቅሉ ተዳሷል፡፡

### 2.1. የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋፋት

ይህን ዓላማ በማሳካት የሚጠበቀው ወጤት ትምህርትን በየደረጃው በማስፋፋትና ለሁሉም በማዳረስ የግለሰብን የአካልና የአዕምሮ ተሰጥኦ በማጎልበት የሚያጋጥሙ ችግሮችን የማወቅና

የመፍታት ዝንባሌና ችሎታ ያዳበሩ ዜጎች ማፍራት እንደሆነ ፖሊሲው ያስቀምጣል፡፡ ይህም መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ መርሐ ግብሮች በመክፈት ተገቢና ተስማሚ የትምህርትና የሥልጠና ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ፣ ለአካል ጉዳተኞችና ልዩ የትምህርት ድጋፍና አቀራረብ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች እንደየችሎታቸውና ፍላጎታቸው እንዲማሩ ዕድል መፍጠርን እንደሚያካትት ዓላማው አስቀምጧል፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ይህን ዓላማ ለማሳካት ከሃያ ዓመት በፊት ዝቅተኛ የነበረውን የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን በማሳደግ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች አቅርቦትን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ከአጠቃላይ ትምህርት ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚደረገውን ሽግግር ቀልጣፋ ለማድረግና በዚህ ደረጃ የሚኖረውን ተሳትፎ ለማሳደግ በሁለተኛው ደረጃ የሁለተኛ ሳይክል (11ኛ እና 12ኛ) የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎች በዩኒቨርሰቲዎች በብቃት የተዘጋጁ እንዲሆኑ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት መንግስት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በማድረግ ርብርብ አድርጓል፡፡ በሌሎች አገራት ባልተለመደ መልኩ መንግስት በወሰደው ከፍተኛና ቁርጠኛ ውሳኔ መሰረት በተደረገው ኢንቨሰትመንትና ርብርብ ዩኒቨርሲቲዎቻችን በመስፋፋታቸው ምክንያት የቅበላ (Intake)ና የተሳትፎ (Enrolement) አቅማቸው በእጅጉ ጨምሯል፡፡ የዩኒቨርሰቲዎቹ አመሰራረትም ለሁሉም የአገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማስቻል ፍትሃዊ ስርጭት እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ ፖሊሲው ባስቀመጠው መሰረት ዩኒቨርሰቲዎቻችን መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የቅድመና ድህረ ምረቃ መርሃ ግብሮች በመክፈታቸው አጠቃላይ ተሳትፎው ሃያ ዓመት በፊት ከነበረው በጣም ዝቅተኛ (ከበሺዎች የሚቆጠርየተሳትፎ አቅም) ጥቅል ተሳትፎን ወደ ግማሽ ሚሊዮን ማሳደግ ተችሏል፡፡ መንግስት በፈጠረው ምቹ ሁኔታ መቶ ገደማ የሚሆኑ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከፍተው ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ ፖሊሲው እንደሚያስቀምጠው አካል ጉዳተኞችንና ሴቶችን ጨምሮ ሌሎች ልዩ ድጋፍ የሚሹትን ዜጎች የትምህርት እድል ለማስፋት በአገር ደረጃ ልዩ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ስርዓትና የትምህርት መርሃ ግብር አመዳደብ አሰራር ተዘርግቷል፡፡ በዚሁ ምክንያትም የነዚህ ዜጎች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ በተነፃፃር አድጓል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሰሃራ በታች ያሉት የአፍሪካ አገራትን ጥቅል ተሳትፎ ያህል ያሳካን ቢሆንም አሁንም ከህዝብ ቁጥራችንና ከራዕያችን አንፃር የደረስንበት የተሳትፎ መጠን አነስተኛ ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚፈለገው ደረጃ በትምህርት መሰረተ ልማትና ብቃት ባለው የሰው ሃይል (መምህራንና አመራር) ስላልተደራጁ ተማሪዎቹ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚያደርጉት ሽግግር ቀልጣፋ አይደለም ብቻ ሳይሆን ዩኒቨርሰቲ የመግባት እድል ያገኙትም

ቢሆን የመዝለቅ አቅማቸው አነስተኛ ስለሆነ አጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ በፍጥነት ማሳደግ ላይ ያልተሻገርነው ተግዳሮት ሆኗል፡፡ በተለይም የሴቶችና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎን ለማሳደግ ያደረግነው ጥረት አበረታች ቢሆንም ያስቀመጥነውን ግብ ከማሳካት አኳያ አሁንም ቀጣይ ትኩረት የሚሻ ፈታኝ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ በማደጉ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥሩ ቢጨምርም ከፍተኛ ትምህርት ገብተው በብቃት የሚዘልቁ ተማሪዎችን እንዲሆኑ ከማዘጋጀት አንጻር ግን ክፍተት ይታይበታል፡፡

በሌላም በኩል የከፍተኛ ትምህርት የማስፋፋት ግቦቻችንን ለማሳካት በመንግስት የተደረገው ኢንቨስትመንትና ርብርብ የላቀ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲዎች አመሰራረትና እድገት በሚጠበቀው ደረጃ ፈጣን ባለመሆኑ የተማሪዎችን ቅበላ እየገደበ ያለ ሁኔታ እንደሆነ ታይቷል፡፡ በብዙዎቹ ተቋማት የሚታየው የግንባታ መጓተትና የትምህርት ግብዓቶች፣ የመምህራን አቅርቦት በፍጥነት ያለማሟላት ችግር፣ በየደረጃው የተደራጀና የተቀናጀ አመራር የመፍጠር ችግር ዋነኛውን ድርሻ እንደሚወስድ አድርጎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን በየተቋሙ በተለይ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት መስኮች ዙርያ ለነበረው የቅበላ እድገት ውስንነት ዋናው ምክንያት የመምህራን አቅርቦት እጥረት ነበር፡፡ ለዚሁም ያልተመጣጠነ የቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ተሳትፎ እድገት እንደ ምክንያት መግለፅ ይቻላል፡፡ የድህረ ምረቃ ትምህርት ለቅድመ ምረቃ ትምህርት የመምህራን አቅርቦት ማሳደጊያ መንገድ እንደመሆኑ መጠን በሁለቱም እርከኖች ስናስፋፋ ምጣኔዎችውን በጥንቃቄ ማቀድ እንዳለብን ትምህርት ይሠጠናል፡፡ በአጠቃላይ ፖሊሲው ያስቀመጠው የማስፋፋት ዓላማ ትክክለኛና መቀጠል ያለበት ሆኖ በቂና ችግር ፈቺ የሆኑ የሰለጠኑ ዜጎችን ለማፍራት የምንጠቀምባቸው ስትራቴጂዎችና ስልቶች አፈፃፀም ግን ክፍተት ያሉባቸው ስለሆኑ በቀጣይ መሻሻል ይገባቸዋል፡፡

## 2.2. ሀብትን የሚንከባከቡና በተገቢው መንገድ የሚጠቀሙ በልዩ ልዩ ተክህኖ የሠለጠኑ ዜጎችን ማፍራት

ፖሊሲው የትምህርት ውጤቶች እንዲሁም የትምህርት መሳሪያዎች የትምህርት ግብዓት እንዲሆኑ ይህንን የሚንከባከቡና በተገቢው መንገድ የሚጠቀሙ የተለያዩ ክህሎቶች በስልጠና የጨበጡና የተካኑ ዜጎችን ማፍራት እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ አኳያ ፖሊሲው የግለሰብንም ሆነ የኅብረተሰብን ንብረት በተገቢው መንገድ የመጠበቅና የመጠቀም አመለካከትና ችሎታን ያዳበሩ ብሎም ልዩ ልዩ ክህሎተ ያላቸው ዜጎችን በማፍራት የአገሪቱን የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ማርካት የሚያስችል ትምህርት መስጠት እንደሆነ ይተነትናል፡፡ የመንግስትና የግል ሃብትን

በተገቢው የሚንከባከቡና የሚጠቀሙ የሰለጡኑ ዜጎችን ከማፍራት አኳያ የከፍተኛ ትምህርት አመራርና መምህራን ተምሳሌታዊ ሚና ስለሚጫወቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ መሆኑን በመገንዘብ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባራትን ለመቀነስና ለመከላከል ከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የትምህርትና ቴክኖሎጂ ልማት ሰራዊት በመገንባት የአደረጃጀት፣ አሰራር፣ ክህሎት፣ አስተሳሰብና ግብዓት ማነቆዎች በመለየትና በመፍታት የሃብት እንክብካቤና ውጤታማነት ለማሳደግ ብዙ ስራ ተሰርተዋል፡፡ ከመስፋፋት ጋር ተያይዞ ዩኒቨርሲቲዎች ከከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ከማስተዳደር  ከፍተኛ ሃብት ወደ ማስተዳደር የተቀየሩበት ሁኔታ ስለነበር ለኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባራት የተጋለጡበት ሁኔታ እንደነበር በግልፅ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከሃብት ብክነት ባሻገር በዚህ ሂደት ለምናፈራቸው ዜጎች የሚሰጠው ተሞክሮው አደገኛ  እንደሆነ አያከራክርም፡፡

እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት በየተቋሙ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ክፍሎች በማቋቋምና ከአገራዊው ኮሚሽን ጋር በማስተሳሰር የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባር ለመከታተልና ለመታገል ያለመ አደረጃጀት ተፈጥሯል፡፡ መላው የዩኒቨርሰቲ ባለድርሻ አካላት ማለትም ተማሪዎች፣ መምህራንና አመራር እንዲሁም ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማቀናጀት ከነክፍተቱም ቢሆን የተፈጠረው የትምህርትና ቴክኖሎጂ ሰራዊት ኪራይ ሰብሳቢነትን ሙሉ በሙሉ ባያጠፋም ተግባሩን ለመፈጸም ህገ ወጥና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በየጊዜው በአገር ደረጃ የወጡት የፋይናንስና ግዥ መመርያዎችና ደንቦች  ተጠያቂነትና ግልፅነትን በመፍጠር በከፍተኛ ትምህርት ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመታገል ምቹ ሁኔታን  ፈጥሯል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ የማዕቀፍ ግዥና የተቋማቱ የውስጥ ገቢ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱ ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመታገል ከተወሰዱት እርምጃዎች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በየሙያ መስካቸው ተማሪዎች የሚከታተሉት ትምህርት እንደተጠበቀ ሆኖ የስነ ምግባር ትምህርት ለሁሉም እንዲሰጥ ለማድረግ በዚህም ውስጥ መልካም ስነ ምግባር ለመገንባት ጥረት ተደርጓል፡፡ የግልና የአገርን ሃብት በአግባቡ ለመንከባከብና ለመጠቀም ፖሊሲው ባስቀመጠው መሰረት በተለያዩ መስኮች በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የተገነቡ ዜጎችን የማፍራት ሂደት ጀምረናል፡፡

ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመቀነስና ለማጥፋት በየደረጃው የተወሰዱ እርምጃዎችና የተገኙ ውጤቶች የማይናቁ  ቢሆኑም አሁንም በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አመለካከቱና ተግባሩ ሙሉ ለሙሉ አልተቀረፈም፡፡ ከዚህ አኳያ ኪራይ ሰብሳቢነትን በሂደት ከምንጩ  ለማድረቅ በሰራዊት አግባብና መልካም አስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ የተዘረጉ የአሰራርና አደረጃጃት እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው በመላው የተቋማቱ ማህበረሰብ ይህንን አስተሳሳብና ተግባር የማይሸከም

ማህበራዊና ነባራዊ ሁኔታ በመፍጠር ሃብትን በአግባቡ የሚንከባከቡና የሚጠቀሙ ዜጎችን ለማፍራት የሚያስችል ተቋማት መገንባት አለብን፡፡

ተማሪዎች በየትምህርት መስካቸው ዙርያ ከሚጨብጡት የሙያ ክህሎት ባሻገር የግልንና የመንግስትን ሃብት በተገቢው መልኩ መጠቀም እንዲችሉና መልካም ስብዕናን ለመገንባት ከምንሰጠው የስነዜጋና ስነ ምግባር ትምህርት በተጨማሪ የሚከታተሉት ትምህርት ስብጥርም ለሥራ ፈጠራ ብቃትን የጨበጠ ዜጋ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ እንዲቀረፁ ለማድረግ በትምህርት ሰርዓት ማሻሻያነ ቀረፃ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 2.3. ዲሞክራሲያዊና የተሟላ ስብዕና ያለቸውን ዜጎች ማፍራት

ይህ የሚያመለክተው የማህበራዊ ኑሮና ግንኙነት ባህልን በማበልፀግ ለሰው ልጅ ደህንነትና እኩልነት፣ ለፍትሕና ለሠላም የቆሙ በሥነ-ምግባርና በዲሞክራሲ ባህል የታነጹ ለሕዝብና ለሀገር ፍቅር ያላቸውና ሁለንተናዊ ሰብዕናቸው የተሟላ ዜጎችን ማፍራት ነው፡፡ ለዚህም ትምህርት ሴኩላር ሆኖ እንዲካሄድ በማድረግ፣ የዲሞክራሲ ባህል የሚያሰፍን የመቻቻል፣ ቅራኔን በሠላምና በውይይት የማርገብና የመፍታት እንዲሁም ማህበራዊ ኃላፊነትን የመወጣት ግንዛቤን ከፍ የሚያደርግ፣ ለእኩልነት ለነፃነት ለፍትሕና ለዲሞክራሲያዊ አንድነት የቆሙ በሥነ-ምግባር የታነጹ ዜጎችን ማፍራት የሚያስችል እንዲሁም ትምህርት በሁሉም መልኩ ስለሴቶች ሚናና አስተዋጽኦ ያለውን ማህበራዊ አመለካከት የሚለውጥና ትክክለኛውን ግንዛቤ የሚያንፀባርቅ አድርጎ መቅረፅና መተግበርን ተገቢነት ያስቀምጣል፡፡

ሴኩላር ትምህርት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመስጠት ከሃይማኖት፣ ባህልና ፖለቲካ ተፅዕኖ የፀዳ ሥርዓት ትምህርት በመቅረፅና በመተግበር ከተሰራው ስራ በተጨማሪ ብዝሃነትን ለማስተናገድ የሚያስችል ምቹ ተቋማዊ ሁኔታ በመፍጠርም ብዙ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ዩኒቨርሲቲዎች ከተለያዩ ሃይማኖትና ባህል የተሰባሰቡ መምህራን፣ ሰራተኞችና ተማሪዎች በአንድነትና በመከባበር የሚኖሩባቸው ተቋማት በማድረግ ላይ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ አልፎ አልፎ ሲያጋጥሙ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት በከፍተኛ ትምህርት ማህበረሰብ በግቢ ውስጥ የሚተገበር ሴኩላር የሆነ የአለባበስ፣ አመጋገብና አምልኮ ፕሮቶኮል ወጥቶ ተግባራዊ መደረጉን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዩኒቨርሰቲ ግቢዎች ውስጥ የሰላም መደፍረስ ምንጮችን በመለየት ከአሰራርና አደረጃጀት ጋር የተያያዙ መፍትሄዎችን በማስቀመጥና በመተግበር ዙርያ መልካም ተሞክሮዎችን ቀስመናል፡፡ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎና ውጤታማነት ለማጎልበት ልዩ

የዩኒቨርሰቲ መግቢያ ሥርዓት በማበጀት፣ አካዳሚያዊ፣ ስነ ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ በማድረግ ረገድ ወጣ ገባነት ቢኖረውም ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል፡፡

ሆኖም ግን ሃይማኖትን ተገን በማድረግ የሚታዩ ችግሮች አሁንም በስፋት በተቋማቱ ስለሚታዩ የዩኒቨርሲቲ ግቢዎችን የሴኩላር አመለካካት ተግባር የበላይነት የሚረጋገጥበት ደረጃ እስኪደርስ በብዝሃነት ላይ የተመሰረተ አንድነት የመፍጠር መርህ በተሟላ መልኩ የሚፈጥሩ እርምጃዎች መውሰድ አለብን፡፡ በሴቶች ላይ ሊኖር የሚገባው መልካም አመለካከት በተሟላና አስተማማኝ ሁኔታ ለመፍጠር ከስካሁኑ የወሰድናቸው እርምጃዎች ተቋማዊ ሰርዓት ሆነው እንዲቀጥሉ በማድረግ የሴት አመራር፣ መምህራንና ተማሪዎች ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን ስኬታማነትንም በማጎልበት ለሴቶች መልካም አመለካከት ያለው ዜጋ ማፍራት ይጠበቅብናል፡፡

## 2.4. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያላቸውን ዜጎች ማፍራት

የዚህ ዓላማ ዋናው ይዘት የማመዛዘን፣ የመፍጠርና የመመራመር ችሎታን በማዳበር ጎጂ ባህሎችን ከጠቃሚዎቹ የሚለዩ እውነትን የሚሹ ለእውነት የሚቆሙ ውበትን የሚያደንቁ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት መስረጽና ማደግ አዎንታዊ አመለካከት የሚያሳዩና አስተዋጽኦ ያላቸው ዜጎች ማፍራትን ያመለክታል፡፡ ትምህርት ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚረዳ መሣሪያ እንዲሆን ማድረግ ለጥናትና ምርምር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ከልማት ጋር ተገቢው ተስተጋብር እንዲኖራቸው በቅንጅት ማካሄድ እንደዚሁም ትምህርት ባህላዊ ቴክኖሎጂን ለማሳደግና ተስማሚ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚረዳ መሣሪያ እንዲሆን ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ዓላማዎች ነበሩ፡፡

የምናፈራቸው ባለሙያዎች ስብጥር ከሃገሪቱ የልማት እንቅስቃሴና ራዕይ ጋር ለማጣጣም ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያተኮረ የከፍተኛ ትምህርት እድገት አቅጣጫ በመቅረጽ በ70፡30 የመስኮች ምጣኔን በመቀመርና በመተግበር በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎታችን ለማርካት ጥረት አድርገናል፡፡ ምርምርንና ማህበረሰብ አገልግሎትን ችግር ፈቺ ለማድረግ የተቀመጠውን ኣላማ ለማሳከት የምርምር አጀንዳዎች በመቅረፅ፣ የምርምር አቅምን ለማጎልበት ጥረት ተደርጓል፡፡ ተቋማት የአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የምርምር የትኩረት መስኮች በመለየት በተለያየ ደረጃ ቢሆንም የምርምር እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል፡፡ ተቋማት የሚያከናውናቸው ምርምርና ትምህርት ስራዎች ከአከባቢያቸው ኢንዱስትሪ ጋር ለማስተሳሰር በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፤፤ በተቋማት የምርምር አቅምን ለማጎልበት የሶስተኛ ድግሪ ያላቸውን ምሁራን ቁጥር ከፍ

ለማድረግ ግብ በማስቀመጥ የተሰራ ሲሆን፣ አቅም በፈቀደ መልኩ የቤተ ሙከራ፣ ዎርክሾፕ እና ሌሎች የምርምር መሰረተ ልማቶችን የማደራጀት ጥረት አለ፡፡

ጅምሮቹ እንደተጠበቁ ሆነው የከፍተኛ ትምህርት የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች በአግባብነት፣ በጥራትና በመጠን እጥረት ይታይባቸዋል፡፡ አገራዊ የምርምር ማዕቀፍ አልተዘጋጀም፤ ለምርምር የሚመደበው በጀት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በምርምር ላይ የሚሳተፈው የተመራማሪዎች አቅምና ቁጥርም ውሱን ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን የችግር ፈቺነት ዓላማ ማሳካት ላይ ክፍተት ይታይበታል፡፡ በአጠቃላይ በተቋማት የሚደረጉ ምርምሮች በብዛት፣ በጥራት፣ እንደዚሁም በችግር ፈቺነትም ውስንነቶች ይስተዋልባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የአገርቱን የልማት እንቅስቃሴና ራዕይ ለመደገፍ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያተኮሩ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲያከናውኑ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ዩኒቨርሰቲዎች የምርምር አጀንዳዎች ቀደም ተከተል በማስቀመጥ፣ የተመራማሪዎችን አቅምና ተነሳሽነት በመገንባትና አስፈላጊውን በጀት በመመደብ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ማድረግ ይገባል፡፡

በማህበረሰብ አገልግሎት ዙርያ በተለያዩ ተቋማት የሚከናወኑ የተለያየ ደረጃ ያላቸው ስራዎች ቢኖሩም በጥቅሉ ሲታይ ግን ይህ ተልዕኮ በአመራርም ይሁን በመምህራን ትኩረትና ኢንቨስትመንት የሚደረግበት እና በቂ ጊዜ የሚሰጥበት ነው ተብሎ ሊወሰድ አይቻልም፡፡ ተልዕኮው ባአብዛኞቹ መምህራን አካዳሚያዊ (scholar activity) ተደርጎ የማይታይበት ሁኔታ እንደሚንፀባርቅ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የማህበረሰብ አገልግሎት ከመማርና ማስተማር እንደዚሁም ከምርምር ጋር በማቀናጀት የመምህራንን አቅምና ተነሳሽነት በማሳደግ በተሻለ ደረጃ የሚፈፀምበት መንገድ መቀየስ አለበት፡፡

## 2.5. አካባቢያቸውን ለማወቅና ለመለወጥ ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት

ከላይ የተዘረዘሩ ዓላማዎች እንዳሉ ሆነው የምናፈራቸው ዜጎች በድምር ትምህርትን ለአካባቢው ተስማሚና ተገቢ በማድረግ አካባቢያቸውን የማወቅ፣ የማጤን፣ የመገንዘብ፣ የመመዘን፣ የመገምገም፣ የመተንተንና የመለወጥ ችሎታ ያላቸው ዜጎችን መቅረፅ እንደሆነ ፖሊሲው ያስቀምጣል፡፡ የዚሁ ዋናው ትኩረት ከላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች ለማሳካት የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት የማረጋገጥ ስራ በስኬትም ጭምር እንዲታጀብ በጥራትና አግባብነት ላይ በመስራት ብቁ ዜጋ ማፍራት እንዳለብን ያስገነዝባል፡፡

በድምሩ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ በትምህርት ስርዓቱ የሚያልፉት ዜጎች ችግር ፈቺ የሆኑ ለማድረግ ስርዓተ ትምህርቱ የአገራችን ነባራዊ ሁኔታን ማዕከል ያደረገ፣ የትምህርት አሰጣጡ ተግባር ተኮር እንዲሆን ማድረግ፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች አገራዊና አካባቢያዊ ችግሮችን ማዕከል ማድረግና ጠንካራ የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር በመፍጠር ዙርያ ያሉብንን ክፍተቶች ስንገመግም የምናፈራቸው ዜጎች በፖሊሲው መሰረት ወደሚፈለገው ደረጃ ደርሰዋል ብሎ ለመናገር አያስደፈርም፡፡

ከዚህ አኳያ ከስካሁኑ ጥራትና አግባብነትን ለማጎልበት በሰርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣ በመምህራን ልማት፣ በመሰረተ ልማት፣ በሙያ ስብጥር ልየታና ትግበራ፣ በመልካም አስተዳደር እና በመሳሰሉት የተወሰዱ የአሰራር፣ የአደረጃጀት፣ የግብዓት አቅርቦትና የክህሎት ግንባታ እርምጃዎች አጠናክሮ በመቀጠል በሁሉም መስኮች ላይ አገራዊ ፍላጎትንና ዓለምአቀፍ ተሞክሮን መሰረት ያደረጉ ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት አካባቢያቸውን ለመገንዘብና ለመለወጥ ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት የሚችሉ ተቋማት መገንባት አለብን፡፡

በጥቅሉ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ከከፍተኛ ትምህርት አንፃር ሲታይ ሁሉዓቀፍ፣ ግልፅና የሚያሰራ ሲሆን በትግበራ ግን ብዙ ክፍተት ይታይበታል፡፡ ስለዚህ ዋናው ቀጣይ ትኩረታችን መሆን ያለበት ዓላማዎችንና ስትራተጂዎችን በጥልቀት በመገንዘብና በመተንተን ካለፉት ሃያ ዓመታት ጉዞአችን በመማር የሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ግቦችንንና አቅጣጫዎችን በጥንቃቄ መቅረፅና መተግበር ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ማለት ግን በቀጣይ ሊቀያየር የሚችለውን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታችን የሚጠይቀውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው አግባብነትና የትግበራ አመቺነት ሰፊና ሳይንሳዊ ምርምር በማድረግና ዓለምአቀፍ ተሞክሮን በመቀመር እንደአስፈላጊነቱ በሂደት መስተካከል አይችልም ማለት አይደለም፡፡

## 3. የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሁኔታ ግምገማ

ይህ ሰነድ ስድስት የትኩረት መስኮችን ወይም ምሰሶዎችን በመለየትና የክፍተቶች ትንተና (Gap Analysis) በማድረግ ቀጣይ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ የሚረዱ መረጃዎችን አቅርቧል፡፡ እነዚህም የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ አግባብነትና ጥራት፣ የመምህራና ልማት፣ ምርምር፣ ቴክኖሎጂና ማህበረሰብ አገልግሎት፣ አመራር፣ አደረጃጀትና አሠራር ናቸው፡፡

## 3.1. ተደራሽነትና ፍትሐዊነት

በፍጥነትና በተከታታይ እያደገ ያለውን የአገራችን ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለማስቀጠል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቂና ብቁ የሰው ሀይል የማፍራት አቅጣጫ ይዘው ቀጥለዋል፡፡ በመጀመሪያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን  የተቋማት ቁጥርን በመጨመር፣ የቅበላ አቅምን በማሳደግ፣ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማበረታታት እና የተለያዩ የትምህርት መርሀ ግብሮችን በመቅረጽና በመተግበር የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ላለፉት ተከታታይ አምስት ዓመታት በተነፃፃሪ መልኩ ጉልህ በሆነ ሁኔታ ሊጨምር ችሏል፡፡ ለአብነት ያህል በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛው መርሀ ግብር የቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ተማሪዎችን ብቻ ብንወስድ የመጀመሪያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻው ላይ በ2002 ዓ.ም ላይ 185,785 የነበረ ሲሆን ይህ አሃዝ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማገባደጃው ዓመት 2007 ዓ.ም ላይ 387,565 በመድረስ በዕቅድ ዘመኑ መነሻ ካደረገው ዓመት ከ2002 ዓ.ም በ208.61% ያደገ ሲሆን የ41.7% ዓመታዊ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

### 3.1.1. የትምህርት ተደራሽነት

የኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት የሀገራችንን የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ አግባብነትና ጥራትን በማረጋገጥ የሰለጠነ የሰው ሃይል ለማፍራት የዘርፉን ተቋሟት በመገንባት ረገድ የላቀ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ እጅግ ከፍተኛ በሚባል ሁኔታ ዩኒቨርሲቲዎችን በሶስት ምድቦች/ትውልዶች ከፍሎ በማስፋፋት 33 የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም ነባር ዩኒቨርስቲዎችን በማጠናከርና ኮሌጆችን/ተቋማትን በማሳደግ በመጀመሪያው ምድብ ውስጥ የሚካተቱ 9 ዩኒቨርስቲዎች (አዲስ አበባ፣ ሃረማያ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ጅማ፣ ሀዋሳ፣ አዳማ፣ አርባምንጭ እና መቀሌ)፣ በክልሎች ፍትሐዊነትን በጠበቀና ብዝሃነትን ሊያስተናግድ በሚችል መልኩ 22 አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች ተመስርተዋል፡፡ እነዚህም በሁለተኛው ምድብ ውስጥ የሚገኙ ከ10 ዓመት እድሜ ያልበለጣቸው 13 ዩኒቨርስቲዎች (አክሱም፣ ወሎ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደብረ ብርሃን፣ ወለጋ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ሚዛን-ቴፒ፣ ሰመራ፣ ጂግጂጋ፣ ድሬዳዋ፣ መደወላቡ፣ አምቦ እና ዲላ) አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሶስተኛው ምድብ የሚካተቱት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በነበሩት አምስት ዓመታት ውስጥ ተማሪዎች ተቀብለው  አገልግሎት የጀመሩ አዳዲስ 9 ዩኒቨርስቲዎች (አዲግራት፣ ወልድያ፣ ደብረ ታቦር፣ አሶሳ፣ መቱ፣ ቡሌ ሆራ፣  ዋቻሞ፣ ወልቂጤ እና አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ) ተመስርተዋል፡፡

በዚህም መሰረት በመጀመሪያው የዕ.ት.ዕ ወቅት ይገነባሉ ተብሎ የታቀዱ 11 አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች በዕቅዱ መሰረት ተገንብተው ተማሪዎችን በመቀበል በማስተመር ላይ ይገኛሉ፡፡ በሁለተኛ የዕ.ት.ዕ ወቅት ይገነባሉ ተብለው ከታሰቡት መካከል ደግሞ ጋምቤላና አርሲ ዩኒቨርሰቲዎች በ2007 ዓ.ም ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ጀምረዋል፡፡

በተጨማሪም ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፣ ኮተቤ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅና የመከላከያ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ለሰው ሃብት ልማት እድገት እንዲሁም ሳይንስና ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ከፍተኛ አስተጽዖ በማድረግ ላይ የሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ናቸው፡፡ አገራችን ልማትንና ዲሞክራሲን በማሳደግ መካከለኛ ገቢ ያላት አገር ለመሆን እያደረገች ያለውን ጉዞ ለማፋጠን መንግስታዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ የሚወጡት አይሆንም፡፡ በመሆኑም የግል ዘርፉንም ተሳትፎ ማጠናከር አስፈላጊ ከመሆኑ አኳያ መንግስት አቅም በፈቀደው መጠን ድጋፍ እየተደረገላቸው በርካታ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትምህርትና ስልጠና ልማቱ ላይ ተሰማርተዋል፡፡ እነዚህም የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አራት ዩኒቨርስቲዎች (ዩኒቲ፣ ቅድስት ማርያም፣ አድማስ እና ሪፍትቫሊ) እና ከ90 በላይ የሆኑ ዩኒቨርሰቲ ኮሌጆች እና ኮሌጆች በመስፋፋትና በማደግ በሰው ሃብት ልማቱና በአገራዊው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነባሮቹም ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ አቅማቸውን ማሳደግ ከጊዜ ወደ ጊዜ የቅበላ አቅማቸው እንዲያድግ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር በእጅጉ ሊጨምር ችሏል፡፡

በዚህም ረገድ አጠቃላይ የመንግስትና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ የተሳትፎ አቅም በመጀመሪያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ባደረገው /Base year በ2002 ዓ.ም በሁሉም የትምህርት መርሀ ግብሮች (በመደበኛ፣ በማታ፣ በርቀትና በክረምት) የነበረው ተሳትፎ 420,387 ከዚህ ውስጥ በመንግሰት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛ መርሀ ግብር ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ ተማሪዎች ብዛት 185,785 ገደማ የነበረ ሲሆን ይህ አሃዝ በመጀመሪያው ዕ.ት.ዕ. መገባደጃ በ2007 ዓ.ም ላይ 593,571 ደርሷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች በመደበኛው መርሀ ግብር በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር 387,565 ነው፡፡

ከዚህ አጠቃላይ የመጀመሪያ ዲግሪ የተማሪዎች ተሳትፎ የመንግስት ተቋማት ድርሻ 503,566 (84.8%) ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ በእነዚሁ የመንግስት ተቋማትበመደበኛ 335,078 በተከታታይ መርሀ ግብር 80,205፣ በክረምት 102,640፣ በርቀትትምህርት 75,648 ተማሪዎች ትምህርታቸውን መከታተል ችለዋል፡፡ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጅማሬ በቅርብ

ቢሆንም  በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ዕድገት በማሳየት በከፍተኛ ትምህርት ከሚገኙት አጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ 90,005 (15.2%)ቱን ማስተናገድ ችለዋል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የማስፋፋት ስራው በመንግስት ብቻ ሳይሆን የግል ከፍተኛ ተቋማትም በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ቁጥራቸው በመጨመሩ የቅበላ አቅማቸውም በማደጉ ነው፡፡ በዚህም አገሪቱ የምትፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሀይል ፍላጎትን ከማሟላት አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረጉ እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብርም ባለፉት ዓመታት መስፋፋት ታይቷል፡፡ በሃገራችን የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት በ2002 ዓ.ም የነበረው የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ተሳትፎ 12,621 ሲሆን ይህ አሃዝ  በ2006 ዓ.ም ወደ 26,117 ደርሷል፡፡ ቀደም ሲል በድህረ ምረቃ ትምህርት ብዙም ሲንቀሳቀስ ያልነበረው የግል ዘርፉም የሁለተኛ ዲግሪ ተሳትፎውን 3,158 አድርሷል፡፡ በሁለቱም ዘርፎች የሀገራችን የሁለተኛ ዲግሪ ተሳትፎ 29,275 ደርሷል፡፡
በተመሳሳይ ሁኔታ በ2002 ዓ.ም የትምህርት ዘመን 791 የነበረው የሶስተኛ ዲግሪ ተሳትፎ በ2006 ዓ.ም ወደ 3,296 ደርሷል፡፡ ይህ የትምህርት ደረጃ እስከ አሁን ድረስ በግሉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ መሰጠት አልተጀመረም፡፡ የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት ተሳትፎ ከአጠቃላይ የድህረ ምረቃ ተሳትፎ ጋር ሲነፃፀር ያለው ድርሻ 11.3% ገደማ ብቻ ሲሆን የሁለተኛና የሶሰተኛ ዲግሪ ተሳትፎ ከአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ድርሻ 5% ብቻ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ የሚያሳየው የሁለተኛና የሦስተኛ ድግሪ ተሳትፎን ለማሳደግ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች በማበልፀግ ዙሪያ ብዙ ርቀት መጓዝ እንዳለብን ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን የሁለተኛም ሆነ የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት ተሳትፎው በሚፈለገው ደረጃ ደርሷል ባይባልም የእስከ አሁኑ እድገት በተለይ የመጀመሪያ ዲግሪ ተሳትፎ ማስፋፋትን ለማሳካት ለዩኒቨርሲቲዎች የመምህራን ፍላጎት ማሟላት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ከዕቅድ አፈጻጸም አኳያ በዕ.ት.ዕ መነሻ በ2002 ዓ.ም በመደበኛው መርሃ-ግብር የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች የቅድመ ምረቃ ተማሪዎችን ቁጥር ከ185,785 ወደ በ2007 ዓ.ም 467,445 ለማድረስ ግብ የተቀመጠ ሲሆን በእቅድ ዘመኑ መገባደጃ 2007 ዓ.ም ላይ 387,565 ደርሷል፡፡ የዕቀድ አፈጻጸም (82.9%) አበረታች ቢሆንም ከተጣለው ግብ አንጻር ብዙ ይቀራዋል፡፡

የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ ባለፉት ዓመታት በነበረው ማሰፋፋት በከፍተኛ ደረጃ ቢያድግም ከአገራችን ራዕይ አኳያ ከዚህ በላይ ማደግ ይኖርበታል፡፡ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) ስታንዳርድ መሰረት የከፍተኛ ትምህርት የዕድሜ ክልል የሚባለው ሁለተኛ ደረጃ ከተጠናቀቀ በኋላ ያሉት 5 ተከታታይ ዓመታትን

ያካትታል፡፡ በሀገራችን ሁኔታ ይህ የዕድሜ ክልል ከ19 እስከ 23 ያለውን የሚያካትት ነው፡፡ በማዕከላዊ ስታቲስትክስ ባለሥልጣን መረጃ መሰረት በ2006 ዓ.ም ከ19 እስከ 23 ዕድሜ ክልል ውስጥ የነበረው የህዝብ ቁጥር 6,256,672 ነበር፡፡ በ2006 ዓ.ም በቅድመ ምረቃ ደረጃ በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ መርሀ ግብሮች 593,571፣ በድህረ ምረቃ (በ2ኛ ዲግሪ 29,275፣ በ3ኛ ዲግሪ 3,292) ተማሪዎችን በድምሩ 32,567 ነው፡፡ በአጠቃላይ በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ በዚህ የትምህርት ዘመን የነበሩ የተማሪዎች ቁጥር 593,571 ነበር፡፡ ይህ ማለት የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ 9.49% ደርሷል ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ወቅት ከሰሃራ በታች ያሉት የአፍሪካ አገሮች አማካይ የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ 8.2% ሲሆን የሃገራችን ደግሞ ከዚህ በላይ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የተመዘገበው ውጤት በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ይደረስበታል ተብሎ የተቀመጠው የ9.3% የጥቅል ተሳትፎ ግብ ከወዲሁ በማሳካት ከፍተኛ ተሳትፎ ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

ሆኖም ግን እሰከ አሁን የደረስንበት የተሳትፎ ዕድገት ከዓለም አቀፍ እና ከአንዳንድ የአፍሪካ አገራት አኳያ ሲታይ ገና አነስተኛ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና ባህል ድርጅት (UNESCO) በቅርቡ ባወጣው የከፍተኛ ትምህርት ስታቲስትካዊ መረጃ እንደሚያመለክተው እ.ኤ.አ በ2012 በዓለም ደረጃ በተገቢው የዕድሜ ክልል ከሚገኙ 100 ሰዎች ውስጥ 32ቱ ወይም አንድ ሶስተኛው ገደማ በከፍተኛ ትምህርት ተሳትፈዋል፡፡ የደበብ አፍሪካ እና የቻይና የጥቅል ተሳትፎ መጠን በቅደም ተከተል 18% እና 30% ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በተጠቀሰው ዓመት ውስጥ የዚህ አሃዝ የአፍሪካ አማካይ 11.59% ሲሆን በዚህ ወቅት ዝቅተኛ የገቢ መጠን ያላቸው ሀገሮች አማካይ የከፍተኛ ትምህርት ተሳተፎ መጠን 9.49% ነበር፡፡ በተመሳሳይ ወቅት የነበረው የዝቅተኛ የመካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች ግን 22.86% ነበር፡፡

ከዚህ አኳያ ሲታይ የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ የማሳደግ ጥያቄ ከሀገራዊ ራዕይ፣ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄደውን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛትና የትምህርት ጥራትን ታሳቢ በማድረግ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ የተገለፁት በተለይ ባለፉት የተወሰኑ ዓመታት የተመዘገቡ ውጤቶች አበረታች በመሆናቸው ለቀጣይም እንደ ጠንካራ መሰረት እና መደላድል ሆነው ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን የከፍተኛ ትምህርት የስኬት ደረጃ መለካት ያለበት መድረሻችን ከሆነው ሃገራዊ ራእይ ሲሆን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን (ከ2008-2012 ዓ.ም) ማገባደጃ ጀምሮ በሚኖሩት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የመካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር የመገንባት ታላቅ ራዕይን እውን ለማድረግ በቀጣይ

ከሚጠበቅበት የላቀ ሚና አኳያ የሃገራችን ከፍተኛ ትምህርት ብዙ ርቀት መሄድ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የከፍተኛ ትምህርት ልማትን ለማስቀጠል የሚያስችሉ ግቦችን፣ አቅጣጫዎችንና ትኩረት የሚሹ ክፍተቶችን መለየት ያስፈልጋል፡፡

### 3.1.2 ፍትሃዊነት

ከፍተኛ ትምህርትን ለዜጎች ተደራሽ ማድረግ በአንድ አገር ውስጥ ያለውን የትምህርት እኩል ተጠቃሚነት ማረጋገጫ መንገድ ነው፡፡ ይህም በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ቡድኖችን ያካተተው የማህበረሰብ ጥንቅር (በፆታ፣ በማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ በጂኦግራፊያዊ አሰፋፈር፣ ልዩ ፋላጎት ያላቸውን ወዘተ)፤ በእኩልነት በሚያቅፍ መልኩ እድል በመስጠት ያለው መስፋፋት በሁለንተናዊ አቅጣጫ ለአገሪቱ ልማት የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይልን በማፍራት የአገርን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትና እድገትን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለማፋጠን የሚረዳ ዋነኛው መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም አነስተኛ ውክልና የነበራቸው እና ተጠቃሚ ያልነበሩትን የሕብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ የትምህርት ፖሊሲዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች ያስፈልጋሉ፡፡ አገራችንም ይህንኑ እውን በማድረግ ወሳኝ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ግቦችን በማስቀመጥ ወደ ተግባር ገብታ ተጨባጭ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችላለች፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ፍትሐዊነት ማለት ዜጎች በሚገኙበት/በሚመደቡበት ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ጎሣ፣ ዘር፣ ፆታ፣ ከባቢያዊ /ጂኦግራፊያዊ መኖሪያ፣ ወዘተ ሳይወሰኑና ልዩነት ሳይደረግባቸው ችሎታ፣ ዝግጁነትንና ተነሳሽነት መሰረት ባደረገ መንገድ እኩል የትምህርት እድል ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም በአገራችን፡ የዜጎችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳትፎን በማሳደግ በልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ልማቱን በማፋጠን ረገድ የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ የሚያስችል ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀምጠዋል፡፡ በተያያዥነትም የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለመተግበር የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችና ማኑዋሎች ተዘጋጅተው በስራ ላይ ውለዋል፡፡

በዚህም መሰረት የከፍተኛ ትምህርት የተሳትፎ አቅምን ከማስፋፋት ባሻገር ፍትሃዊነትንና እኩል ተጠቃሚነትን ለማሻሻልም ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎች ፍትሃዊ ሃገራዊ ስርጭት ባለው መልክ ተመስርተዋል፡፡ የመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የከፍተኛ

ትምህርትን በፍትሐዊነት ማስፋፋት መነሻውን 2002 ዓ.ም በማድረግ ከተጣለው ግብ አኳያ ገና ያልተሻገርናቸው ጥረት ጠያቂ ጉዳዮች ቢኖሩብንም በርካታ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

### 3.1.2.1. ሥርዓተ-ፆታ

በአገራችን ባለፉት 10 ዓመታት በከፍተኛ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ በእጅጉ ቢያድግም እንኳ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ያለው አለመመጣጠን እስከ አሁንም ድረስ ጎልቶ ይታያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የትምህርት ሚኒስቴር የ2006 ዓ.ም ዓመታዊ ስታቲስትክስ መረጃ እንደሚያሳየው በቅድመ ምረቃ በመደበኛው ትምህርት በመጀመሪያው የዕ.ት.ዕ መነሻ በተደረገው 2002 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት አጠቃላይ ተሳትፎ 420,387 የነበረ ሲሆን በ2006 ዓ.ም ወደ 593,571 አድጓል፡፡ በዚህም ወቅት ማለትም በ2002 ዓ.ም የነበረው የሴቶች ተሳትፎ 113,504 መነሻ በማድረግ የ2006 ዓ.ም 179,571 በመድረሱ የሴት ተማሪዎች ቁጥር በ58% ማደግ ችሏል፡፡ ይህ እድገት አበረታች ቢሆንም የከፍተኛ ትምህርትን በፍትሐዊነት ከማሰራጨት አኳያ ሲታይ በ2002 ዓ.ም በመደበኛው የቅድመ ምረቃ መርሀ ግብር የሴቶች ተሳትፎ (ከአጠቃላዩ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ መርሀ ግብሮች) የተማሪዎቹ ቁጥር 27% የነበረ ሲሆን በ2007 ዓ.ም 32% ደርሷል፡፡ በቅድመ ምረቃው ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ የአጠቃላዩን 32% መድረስ በአገራችን ትምህርት ፖሊሲና ስትራቴጂ በተቀመጠው መሰረት በከፍተኛው ትምህርት ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ እያደገ መምጣቱን ያመለክታል፡፡ ለዚህ ተሳትፎ እድገት አስተዋጽዖ ካደረጉት በልዩ ድጋፍ ወደ ከፍተኛ ትምህርት እንዲገቡ የመግቢያው ነጥብ በተወሰነ ነጥብ ዝቅ መደረጉ አንደኛው ነው፡፡

ከቀረበው መረጃ በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ እየጨመረ መሆኑን መገንዘብ ቢቻልም በአሁኑ ግዜ በቅድመ ምረቃው ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ የአጠቃላዩን 32% ብቻ መሆኑ፣ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ይደረስበታል ተብሎ ከተቀመጠው ግብ (40%) አለመደረሱን ያሳያል፡፡ ያስቀመጥነው የድህረ መረቃ የተሳትፎ ግብ በሚፈለገው ደረጃ አልተሳካም ብቻ ሳይሆን የሴት ተማሪዎች የመዝለቅ አቅም አነስተኛ እንደሆነም ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ባደረገው አንድ ጥናት እንደተመለከተው በጥናቱ በተካተቱት የአካዳሚክ ድጋፍና የህይወት ክህሎት ስልጠና በአግባቡ ባልተከናወነባቸው በርካታ ዩኒቨርስቲዎች በርካታዎቹ ሴት ተማሪዎች በገቡበት አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ (ከ11% - 40%) በአካዳሚክ ውጤታማነት ችግር ምክንያት በማቋረጥ መዝለቅ እንዳልቻሉ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በትምህርት ፖሊሲው እንደተቀመጠውና እየተተገበረውም እንዳለው በልዩ ድጋፍ ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግባት ቀጣይ ሆኖ የመዝለቅ ምጣኔውንና ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ የሚሰራው ስራ

ተጠናክሮ በሚመለከታቸው አካላት (ትምህርት ሚኒስቴር) ድጋፍና ክትትል እየተደረገበት ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መደበኛ ባልሆኑ የቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞች በተከታታይ መርሀ ግብሮች 42.6% በመድረስ አንጻራዊ በሆነ መልክ ከፍ ብሎ መታየቱ አማራጭ የትምህርት መርሀ ግብርን መጠቀም ለሴቶች ያለባቸውን የቤት ውስጥ ኃላፊነትና ስራ ጫና ተቋቁመው ተሳትፏቸውን ለማሳደግ አበረታች ማሳያ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ስለሆነም በሁሉም መርሀ ግብሮች ተጠቃሚ በመሆን የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ለሴቶች በሚመች መልክ የማጠናከርና ጥራትን ታሳቢ ያደረገ የማስፋፋት ሥራን መሥራት ያስፈልጋል፡፡

እንደ ቅድመ ምረቃው ሁሉ በድህረ ምረቃው መርሀ ግብርም የሴት ተማሪዎች የተሳትፎ ድርሻ የተሻሻለ ቢሆንም ከዕቅድ አንጻር ገና ይቀረዋል፡፡ የመጀመሪያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ መነሻ ባደረገው ዓመት 2002 ዓ.ም የነበረውን 11.9% የሴቶች ድህረ ምረቃ ተሳትፎ በ2006 ዓ.ም ወደ 19.5% ማድረስ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በ2007 ዓ.ም ሊደረስበት ከተጣለው ግብ 25% አኳያ ዒላማ አድርገን ወደ ተነሳንበት ባለመደረሱ በቀጣይ የተጠናከረና የሁሉንም ትኩረት የሚሻ ስራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ስኬት መለካት ያለብን በመጀመሪያው የዕ.ት.ዕ ካስቀመጥነው ዕቅድ አንጻር ብቻ ሳይሆን ከረዥም ጊዜ ራዕያችንም ጋር በማነጻጸር ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2012 UNESCO ባወጣው መረጃ መሰረት በከፍተኛ ትምህርት የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ እንደ ሀገራቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ እንደሚለያይ አስቀምጧል (ግራፍ 1)፡፡ ለምሳሌ፡- በከፍተኛ ደረጃ ያደጉ ሀገሮች የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ድርሻ እስከ 55% የሚደርስ ሲሆን በአንጻሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች ይህ አሃዝ 40% ገደማ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የደረሰችበት የሴቶች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ድርሻ (32%) ከሰሃራ በታች ያሉት የአፍሪካ ሀገሮች አማካይ ድርሻ (38%) ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው፡፡ ከራዕያችን አንጻር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ቢያንስ የታችኛው መካከለኛ ገቢ ምድብ የገቡ ሀገሮች ያሉበትን የሴቶች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ድርሻ (45%) ለመድረስ ግብ አስቀምጦ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡




ግራፍ1. እ.ኤ.አ. በ2012 በተለያዩ የዓለም ከባቢዎች ሴት ተማሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ የነበራቸው ድርሻ (%)

በመሆኑም በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የሴቶችን ድርሻ በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ ትምህርት ላይ ፍትሐዊ የሆነ ተሳትፎን ለማምጣት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የተጠናከረ ስራን መስራት የግድ ይላል፡፡ ይህም ሴቶች በፍትሐዊነት  ትምህርት ተጠቃሚ ከመሆን አኳያ በሁሉም አካላት ከፍተኛ ርብርብና ጥረትን የሚጠይቅ ስራን መስራት ይጠይቃል፡፡

### 3.1.2.2 ክልላዊ ሁኔታ

እንደሚታወቀው በታሪክ ሂደት በርካታ ክልሎች እኩል የትምህርት ተሳትፎና ተጠቃሚነት ሳያገኙ ቆይቷል፡፡ መንግስት የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ከቀረጸ በኋላ በእነዚህ ክልሎች የትምህርት ተደራሽነት አድጓል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ  ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ነገር ግን ክልሎቹ ረዘም ላለ ጊዜ የተረሱና ኋላ ቀር በሆነ ማህበረ-ኢኮኖሚ ላይ የተመሰረቱ፣ በተለይ በአርበቶ አደርነት የሚተዳደሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተከታታይ በሚከሰተው ድርቅ፤ የውሀና የግጦሽ ዕጥረት ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ የሚዘዋወሩ

በመሆናቸው፣ መሰረተ ልማትን በሚሟላት በተፈለገው ፍጥነት የትምህርት ተጠቃሚዎች እንዳይሆኑ ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል፡፡

በክልሎች መካከል የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ያለው ልዩነት በሚመለከት ቀጥተኛ መረጃ ባይኖርም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ያለውን ሁኔታ ግን ማየት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በ2006 ዓ.ም ያለውን የትምህርት ተሳትፎ ስንመለከት በሚጠበቀው የዕድሜ ክልል ወደ መሰናዶ የገቡ ተማሪዎች (17-18 ዓመት) መረጃ እንደሚያሳው የመሰናዶ ትምህርት ንጥር ተሳትፎ ከፍተኛው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር (33.5%) ሲሆን በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘው ደግሞ አፋር (1.3%)፣ ከዚያም ሶማሌ እና ኦሮሚያን (3.2%) እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህ መረጃ በየጊዜው የእኩል ተጠቃሚነት እድል እያደገ የመጣ ቢሆንም፤ አሁንም በክልሎች መካከል በሚጠበቀው እድሜ የመሰናዶ ትምህርት እኩል የተሳትፎ ዕድል አለመኖሩን በግልጽ ያሳያል፡፡የመሰናዶ ትምህርት የተሳትፎ ዕድል እኩል አለመሆኑ በራሱ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ባለው ተጠቃሚነት የሚገድብ በመሆኑ በከፍተኛ ትምህርት ላይ ያለውን ክልላዊ የተሳትፎ ክፍተት መቀጠሉን ያሳያል፡፡

በተጨማሪም በነዚህ አካባቢዎች የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላና ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን አንደኛው ተግዳሮት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የእነዚህ ዜጎች የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚነት ዝቅተኛ መሆን፡ ቀጣይ ወደ ሆነው እርከንና ወደ ከፍተኛ ትምህርት የመዝለቅ ዕድል ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ ተግዳሮቱን ለመቅረፍ በርካታ ስራዎች (የትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ የተለያዩ ልዩ ልዩ ድጋፎችን ማድረግ ወዘተ) እየተሰሩ ያሉ ቢሆንም በየደረጃው ያለው የተሳትፎ ምጣኔ አነስተኛ ነው፡፡

በመሆኑም ይህንን ክፍተት በመዝጋት ሁሉንም ክልሎች እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ ተጀምሮ ያለው ትምህርትን የማስፋፋትና የተደራሽነት ስትራቴጂውን በላቀ ደረጃ ለመፈጸም በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላና ተሳትፎ ፍትሐዊነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ለማድረግ በቁርጠኝነት መስራትን ይጠይቃል፡፡

### 3.1.2.3. የማህበረ-ኢኮኖሚ ደረጃ ሁኔታ

በዜጎች መካከል እኩል የትምህርት ተሳትፎ እንዳይኖር ምክንያት የሆነው ሌላው ጉዳይ የተማሪዎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸው

የማህበረሰብ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች የተሻለ ኑሮ ከሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲነጻጸሩ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚነታቸው አነስተኛ ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሱት ቤተሰቦቻቸው ልጆቻቸውን ደግፈው ለማስተማር አቅም ማጣታቸው፣ ለትምህርት የሚያስፈልጋቸው ግብዓቶች አለመሟላት፣ ከድህነት የተነሳ የሚከሰት የጤና ችግርና አሉታዊ የማህበራዊ ተጽዕኖዎች እንደሆኑ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የእነዚህ ችግሮች መከሰት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት አዘውትረው እንዲቀሩ፣ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ እንዲያቋርጡ፣ በዝግጁነት ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ፣ በአጋጣሚ ሆኖ ትምህርታቸውን ቢቀጥሉም ውጤታማ እንዳይሆኑ እንደሚያደርጋቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በ2003 ዓ.ም በተደረገ ጥናት እንደተመለከተው ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸው የህብረተሰብ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች በመዋዕለ-ህፃናት ውስጥ ያላለፉ ስለሆነ የንባብና የመሰረታዊ ስሌት ችግር እንደሚታይባቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም ለመደበኛው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ሳያደርጉ ወደ ትምህርት ቤት በመሄዳቸው በቀላሉ ተስፋ እንዲቆርጡና ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ አድርጓቸዋል፡፡ አልፎ አልፎም የህፃናቱን አቅም ያላገናዘበ የገቢ ማመንጫ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ስለሚደረጉ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለመቀጠልና ውጤታማ ለመሆን ይቸገራሉ፡፡ ይህም በየደረጃው ያለውን የትምህርት እርከኖች በቅደም ተከተል ከመጀመሪያ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ብሎም ወደ ከፍተኛ ትምህርት የመቀጠልና የመድረስ ዕድል አሳጥቷቸዋል፡፡

በመሆኑም ከዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ካለው የማህበረሰብ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በተገቢው ሁኔታ ሳያቋርጡ ከፍተኛ ትምህርት ደርሰው የማጠናቀቅ ብቃትና ፍትሐዊ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በትምህርቱ ሴክተር በየደረጃው የተጠናከረ ተያያዥነት ያለው ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

### 3.1.2.4. የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ሁኔታ

በአገራችን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ውስጥ ሁሉም ዜጎች/ተማሪዎች እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው (ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ በልማት ያላደጉ አካባቢዎች፣ ወዘተ) መማር እንዲችሉ አስቀምጧል፡፡ ይህም መንግስት ዜጎቹ ፍትሐዊ የትምህርት ተሳትፎንና ተደራሽነትን ፖሊሲ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ያለውን ቁርጠኝነት በማረጋገጥ የተለያዩ ዓለማቀፋዊ ስምምነቶችን ፈርሟል፡፡ እነዚህን ፖሊሲዎችንና ስምምነቶችንም ለማስፈጸም የሚያስችሉ ልዩ ልዩ

ስልቶች፣ ደንቦችና መመሪያዎችም ተቀርጸዋል፡፡ ይህም ትምህርት የዜጎችን ዲሞክራሲያዊ እሴቶችንና እኩልነትን ከሰብዓዊ መብት ጋር አጣምሮ ሊያስገኝ የሚችል መሳሪያና ድህነትን በመቀነስ ብሎም በማጥፋት ሁሉም ዜጎች በአገሪቱ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ መሆኑን ፖሊሲው ያስቀምጣል፡፡
ይህንንም መሰረት በማድረግ በሁሉም የትምህርት እርከኖችና የትምህርት ተቋማት ውስጥ አካቶ ትምህርትን በማስፋፋትና በማጠናከር ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ተጠቃሚነት በማሳደግ ተደራሽነትን በማስፋት ፍትሐዊ የሆነ ስርጭትን ዕውን ለማድረግ ዋነኛ መንገድ መሆኑን በመገንዘብ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ ለአብነት ያህል ብንመለከት በትምህርት ዘርፉ የልማት ዕቅድ (ESDP-IV) ላይ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ተሳትፎ ለማሳደግ በየትምህርት እርከኑ ግብ ተጥሎ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በ2002 ዓ.ም (2009/10) የነበሩትን 398 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር መነሻ በማድረግ በ2007 ዓ.ም (2014/15) 946 ለማድረስ ግብ በማስቀመጥ የተግባር እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በ2005 ዓ.ም የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው በአምስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ብቻ 1,000 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በተቋማቱ ውስጥ ተካትተው እየተማሩ ስለመሆናቸው ተመልክቷል፡፡ ይህም ከተቀመጠው ግብ አኳያ ሲታይ አበረታች የሆነ ለውጥ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሊታይ የሚገባው ግን በአሁኑ ጊዜ ካለው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ተያይዞ በሀገራችን ሊኖር የሚችለው የአካል ጉዳተኞች ቁጥር እንደ የዓለም ጤና ድርጅትና የዓለም ባንክ ዘገባ ከጠቅላላው ህዝብ ቁጥር ውስጥ 16 በመቶ የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ጋር ሲነፃፀር በርካታዎቹ አካል ጉዳተኛ ህፃናት በተለያዩ የትምህርት ዕርከኖች ውስጥ የትምህርት ዕድል ሳያገኙ ከትምህርት ቤት ውጭ መገኘታቸው ነው፡፡ በተጨማሪም በ2006 የትምህርት ሚኒስቴር አመታዊው የትምህርት ስትስቲክስ መረጃ በ1ኛ ደረጃ በሁለቱም ሳይክል (1ኛ - 8ኛ) 70,477፣ በ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል (9ኛ-10ኛ) 6,020 እንዲሁም በሁለተኛው ሳይክል (11ኛ-12ኛ) 1,248 ልዩ ፍላጎት ያላቸው የትምህርት እድል አግኝተው በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች መኖራቸው፤ ከእርከን ወደ እርከን ባለው ሽግግር ወቅት ከፍተኛ የሆነ መጠነ ማቋረጥ እንደሚታይ እነዚህ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ላይ ካሉ አጠቃላይ የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በደረጃው ሊኖሩ ከሚገባቸው ተማሪዎች መካከል 1.9 በመቶ ብቻ በትምህርት ገበታ ላይ እንደሚገኙ ተመልክቷል፡፡ ይህም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመድረስ ያላቸው ዕድል ጠባብ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን በተዘዋዋሪ ግን በየትምህርት ዕርከኖቹ ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች ተስማሚ የሆኑ ድጋፎችን በበቂ ደረጃ እንደማያገኙ የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ትምህርት ተሳትፎ በየእርከኑ ለማሳደግ የትምህርት ዘርፉ ልዩ የትኩረት መስክ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር በጅምር ያለው የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት አገልግሎቱን በማጠናከርና በማስፋት በሁሉም የትምህርት ዕርከኖች የትምህርትን ተደራሽነት ለማረጋገጥና የልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎችን ፍትሐዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

### 3.1.3. አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት ትንበያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ በመቀጠል የሰለጠነ የሰው ሀይል በበቂ ደረጃ ማፍራት ይጠበቅባታል፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ከታች በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ የመጣ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የሚከታተሉት ተማሪዎች ቁጥር ጋር ተያይዞ የሚኖረውን ከፍተኛ ፍላጎት ማሟላት ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም መረጃዎች እንዲሚያሳዩት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የመዝለቅ አቅም ወይም የ10ኛ ክፍል የብሔራዊ ፈተና ውጤት ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ 2 ነጥብ እና ከዚያ በላይ ያመጡትን ተማሪዎች ብቻ ብንወስድ በ2001 ዓ.ም 49.9% ከነበረው በ2005 ዓ.ም ግን ወደ 67.9% አድጓል፡፡

በ10ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና 2 ነጥብ እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች ድርሻ መጨመሩ በመርህ ደረጃ የሚያሳየው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመሸጋገር እየጨመረ የመጣ ፍላጎትን ነው፡፡ በተያየዘ ሁኔታም ይህ አሃዝ የመሰናዶ ትምህርትን አጠናቀው ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥርን ያሳድጋል፡፡ በዚህ መሠረት የመሰናዶ ትምህርት የጥቅል ተሳትፎ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ካስቀመጥነው ሀገራዊ ራዕይ አኳያም በሚቀጥሉት ዓመታት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጥቅል ተሳትፎ ምጣኔ ማሳደጋችን አይቀርም፡፡ የመካከለኛ ገቢ የደረሱ ሀገሮች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጥቅል ተሳትፎ ከ60- 80% እንደሚደርስ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ይህን ከፍተኛ የሆነውን የተማሪዎች ቁጥር ሊያስተናግዱ የሚችሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የማስፋፋት ሥራ በመንግስት በኩል እንደ አቅጣጫ መያዝ ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት የቀጣይ የከፍተኛ ትምህርት የተሳትፎ እድገት ደረጃን አሁን ካለው የአጠቃላይ ትምህርት ተሳትፎ አንጻር መገመት ይቻላል፡፡ በሠንጠረዥ 1 እንደተመለከተው የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ተማሪዎች

የተሳትፎ መጠንና በየትምህርት ደረጃው የሚከሰተው የትምህርት ብክነት (attrition rate) ታሳቢ በማድረግ በሚቀጥሉት ዓመታት ሊኖር የሚችለውን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ለመተንበይ (enrolment projection) ተሞክሯል (ሠንጠረዥ 2)፡፡ ትንበያው ተማሪዎች ከአንድ የትምህርት ክፍል ወደሚቀጥለው ክፍል በሚያደርጉት ሽግግር የሚፈጠረውን የተሳትፎ ለውጥ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ የተማሪዎች ሽግግር የክትትል ስርዓት (cohort tracking system) መነሻ የሚያደርገው በእያንዳንዱ የትምህርት ደረጃ የሚኖሩ አጠቃላይ ሀገራዊ የተማሪዎች ብዛት እና ተማሪዎቹ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚያደርጉት ዝውውር የሚኖረው የትምህርት ብክነት መጠንን (attrition rate) ነው፡፡ ለምሳሌ በ2012 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገቡ መደበኛ ተማሪዎች በ 2003 ዓ.ም 4ኛ ክፍል የነበሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በ2003 ዓ.ም 5ኛ ክፍል የነበሩት ደግሞ ወደ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገቡት በ2011 ዓ.ም ይሆናል፡፡ ስለዚህ በተማሪዎቹ የዝውውር ሂደት ያለው የመዝለቅ መጠን ከታወቀ በየዓመቱ ወደ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገቡት አመላካች ሊሆን የሚችል ግርድፍ የተማሪዎች ብዛት ማስላት (መተንበይ) ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት በየዓመቱ በትምህርት ሚኒስቴር እየታተሙ የሚወጡትን ስታቲስትካዊ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በየደረጃው የነበሩትን የብክነት መጠን አሃዞችን በመጠቀም የትንበያ አማራጮቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **አማራጭ 1፡** ባለፉት አምስት ዓመታት (1999-2003 ዓ.ም.) የነበረው የትምህርት ብክነት መጠን እንዳለ ቢቀጥል
- **አማራጭ 2፡** የትምህርት ብክነት መጠን በአማራጭ 1 ከተቀመጠዉ በ50% ቢቀንስ
- **አማራጭ 3፡** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት የትምህርት ብክነት መጠን ከአማራጭ 1 በ 98% ቢቀንስ የሚል መነሻ ሃሳብ ተወስዷል፡፡

**ሠንጠረዥ1.** የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በተለያዩ አማራጮች ከአንድ የትምህርት ክፍል ወደሚቀጥለው ክፍል የሚዘዋወሩበት መጠን (በመቶኛ)

| በትምህርት የመዝለቅ አቅም | 4ኛ ክፍል | 5ኛክፍል | 6ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል[1] |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አማራጭ 1 | 91.8% | 90.8% | 93.3% | 91% | 87.7% | 64.7% | 20% |
| አማራጭ 2 | 95.9% | 95.4% | 96.65% | 95.5% | 93.85% | 82.35% | 20% |
| አማራጭ 3 | 98.36% | 98.26% | 98.66% | 98.82% | 97.75% | 94.9% | 20% |

[1] ይህ የትምህርት ፖሊሲውን መነሻ ያደረገ ሲሆን ከ10ኛ ክፍል ወደ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገቡትን በሥራ ላይ ያለውን የተማሪዎች ምጣኔ ይመለከታል፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ1 የተገለጹትን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን የመዝለቅ አቅም መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ያለውን በሶስቱም አመራጮች ወደ አሥረኛ ክፍል የሚደርሱ ተማሪዎችን ብዛት ማስላት ይቻላል (ሠንጠረዥ3)፡፡

የዓመቱ የጠቅላላ ተሳትፎ መጠን ለማስላት ታሳቢ የተደረጉ ነገሮች በሠንጠረዥ 2 ላይ የቀረበው የመጀመሪያ ዓመት የተማሪዎች ቅበላ መጠን፣ የትምህርት ዘመን ርዝማኔ፣ ምረቃና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ መረጃው የአጠቃላይ ትምህርት የመዝለቅ ምጣኔ ደረጃ ለከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ከፍተኛ ተፅእኖ እንዳለው ያሳያል፡፡ በቀረቡት አማራጮች በ2012 ሊኖር የሚችለው ዝቅተኛው ተሳትፎ 547,511 ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 1,085,381 ነው፡፡ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እና በግል ከሚፈተኑ ተማሪዎች በ 5% ምጣኔ ቢጨምር ተሳትፎው ከ 645,448 እስከ 1,185,381 ይደርሳል፡፡ በሁለተኛው አማራጭ ይህ አሃዝ 850,897 ይሆናል፡፡ እዚህ ጋር ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ የ20፡80 ቀመር (የከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ድርሻዎች) ከተቀየረ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡት ተማሪዎች ቁጥርም ከፍ ወይም ዝቅ ሊል እንደሚችል ነው፡፡

**ሠንጠረዥ2.** በየዓመቱ በዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ አጠቃላይ መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ብዛት ወይም ተሳትፎ

| ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበት የትምህርት ዘመን (ዓ.ም.) | ጠቅላላ የተማሪዎች ተሳትፎ | | |
|---|---|---|---|
| | አማራጭ 1 | አማራጭ 2 | አማራጭ 3 |
| 2006 | 356,140 | 375,541 | 375,541 |
| 2007 | 408,723 | 443,172 | 510,713 |
| 2008 | 419540 | 523,691 | 628,578 |
| 2009 | 441328 | 590,184 | 733,019 |
| 2010 | 475239 | 603,441 | 765,069 |
| 2011 | 492,595 | 697,791 | 911,213 |
| 2012 | 547,511 | 810,378 | 1,085,381 |

ትንበያውና በ2007 ዓ.ም በተጨባጭ ያለው መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ቁጥር (387,565) ተቀራራቢ ነው፡፡ የሚታየው የተወሰነ ልዩነት በአማራጭ አንድ የቀረበው የብክነት መጠን በተግባር

አነስ ያለ መሆን ወይም የግል ተፈታኞች ቁጥር በምክንያትነት ሊገለጽ ይችላሉ፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የመደበኛ ተማሪዎች ተሳትፎ አቅማችን ሲያድግ የክረምት፣ የማታና የርቀት ትምህርት ተሳትፎ መጠንም ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ደረጃ ያድጋል፡፡ ለምሳሌ፡- በአማራጭ ሁለት የመደበኛ ተማሪዎች ተሳትፎ አቅም 810,378 እንደሚደርስ የተተነበየ ሲሆን ከመደበኛ ውጭ ባሉት መርሀ ግብሮች ተመሳሳይ ቁጥር በመጨመር 1.0 ሚሊዮን ተማሪዎች ገደማ ሊኖሩን ይችላሉ ማለት ነው፡፡

በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ መሰረት አጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 73,952,991 እንደነበረ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታቲስትክስ ባለሥልጣን ሪፖርት ሲያመለክት በ2006 ዓ.ም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ባወጣው ትንበያ በ2009 ዓ.ም ደግሞ 94,351,001 እንደሚሆን ያሳያል፡፡ በዚህ 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚኖረው የህዝብ ቁጥር አማካይ ዓመታዊ ዕድገት 2.79% እንደሆነ ማስላት ይቻላል፡፡ ይህንን አማካይ ዕድገት በመጠቀም እስከ 2012 ዓ.ም የሚኖረው የህዝብ ቁጥርም ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ተገምቷል፡፡

**ሠንጠረዥ. 3.** ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም ባለው ወቅት ሊኖር የሚችል የአገራችን ህዝብ ብዛት ትንበያ እና በአማራጭ 1 የከፍተኛ ትምህርት መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ቁጥርና ጥቅል ተሳትፎ

| ዓመት ምህረት | የተተነበየ የህዝብ ብዛት | የከፍተኛ ትምህርት ዕድሜ ክልል* (ከ19-23**) ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ቁጥር | በዝቅተኛው አማራጭ (አማራጭ 1) የሚኖረን የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥርና ጥቅል ተሳትፎ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መደበኛ | መደበኛ ባልሆነ*** | ድምር | ጥቅል ተሳትፎ (%) |
| 2008 | 92,206,005 | 7284274 | 419540**** | 369810 | 789350 | 10.59% |
| 2009 | 94,351001 | 7453729 | 441328 | 389017 | 830345 | 11.14% |
| 2010 | 96986407 | 7661926 | 475239 | 418908 | 894147 | 11.67% |
| 2011 | 99695426 | 7875938 | 492,595 | 466694 | 959289 | 12.18% |
| 2012 | 102480114 | 8095928 | 547,511 | 485,529 | 1,033,040 | 12.76% |

**ሠንጠረዥ**. 4. ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም ሊኖር የሚችል የሀገራችን ህዝብ ብዛት ትንበያ እና በአማራጭ 2 የሚኖር የከፍተኛ ትምህርት መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ቁጥርና ጥቅል ተሳትፎ

| ዓመተ ምህረት | የተተነበየ የህዝብ ብዛት | በከፍተኛ ትምህርት ዕድሜ ክልል (ከ19-23) ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ቁጥር | በከፍተኛው አማራጭ (አማራጭ 2) የሚኖረን የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥርና ጥቅል ተሳትፎ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መደበኛ | መደበኛ ባልሆነ | ድምር | ጥቅል ተሳትፎ (%) |
| 2008 | 92,206,005 | 7284274 | 523,691 | 389521 | 913,212 | 12.54% |
| 2009 | 94,351001 | 7453729 | 590,184 | 438979 | 1,029,163 | 13.81% |
| 2010 | 96986407 | 7661926 | 603,441 | 448839 | 1,052,280 | 13.73% |
| 2011 | 99695426 | 7875938 | 697,791 | 519017 | 1,216,808 | 15.45% |
| 2012 | 102480114 | 8095928 | 810,378 | 602759.2 | 1,413,137 | 17.45% |

በዝቅተኛው አማራጭ በ2012 ዓ.ም የምንደርስበት 12.76% በሠንጠረዥ 3 ለማየት ተችሏል፡፡ በከፍተኛ አማራጭ (አማራጭ 2) ደግሞ በ2012 በከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ የምንደርሰው 17.45% ሲሆን የሁለቱን አማካይ ብንወስድ ግን የተሳትፎ ግባችን 15% ገደማ ይሆናል፡፡ የታችኛው መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት የ10 ዓመት አማካይ ጥቅል ተሳትፎ 16%

አካባቢ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል የአንድ ሀገር የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግ ትምህርት (Elite Education) ከ15% በታች መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ አኳያ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ውስጥ ሀገራችን ከElite Education እንድትወጣ የከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎው ቢያንስ 15% እንዲደርስ ግብ አስቀምጦ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ የተሳትፎ ትንበያው በሠንጠረዥ 5 ተስተካክሏል፡፡

ሠንጠረዥ5. በመንግስት ተቋማት ውስጥ በየዓመቱ የሚገቡና አጠቃላይ ነባር የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የያዘ ሠንጠረዥ

| ዓ.ም | የተተነበየ የህዝብ ብዛት | የከፍተኛ ትምህርት ዕድሜ ክልል (ከ19-23) ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ቁጥር | በተስተካከለው አማራጭ (አማካይ) የሚኖረን የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥርና ጥቅል ተሳትፎ | | | | በየዓመቱ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሊገቡ የሚችሉ አዲስ የመደበኛ ተማሪዎች ቁጥር (ከጠቅላላ መደበኛው1/3) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መደበኛ | መደበኛ ባልሆነ | ድምር | ጥቅል ተሳትፎ (%) | ጠቅላላው | በመንግስት ተቋማት (92.6%) |
| 2008 | 92,206,005 | 7284274 | 418,132 | 368,570 | 786,702 | 10.8% | 139,377 | 129,063 |
| 2009 | 94,351001 | 7453729 | 463,514 | 408,572 | 872,086 | 11.7% | 154,505 | 143,072 |
| 2010 | 96986407 | 7661926 | 482,569 | 425,369 | 907,938 | 11.85% | 160,856 | 148,953 |
| 2011 | 99695426 | 7875938 | 552,560 | 487,064 | 1,039,624 | 13.2% | 184,187 | 170,557 |
| 2012 | 102480114 | 8095928 | 645,448 | 568,941 | 1,214,389 | 15% | 215,149 | 199,228 |

በዚህ በ15% የጥቅል ተሳትፎ ትንበያ መሠረት በ2012 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ዕድሜ ክልል (ከ19 - 23 ዓመት) ውስጥ ከሚደርሱት ተማሪዎች መካከል የሚኖረው ጥቅል የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎው መጠን 1,214,389 የሚደርስ ሲሆን በአጠቃላይ በመደበኛው መርሀ ግብር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩት የተማሪዎች ብዛት 645,448 ይሆናል፡፡ የ2006 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ ስታቲስትካዊ መረጃ እንደሚያሳየው ከአጠቃላይ መደበኛ ተማሪዎች ውስጥ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን የሚከታተሉት 92.1% ነበር፡፡ ይህንን ድርሻ ታሳቢ በማድረግ በ2012 ዓ.ም ይኖሩናል ተብሎ ከሚገመቱት 645,448 መደበኛ ተማሪዎች ውስጥ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩት የመደበኛ ተማሪዎች ብዛት 597,685 ይሆናል ተብሎ የተተነበየ ሲሆን ከላይ በሠንጠረዥ 7 እንደተመለከተው በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚመደቡ አዲስ የመደበኛ ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ 199,228 እንደሚደርስ ተሰልቷል፡፡ ከላይ በ15% የጥቅል ተሳትፎ ትንበያ መሰረት የተሰላው የጥቅል ተሳትፎ የቅድመ ምረቃ ብቻ ሳይሆን የድህረ ምረቃ ተማሪዎችንም ያካትታል፡፡ ከተተነበየው የተሳትፎ መጠን 10% የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ድርሻ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ ስለሆነም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች

የተማሪዎች ተሳትፎ መጠንን በ59,769 በመቀነስ ወደ 537,917 ዝቅ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህንን የተሳትፎ ግብ ለማሳካት የሚያስችሉ ደግሞ በርካታ ምቹ ሁኔታዎች አሉ፡፡

የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የነበረው የመደበኛ ተማሪዎች ተሳትፎ የማስፋፋት ግብ (በ2002 ዓ.ም ከነበረው ከ200,000 ገደማ ወደ 467,000) ከፍተኛ (167%) ነበር፡፡ ከዚህ ጋር ሲነጻጸር ይህ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመደበኛ ተማሪዎች የተሳትፎ ማስፋፋት ግብ (በ2012 ዓ.ም 645,448) ከአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ (2007 ዓ.ም) ከተቀመጠው የተሳትፎ ግብ (467,000) ጋር ሲነጻጸር ዕድገቱ 38% ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጥራትና ማስፋፋትን ጎን ለጎን ለማሳደግ የሚያስችል ምክንያታዊ ግብ ነው፡፡ በቀጣይነት እያደገ ያለው ኢኮኖሚያችንም ተጨማሪ የማስፋፋቱን ወጪ ለመሸፈን ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ አኳያ አሁን ያሉት በተለይ አዳዲስ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግንባታቸው ሲጠናቀቅ ሙሉ አቅማቸውን አሟጠው ስለሚጠቀሙ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪ ማስተናገድ ይችላሉ፡፡ የነባር ዩኒቨርሲቲዎች የቅበላ አቅም ማሳደግ እንደተጠበቀ ሆኖ ግቡን ለማሳካት እንደ አስፈላጊነቱ የተወሰኑ አዳዲስ ተቋማት መመስረትም ይኖርብናል፡፡ በሌላ በኩል የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ድርሻ ጥራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት አሁን ካለበት 7.4% ቀስ በቀስ እንዲያድግ በማድረግ በመንግስት ተቋማት ላይ የሚኖረውን ጫና መቀነስ ይቻላል፡፡

ከተደረገው የሁኔታ ትንተና በመነሳት የሚከተሉት ተግዳሮቶች በቀጣይ ሊፈቱ እንደሚገቡ በዚህ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህም በቅድመ ምረቃው ትምህርት ፕሮግራም በመንግስታዊውም ሆነ በግሉ ዘርፍ የከፍተኛ ትምህርት በማስፋፋት ተደራሽ ከመሆን አኳያ እድገት ቢኖርም ከተጣለው ግብ አኳያ ያልተሻገርናቸው ጉዳዮች (ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች በብዛትም በቁጥርም ዝቅተኛ መሆን፣ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የገቡትም የመዝለቅ አቅም ውሱንነት፣ ወዘተ) መሆናቸው፣ በድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም የመቀበል አቅምም ከተጣለው ግብ አኳያ ዝቅ ማለቱ የሚጠበቀው የሰው ኃይል ማሟላቱ ላይ ያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ በመስፋፋት ላይ ላሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በስታንዳርዱ መሰረት የሚፈለጉትን መምህራን ላይ ዕጥረት እያስከተለ መሆኑ፣ በሌላ በኩል አገልግሎት የጀመሩት ዩኒቨርስቲዎች በሚጠበቅባቸው የመቀበል አቅም ልክ ተቀብሎ ለማስተናገድ ብቁ አደረጃጀቶችን አለመያዛቸው (ላቦራቶሪ፣ ላይብራሪ፣ ወርክ ሾፕ፣ የሰው ኃይል ወዘተ)፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግንባታዎች ወቅታቸውን ጠብቆ ያለመጠናቀቅ፣ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች (ሴቶች፣ ታዳጊ ክልሎች፣ የገጠር አካባቢዎችን፣ ልዩ ፍላጎት ወዘተ) ከታችኛው እርከን እስከ መሰናዶ በሚደርሱበት አግባብ

ተጠናክሮ የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስርዓት አለመጠናከሩ፣ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች መንግስት በልዩ ድጋፍ ቅበላ እየተደረገ ያለ ቢሆንም ከገቡ በኋላ የሚደረገው የማብቃት ድጋፍ አነስተኛ መሆኑ እና በቅድመ ምረቃ ፕሮግራምም ሆነ በድህረ-ምረቃ ፕሮግራም  በከፍተኛ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት አነስተኛ መሆን በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 3.2. የትምህርት አግባብነትና ጥራት

የትምህርት ጥራት በዚህ ሰነድ አውድ ለታለመ ለአንድ አላማ ብቁ ሆኖ መገኘት ወይም አስቀድሞ የተቀመጠን መስፈርት ማሟላት የሚለውን ትርጉም መውሰድ ይቻላል፡፡ እንዲሁም የጥራት ምንነት የተገልጋዮች እርካታ ጋር ተያይዞ ሊታይም ይችላል፡፡ ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ስፖንሰሮቻቸው የተቋማት ደንበኛ/ተገልጋዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ተገልጋዮች ለሚያጠፉት ገንዘብና ጊዜ ከመቼውም በበለጠ መብታቸውን በመጠቀም በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፡፡ ተመራቂዎች በስራው ዓለም ላይ የሚኖራቸው ተፈላጊነት ያሳስባቸዋል፡፡ በመሆኑም ስለ ትምህርት ጥራትና አግባብነት በቋሚነት እንድናስብ ያደርገናል፡፡

ተቋማት የራሳቸውን ስታንዳርድ በማስቀመጥ ያንኑ ስታንዳርድ ማስቀጠል ይሻሉ፡፡ ይሄንን ለማሳካት ደግሞ በቀጣይነት በትምህርት አሰጣጥ ላይ ለውጥ በማምጣት ጥራትን ማስጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ተቋማት ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ለሚያፈስሱባቸው የባለድርሻ አካላት (ለመንግስት፣ ለህዝቡ ወይም ለግለሰቦች) ተጠያቂነት አለባቸው፡፡  ለጥራት የሚሰጡት ከፍተኛ ትኩረት ባለድርሻ አካላቱ ትክክለኛ ውሳኔን እንዲወስኑ ያስችላቸዋል፡፡ በመሆኑም ጥራት እንደ ክትትል መሳሪያ ተደርጎም ስለሚወሰድ ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ስታንዳርዶችን መሰረት ያደረጉ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ለጥራት ከፍተኛ ትኩረት በሚሰጥ ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ከግልጽና ያልተማከለ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ተነሳሽነታቸው ላቅ ያለ በመሆኑ ሃላፊነታቸውን ባግባቡ ከመወጣት ባለፈ የትምህርት ክፍሎች ተመጋጋቢ ስራዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ በመከወን ለተገልጋይ እርካታ የሚተጋ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡ በጥራት ላይ ያለማቋረጥ፣ በወጥነት ከተሰራ በሌሎች ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታን እና ዝናን እንድንጎናጸፍ ያስችለናል፡፡

በአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ሊታይ የሚገባው ተመርቀው የሚወጡ ተመራቂዎች የአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ በሚፈለገው ብቃት ደረጃ ተሳትፈው በሚያስመዘግቡት ለውጥ ይሆናል፡፡ የትምህርት ጥራትን ከስርዓት እይታ (system view) አኳያ ስናየው የትምህርት ግብዓቶች (Input sub-system)፣ የትምህርት ሂደት ንዑስ ስርዓት (Process sub-system) እና የጥራት ማረጋገጫ ንዑስ ሥርዓት(Quality Assurance) ወይም የውጤት ንዑስ ሥርዓት (Output sub-system) ትኩረት ይሻሉ፡፡

### 3.2.1. የትምህርት ግብዓትና ሂደት

በመጀመሪያው የዕ.ት.ዕ ዘመን መንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን ከማስፋፋት ጎን ለጎን አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ግብዓቶችን ለማሟላት ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ርብርብ አድርጓል፡፡ ከዚህ አኳያ ነባሮቹም ሆኑ አዳዲስ ተቋማት በሰው ሀይል (በአመራር፣ በመምህራንና በድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች) ለማደራጀት መንግስት ካደረገው ጥረት ባሻገር ዩኒቨርሲቲዎቻችን በቁሳቁስ (በመጽሐፍት፣ በቤተ ሙከራና በወርክሾፕ ወዘተ.) በማጠናከር የተደረገው እንቅስቃሴ መቀጠል አለበት፡፡ ከተቋማቱ ብዛት የተማሪዎቹ ተሳትፎም ከሀገሪቱ አቅምና ከሚጠበቀው የጥራት ደረጃ አንጻር የግብዓት መሟላት ሥራው ገና ብዙ ርቀት መሄድ ይኖርበታል፡፡

መንግስት አዳዲስም ሆኑ ነባር ተቋማት የትምህርት ግብዓቶችን ለማሟላት ከፍተኛ ኢንቬስትመንትና ርብርብ አድርጓል፡፡ ነገር ግን የግብዓት ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በእቅድ ለማሟላት የሚያስችለን የክትትል ስርዓት አልገነባንም፡፡ ከዚህ አኳያ በእያንዳንዱ ተቋም የሚያስፈልገውን ግብዓት ለማሟላት የሄድንበትን ርቀት በእርግጠኝነት ማወቅ ባይቻልም፤ ከዚህ በፊት የተደረገው ኢንቨስትመንት እንደተጠበቀ ሆኖ ማስፋፋቱን ታሳቢ በማድረግ ገና ያልተሻገርነው ተግዳሮት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የትምህርት ሂደት ስርዓት-ትምህርቱን፣ መምኅራንን፣ አስተዳደሩን፣ የግብዓት አቅርቦቶችን እና የድጋፍ አሰጣጥ ሁኔታን በማካተት የለውጥ ንዑስ ስርዓትን (Transformational/ Process sub-system) በማካተት ሊታይ ይችላል፡፡ እንዲሁም የፕሮግራሞቹ አወሳሰን፣ የፕሮግራሞቹ ይዘት፣ የፕሮግራሞቹ አደረጃጀት፣ የመስኮች ምጣኔ እና የተማሪዎች ዳሰሳ ጥናትንም ያካትታል፡፡

የትምህርት ጥራትን በማጎልበት ሂደት ውስጥ ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል የትምህርት ግብዓት (input) እና የትምህርት ሂደት (process) በተማሪዎች ውጤት (output) ላይ ያለውን መስተጋብር ማየት ተገቢ ነው፡፡ ከግብዓት አንፃር መታየት ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች (ስርዓተ ትምህርት፣ የመምህሩ ብቃት፣ የመማሪያ ቁሳቁስ ወዘተ.) የሚያካትት ሲሆን በዋናነት ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ብቃት አንዱ ነው፡፡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከመሰናዶ ትምህርት ወደ ዩኒቨርሲት የሚገቡት ብዙ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤታቸው ከ50% በታች መሆኑን ነው፡፡ በትምህርት መስክ ሲታይ ደግሞ ለኢንጂነሪንግ የሙያ መስክ ቁልፍ በሆኑት በእንግሊዘኛ፣ ሂሳብና ፊዚክስ ትምህርቶች እጅግ ዝቅተኛ ውጤት እንደሆነም በትምህርት ምዘና ላይ የተደረገው የዳሰሳ ጥናት ውጤት መረጃው ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ሲታይ ከ2005 ዓ.ም በፊት በነበሩት 4 ዓመታት የ10ኛ ክፍል የብሔራዊ ፈተና ወስደው ከ 2 ነጥብ በላይ ያመጡት ተማሪዎች ብዛት ከ 49.4 ወደ 74.9% ማደጉ የሚያበረታታ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የተማሪዎች የውጤታማነት ዕድገት በቀጣይነት ከማረጋገጥ አኳያ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በ2006 ዓ.ም. የትምህርት ዘርፍ ዓመታዊ ስታቲስትክስ መረጃ እንደሚያመለክተው በቅድመ-ምረቃ ፕሮግራም ትምህርታቸውን አጠናቅቀው የተመረቁ ተማሪዎች ቁጥር በ2002 ዓ.ም 66,999 ከነበረበት በ2006 ዓ.ም. ወደ 96,980 አድጓል፡፡ ይህም ማለት አማካይ አመታዊ የምሩቃን ቁጥር የእድገት ምጣኔው ወደ 8% ገደማ ደርሷል ማለት ነው፡፡ በአንጻሩም የድህረ-ምረቃ ምሩቃንን ቁጥሩ ስንመለከት በ2002 ዓ.ም 4873 ከነበረበት በ2006 ዓ.ም. ወደ 8021 አድጓል፡፡ ይሄም አሃዙ 10.5 አማካይ ዓመታዊ የእድገት ምጣኔ አሳይቷል፡፡ ነገር ግን በየደረጃው ከሚገቡ ተማሪዎች አንጻር የሚታየው የመዝለቅ ምጣኔ በሚፈለገው ደረጃ አልደረሰም፡፡ ለምሳሌ የሶስተኛ ድግሪ በጊዜ የማጠናቀቅ ምጣኔው አነስተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የተማሪዎችን አነስተኛ የመዝለቅ አቅም ወይም ከፍተኛ ብክነት ሲሆን አነስተኛ የመዝለቅ አቅም ወይም ከፍተኛ ብክነት ማለት ደግሞ ጥራት የጎደለው የትምህርት ስርዓት ምልክት መሆኑን የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ይናገራሉ፡፡

ባገባደድነው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የትምህርት ጥራትንና አግባብነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ስርዓቶች ለመዘርጋት ተሞክሯል፡፡ ይህም ችግሩን ለመቅረፍ በየተቋማቱ እየተሠራበት ያለው የአቻ ለአቻ (Peer learning) የመረዳዳት ትምህርት፣ በፕሮግራሞች ላይ እየተደረገ ያለው በሞጁል የማስማማት ሥራ ወይም ብቃት ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ (Modularization) እና በትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ ዙሪያ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች እንደ አበረታች ጅምር ሥራዎች ሊወሰዱ የሚገቡ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በቀጣይ ዓመታት ውስጥ

በተወሰኑ የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ የውጤት ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ለመተግበር ሥርዓተ ትምህርቶች በዚህ ዓይን እንዲቃኙ አቅጣጫ ተቀምጦ ሥራ ተጀምሯል፡፡ ስለሆነም የትምህርትን ብክነት ለመቀነስ የተጀመሩትን መልካም ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋሚት የሚታዩ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ችግሮች በግል ተቋማትም በበለጠ ጎልተው ይታያሉ፡፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትም የሚያፈሩት የሰለጠነ የሰው ሃይል በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፍ በመሆኑ ተገቢውን ብቃት ይዞ መውጣት ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆንም በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች እየተወሰዱ የሚገኙት የጥራት ማሻሻያ እርምጃዎች የግል ተቋማትንም ሊያቅፉ ይገባል፡፡

### 3.2.2. የትምህርት አግባብነት

መንግሥት በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ በፈጠረው ምቹ ሁኔታ የዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ በርካታ የትምህርት መርሀ ግብሮች መከፈታቸው ይታወቃል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግን እነዚህ የትምህርት መርሀ ግብሮች ሥርዓተ ትምህርቶች ከሃገራዊ ፍላጎት አንጻር ለማጣጣም የሚያስችል አስተማማኝ ሥርዓት እንዳልነበረ ግልጽ ነው፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በአገር አቀፍ ደረጃ የስርዓተ ትምህርት ለውጥና ትግበራ ስትራቴጂ ተቀርፆ (በ2000–2003 ዓ.ም)[2] አፈፃጸሙን የሚመራ ሃገራዊ ምክር ቤት ተቋቁሞ በተደረገው የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት ተቋማት በቡድንና በአገር አቀፍ ደረጃ ተወያይተውባቸው በሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጡ ፕሮግራሞች በውጤት ተኮር ሞዱላር ሥርዓት ተደራጅተው በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲስማሙ ተደርገዋል፡፡ በዚህ መልክ የተዘጋጁትን ፕሮግራሞች አንዳንድ የግል ተቋማትም እንዲተገብሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የፕሮግራሞችን አግባብነትና ጥራት ለማስጠበቅ እንደ አንድ ትልቅ መሳሪያ ሊያገለግል የሚችለው አገራዊ የትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍም ተዘጋጅቶ የማስተግበሪያ ደንብ ረቂቅ ሰነድ ዝግጅትም በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

የሰለጠነ የሰው ሃይል ልማት ከሃገር ልማት ፍላጎት አኳያ በመቃኘት በዕቅድ የመምራት ጉዳይ በመሆኑ በአገሪቱ ያሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሰው ሃይል ፍላጎቶችን ማወቅ ወሳኝ ስራ ይሆናል፡፡ ይህንን መረጃ እንደ ሀገር በማዕከል አሰባበስቦ የሚይዝና ተንትኖም ለተፈላጊው ሥራ ማቅረብ

[2] የከፍተኛ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ለውጥና ትግበራ ስትራቴጂ

የሚችል አካልም መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ትምህርት ሚኒስቴር ከየሴክተር መስሪያ ቤቱ ጠቋሚ መረጃ በመሰብሰብ አመላካች የሰው ሀይል ፍላጎት ለመዳሰስ ሞክሯል፡፡ ይህ ጠቋሚ ጥናት እንደ ጅምር እና አመላካች የዳሰሳ ጥናት ሊያገለግል የሚችል ቢሆንም በሂደት ግን በመረጃ አቅርቦት ረገድ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ተከታታይነት፣ ስፋትና ጥልቀት ያለው ተቋማዊ ሥርዓት በመገንባት አጠናክሮ መቀጠል የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

የመስሪያ ቤቶች የሰው ሃይል ፍላጎቶች እንደሚያመለክተው አሁን በተቋማት የሚሰጡ ፕሮግራሞች ላይ ጥናት ማድረግ እንደሚገባ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ይህም የሰለጠነ ሰው ሃይል ፍላጎት እጥረት ያለባቸውንና የሌለባቸውን መስኮች ለይቶ የትምህርት ፕሮግራሞች ለመክፈት ወይም ለመዝጋት የሚያስችል ዓይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጠቋሚ ጥናቱ ተፈላጊነት ባላቸው ፕሮግራሞች የሚመረቁ ምሩቃን በዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የሚፈለገውን አቅም መጨበጣቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት ለመዘርጋትም ይጠቅማል፡፡

በፍጥነትና በቀጣይነት በማደግ ላይ ያለውን የሀገራችን ኢኮኖሚ ለማሳለጥ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማዕከል ያደረገ የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ሃገራዊ አቅጣጫ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የ70፡30 የመስኮች ምጣኔ ቀመር ተዘጋጅቶ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ላይ የሚያተኩረው የስልጠና ስርዓት በቅልጥፍናና በጥራት ለማከናወን 10 የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች እና 2 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች ተቋቁመው ተማሪዎችን በሰፊው ተቀብለው በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሰረት በ2007 ዓ.ም በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተማሪዎች አጠቃላይ ድርሻ ከ70% ባይ ደርሷል፡፡ የደረሰ ሲሆን በዚሁ ዓመት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ከገቡት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ድርሻ ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ሲነጻጸር 73፡27 ደርሷል፡፡ ይህ ደግሞ የ70፡30 ቀመር ግብ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሳይጠናቀቅ እንደተሳካ ያሳያል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው የ2006 የበጀት ዓመት የትምህርት ስታትስቲክስ ስላለፉት አራት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንደሚያሳየው በተከታታይ በተሰራው ሥራ አጠቃላይ የተማሪዎች የመመረቅ ምጣኔ በእጅጉ እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ማብቂያ ላይ ሊደረስበት ከታሰበው የ93 በመቶ (90 በመቶ ለሴቶች እና 95 በመቶ ለወንዶች)[3] የመመረቅ ምጣኔ ማሳካት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ተቃርቧል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የኢኮኖሚ ልማታችን የሚፈልገው የሳይንስና

[3] የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ በ2006 የበጀት ዘመን የቀረበው ያለፉት አራት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ቴክኖሎጂ ተመራቂ ባለሙያዎችን በበቂ ደረጃ ለማፍራት የ70፡30ው ምጣኔ በመዝለቅ ወይም በምረቃም መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ትምህርት ሚኒስቴር ባደረገው ጠቋሚ ጥናት በቀጣይ ዓመታት ከሚፈለገው የሰው ሀይል መካከል ከ70% በላይ የሚሆኑት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች እንደሆነ ያሳያል፡፡ ወደ መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ግንባታ ለሚደረገው ሽግግር የኢንዱስትሪ ልማት ዋናው አቅጣጫ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶት መቀጠል እንዳለበት ያሳያል፡፡ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች ያለችው ቻይና ከ10 ተማሪዎች መካከል 4ቱ የኢንጅነሪንግ ትምህርት የሚከታተሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተቋሞቻችንና የትምህርት መርሀ ግብሮቻችን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት መስኮችን ያማከሉ ሆነው መቀጠል እንዳለባቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 3.2.3. የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማረጋገጫ ስርዓት

የትምህርት ጥራትንና አግባብነትን ማስጠበቅ ቁልፍ የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ በመሆኑ ለዚህ የሚያመች አደረጃጀትና አሰራር መዘርጋት አስፈላጊነቱን በመገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ (HERQA) እና የከፍተኛ ትምህርት ስትሬቴጂ ማዕከልን በአዋጅ 351/1995 ዓ.ም በማቋቋም ከፍተኛ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 ዓ.ም የእነዚህን ተቋማት ሃላፊነታቸውን በማስፋት እንደገና እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ ይህን ተከትሎ የትምህርትን ጥራት ለማሳደግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

የትምህርት ጥራትንና አግባብነትን ለማስጠበቅ የተዘረጉ ሥርዓቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመምከር የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ በውሳኔ ሰጪ አካላት እያስፀደቀ የሙከራ (Piloting) ሥራዎችን ሰርቶ በተገኘ ግብረ መልስ አዳብሮ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ በዚህም መሠረት በተቋማት ደረጃ የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማረጋገጥ በ10 ስታንዳርዶች (Quality focus areas) ማለትም ተልዕኮ፣ ራዕይና የትምህርት ግብ፣ በአደረጃጀትና የአስተዳደር ስርዓት፣ የመሰረተ ልማት እና የማስተማሪያ ሃብቶች፣ የአካዳሚክ እና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ምጣኔ፣ የተማሪዎች አቀባበል እና እገዛ/ድጋፍ ስርዓት፣ የፕሮግራም አግባብነት እና ስርዓተ ትምህርት፣ የመማር ፣ የማስተማር እና የግምገማ ስርዓት፣ የተማሪዎች ውጤታማነት የምሩቃን ፋይዳ፣ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት እና ውስጣዊ የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት መኖር ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት እያንዳንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የግል ግምገማ ሰነድ (Self Evaluation Document) በማዘጋጀት 55 የግልና የመንግስት የከፍተኛ ት/ት ተቋማት ተገምግመው ያላቸው

ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው ተቋማቱ በእያንዳንዱ ስታንዳርድ ሊያሻሽሉ የሚገባቸውን አበይት ጉዳዮች በመጥቀስ በዕቅድ በመያዝ ተቋማቱ በመስራት መንግሥት እና ቀጣሪ ድርጅቶች የሚፈልጓቸውን ብቃት ያላቸውን ምሩቃን እንዲያቀርቡ ከተቋማዊ ጥራት ኦዲት (Institutional Quality Audit) ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በተጨማሪ ተቋማቱ በሚሰጧቸው ፕሮግራሞች ደረጃ የProgram level Quality Audit ፕሮቶኮል ተዘጋጅቶ ተቋማት በት/ት ክፍል የሚሰጡት ጥራት እና አግባብነት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ስራ ከተሞከረ በኋላ /ሦስት/ ፕሮግራሞችን በመገምገም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለተቋማቱ ለማሰራጨት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ በ2007 ዓ.ም ከ20 በላይ የት/ት ፕሮግራሞች ግለ ግምገማ ሰነድ አዘጋጅተው በላኩት መሠረት የጥራት ኦዲት እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡

የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ሁሉንም የትምህርት ዘርፎች የሚያካትት አገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና የብቃት ማዕቀፍ ዝግጅትን ያገባደደ ሲሆን ትግበራ ለመጀመር የሚያስችል የማስተግበሪያ ደንብ አዘጋጅቶ በመንግስት ለማጸደቅ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ማዕቀፉን መሰረት በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ በዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጡ ፕሮግራሞች ሊኖራቸው የሚገባውን ደረጃ በማውጣት ከፕሮግራሞች ዝግጅት እስከ ማጠናቀቂያ ያለውን የብቃት መረጃ አሰጣጥ ባለው ሂደት ላይ ቁጥጥር በማድረግ ለሚሰጡ ብቃቶች ዕውቅና በመስጠት በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል አሰተባባሪነት በሚደራጀው የአስተዳደር መዋቅር እውቅና ተሰጥቷቸው በአገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ብቃት ማዕቀፍ የመረጃ ቋት ውስጥ እንዲመዘገቡ እንዲያደርግ ሃላፊነት ተሰጥቶታል[4]፡፡

እሰከ አሁን ድረስ በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲው በተለይ በግል ከፍተኛ ትምህርት ላይ ሲተገበሩ የቆዩት በርካታ የጥራት ማስጠበቂያ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ተግባራት በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም የተሻለ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ከኤጀንሲው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ከሞላ ጎደል ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን አቋቁመዋል፡፡ እነዚህ የጥራት ማረጋገጫ ማዕከላት አስፈላጊውን ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ የትምህርቱን ጥራት ማሳደግ እንዲችሉ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር ግን ብዙ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ ኤጀንሲው በሁሉም የመንግስትና የግል ተቋማት ላይ ተከታታይነት ያለው ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችለው አቅም ገንብቶና አሰራር ዘርግቶ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለፉት ጥቂት

[4] ENQF Draft Regulation 2014

ዓመታት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የእርስ በርስ ግምገማ ባህል ለማዳበር ያሳዩት ጅምር ስለ ተቋማዊ ጥራትና መለኪያዎቹ ክርክር እንዲጀመር ያደረጉት ጥረትም ትልቅ ቦታ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ የእርስ በርስ ግምገማው ዓላማ ግልፅ ቢሆንም በአካሄዱ ላይ ግን አስተማማኝ ሥርዓት በመገንባትና ከፍተኛ መግባባት በመፍጠር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

የጥራት ማረጋገጫ ስራዎችን ከተማሪዎች ግምገማ፣ ከስርዓተ-ትምህርት ቀረጻ፣ ከመምህራን ልማት (Teachers' Delopment) ስራዎችና ከመነሻ መረጣ (Benchmarking) ጋር አያይዞ ማየት ይገባል፡፡ እነዚህም ጥራት ያላቸው ምሩቃንን በብዛት ወደ ገበያው እንዲወጡ በማድረግ በሃገሪቱ ልማት ላይ የበኩላቸውን አሻራ በማኖር እድገታችንን ያፋጥናሉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ቀረጻና አሰጣጥ፣ የመምህራን አቅርቦትና ጥራት፣ የትምህርትና ምርምር መሰረተ ልማቶችን ማጠናከር ላይ የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያው የዕ.ትዕ. ሊደረሱ የተቀመጡ የአግባብነትና ጥራት ማረጋገጫ ግቦች አፈጻጸም አንጻር በክፍተት የታዩ ጉዳዮች ተግዳሮት ተወስደው በቀጣይ የዕ.ት.ዕ ዘመን ግብ ተጥሎባቸው በተሟላ መልኩ ለማከናወን መዘጋጀትን ይጠይቃል፡፡

## 3.3. የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት

### 3.3.1. የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ምንነት

የትምህርት ጥራትን ከማሳደግ አኳያ አለምአቀፋዊነት አንዱ መሳሪያ መሆኑን ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ምንም እንኳ በተለያዩ ሀገራት በተወሰነ ደረጃ የተለያየ ትርጉም ቢሰጠውም እንደ አጠቃላይ ግን ዓለም አቀፍ መስፈርቶችና የተለያየ ባህላዊና ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው ጉዳዮች ከተቋማቱ ግቦች እና ተግባራት (መማር ማስተማር፣ ምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት) ጋር የሚቀናጁበት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት በተቋማቱ የሚፈራው የሰው ሀይል በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ምርጥ ስታንዳርዶችንና መልካም ተሞክሮዎችን በማፈላለግና በመጠቀም እንዲሁም አካዳሚያዊ ትብብሮችን ማጎልበትን ያካትታል፡፡

ዓለም አቀፋዊነት ቃሉ በአሁኑ ግዜ ከግሎባላይዜሽን ጋር በአማራጭነት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለና አንዳንድ የመመሳሰል ሁኔታ ቢታይባቸውም በጽንሰ ሃሳብ ወይም በትርጉም ደረጃ ግን በመካከላቸው ልዩነት እንዳለ ጥናቶች ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህ መሰረት ግሎባላይዜሽን ማለት ከድንበር

ድንበር የሚደረግ የቴክኖሎጂ፣ የኢኮኖሚ፣ የእውቀት፣ የህዝብ፣ የእሴት፣ የሃሳብ ወዘተ ፍሰት ነው፡፡[5] ስለሆነም በሀገራት ታሪክ፣ ድርጊት፣ ባህልና ሀገራቱ ለራሳቸው በሚሰጡት ቀዳሚ ጉዳዮች ምክንያት በእያንዳንዱ ሀገር ላይ የተለያዩ ተጽዕኖዎችን ያሳድራል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት በአብዛኛው ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው ከትምህርት ጋር በተዛመደ ሁኔታ ሲሆን ከግሎባል አካዳሚክ ከባቢ ጋር ለመወዳደር በትምህርት ሥርዓት እና በተቋማት እንደዚሁም በግለሰቦች የሚተገበሩ ፖሊሲዎችና ድርጊቶችን ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፋዊነት የሚገለጸው ዩኒቨርሲቲዎች እና መንግስት ለግሎባላይዜሽን ምላሽ ለመስጠት የሚተገብሩት የተለያዩ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች እንደሆነ ነው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ዓለም አቀፋዊና ባህላዊ ይዘቶችን (ጉዳዮችን) ከማስተማር፣ ከምርምር እና ከተቋማት አገልግሎት ጋር የማቀናጀት ሂደት ነው፡፡ ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት አንድ ሀገር የራሱን ማንነትና ብሄራዊ ጥቅሙን ጠብቆና አክብሮ ለግሎባላይዜሽን ተጽዕኖ ምላሽ የሚሰጥበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ እሰከ አሁን ባለው ሁኔታ ግሎባላይዜሽንን እንደ መንስኤ (Catalyst) ዓለም አቀፋዊነትን ደግሞ እንድ ምላሽ አድርጎ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

ከዚህ አንጻር ከማይቋረጥ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምጥቀት ጋር ተያይዞ ግሎባላይዜሽንና የግሎባላይዜሽን ውጤቶች ሁሌም የሚኖሩ እና የ21ኛው ክፍለ ዘመን ፍሬዎች ይሆናሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የዩኒቨርሲቲዎች ዓለም አቀፋዊነትም ሊቀር የማይችል (inevitable) ክስተት ስለሆነና ወደ ፊት ዓለማችንን የተሻለች ምድር የሚያደርግ፣ ለሳይንስም የሰው ልጅ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሊገጥመው የሚችለው የተፈጥሮ ተግዳሮቶችንና ውስብሰብሰነትን በከፍተኛ ሁኔታ የመፍታት አቅምን የሚያጠናክር እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ስለሆነም ወደ ዓለም አቀፋዊነት ውስጥ መግባት የውዴታ ግደታ ይሆናል፡፡

### 3.3.3. የዓለም አቀፋዊነት ጥቅሞችና ስትራቴጂዎች

የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ለሀገር እና ለዩኒቨርሲቲዎች የሚያስገኛቸው በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በቅርቡ በ115 ሀገራት ውስጥ በ875 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ዓለም አቀፋዊነትን አስመልክቶ የተካሄደው የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው

---

[5] Akbar Zolfaghari, Mohammad Shatar Sabran, Ali Zolfaghari, (2009) Internationalization of higher education: Challenges, strategies, policies and programs. US-China Education Review, ISSN 1548-6613, USA, May 2009, Volume 6, No.5 (Serial No.54)

የተማሪዎችን የትምህርት ዝግጅት ለማሻሻል፣ ሥርዓተ ትምህርትን ዓለም አቀፋዊ ለማድረግ፣ የተቋማትን ዓለም አቀፋዊ ይዘት (Profile) ለማሳደግ፣ የምርምርና የእውቀት ልማትን ለማጠናከር፣ የዩኒቨርሲቲዎችን ፋካሊቲ እና ሠራተኞችን ብዝሃነት በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠ መሆኑን ነው፡፡[6]

ዓለም አቀፋዊነት የዩኒቨርሲቲዎች የጥራት ግብዓት መገለጫ እየሆነ የመጣበት ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የከፍተኛ ትምህርት አመራር ብቃትን ጭምር ለማሳደግና ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግ አንዳንድ ሀገራት (ለምሳሌ ደቡብ ኮሪያ) የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ የካበተ ልምድ ያላቸው ዓለም አቀፍ የአማካሪ ባለሙያዎች ቡድን የአመራርና አስተዳደር ቦርድ አባላትን እንዲደግፉ የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ፡ ስለዚህ እንደነዚህ ያሉ ልምዶች በዩኒቨርሲቲዎቻችንም ውስጥ ቢተገበሩ ጥቅሙ የጎላ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከሌሎች የመረጃ ምንጮች ለማየት እንደተቻለው ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በዓለም አቀፍ ከሚገኙ ልምዶች በመነሳት እንደየ ሀገሩ ተጨበጭ ሁኔታ ለባህል፣ ለማህበራዊና ኦኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያደርገው አስተዋጽዖ (Social responsiveness)፣ ለፖሊሲ ጉዳዮች፣ ለመንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ልማት ፕሮግራሞች ዕድገት፣ ከትምህርትና ተዛማጅ ጉዳዮች ክፍያ ጋር በተያየዘ እንደ አንድ የውጭ ምንዛሪ ማግኛ መንገድ ወይም ምንጭ እንደሚሆንና ለሀገር እና ለተቋማት ገጽታ ግንባታም ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል፡፡ በጥናቱ ከተጠቀሱት ጠቀሜታዎች መካከል  የተማሪዎችን ዓለም አቀፍ ግንዛቤ ለመጨመር፣ የምርምርና የእውቀት ልማትን ለማጠናከር እና ዓለም አቀፍ ትብብርና መረዳዳትን ማበረታታት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ወደ ከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ውስጥ ለመግባት አራት አቀራረቦች (Approaches) ይኖራሉ[7]፡፡ እነዚህም ተግባር/ድርጊት (Activity- የተማሪ እና መምህራን ወይም ፋካሊቲ ልውውጥን፣ ሥርዓተ ትምህርትን፣ የቴክንክ ድጋፍን ያካትታል)፣ ብቃት (Competency- በተማሪዎችና መምህራን ላይ የሚመጡ የአዳዲስ ዓለም አቀፍ እውቀቶች፣ ክህሎቶች፣ አስተሳሰቦችና እሴቶች እድገትን ያካትታል)፣ (Ethos- ባህል ወይም የሀገራት ፍልስፍና) እና ሂደት (Process- ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን፣ ተግባራትን፣ ወዘተ ከዓለም አቀፍ ሁኔታ ጋር ማቀናጀትን የሚያጠቃልል) ናቸው፡፡ ስለዚህ ዓለም አቀፋዊነት የፋኩሊቲን፣ የተማሪዎችን፣ የአስተዳዳሪዎችን እና ከፍ ብሎም የማህበረሰቡን ጨምሮ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ሚናና ድርጊትን የሚነካ፣

---

[6] International Association of Universities (IAU),(2010). The Third Global Survey Report on Internationalization of Higher Education.

[7] Özturgut, O., Cantu, M. P., Pereira, L. J., and Ramón, D. K.፣ 2014).Effective strategies in internationalization of higher education in the United States. International Journal of Research Studies in Education,2014 April, Volume 3 Number 2, 29-39

ሥርዓተ ትምህርትንና የምርምር ፕሮግራሞችን ሁሉ ያካተተ የተቀናጀ የለውጥ ሂደት ነው፡፡ ዓለም አቀፋዊነት አጀማመሩ በትብብር ላይ የሚመሰረት ሆኖ ቀስ በቀስ ግን ወደ ዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ የሚያስገባም ሂደት ነው፡፡

ወደ ከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ሊያስገቡ የሚችሉ ጠቅለል ያሉ አምስት ዋና ዋና ስትራቴጂዎች አሉ፡፡ እነዚህም፡- ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት መስጠት፣ ዓለም አቀፍ የምርምር ትስስሮችን በማጠናከር የምርምር ሥራዎችን ማሳደግ፣ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር ያለውን ትብብር ማሳደግ፣ ውስጣዊ ዓለም አቀፋዊነትን ለማበረታታት መሰረተ ልማትን ማሻሻል፣ የዓለም አቀፋዊነት የረጅም ጊዜ ዕቅድ ማዘጋጀት ናቸው፡፡[8]

ዓለም አቀፋዊነት እየተንሰራፋ በመምጣቱ አንዳንድ የዓለም ትላልቅ ስጋቶችና መነጋገሪያ እየሆኑ ካሉት ጉዳዩች መካከል የተማረ የሰው ሀይል (በተለይም ተመራማሪዎች፣ ሀኪሞችና መሀንዲሶች) በተማሩበት ውጭ ሀገር መቅረት ወይም ወደ ሌላ ሀገር መኮብለል (Brain drain) እና በባህል ላይ የሚያሳድረው ከፍተኛ ተጽዕኖ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ስለሆነም ይህንን እና መሰል ተጽዕኖዎችን በተጨባጭ ለመመከት በዚህ ዙሪያ ግብ በማስቀመጥ ትኩረት ሰጥቶ መሥራትም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 3.3.3. የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ያለበት ደረጃ

የዓለም አቀፋዊነት ተሳትፎ ከሚለኩባቸው በርካታ ጠቋሚዎች መካከል የዓለም አቀፍ ተማሪዎች ተሳትፎ፣ የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ፣ በውጭ ሀገር ካምፓስ መክፈት፣ ዓለም አቀፍ አጋርነት፣ ፍይናንስን፣ የሰው እና የቴክኖሎጂ ሀብቶችን ለዓለም አቀፋዊነት ሥራ ማዋል፣ የዩኒቨርሲቲ የግል ድርጅቶች አጋርነት፣ ፋካሊቲ ለዓለም አቀፋዊነት የሚያደርገው አስተዋጽዖ፣ ምርምር ለዓለም አቀፋዊነት የሚያደርገው አስተዋጽዖ፣ የዩኒቨርሲቲ ዓለም አቀፋዊነት የልማት ፕሮጀክቶች ያደረጉት አስተዋጽዖ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወቅት በዓለም አቀፋዊነት ዙሪያ መደረስ አለበት ተብሎ የተቀመጠ ግብና ለግቡ ማሳኪያ የተቀየሰ ስልት ባለመኖሩና ከመረጃ እጥረት ጋር ተያይዞ ሁኔታውን መገምገም አስቸጋሪ ቢሆንም በአገር ደረጃ የተቀመጡ መርሆዎችና ኃላፊነቶች አሉ፡፡

[8] Akbar Zolfaghari, Mohammad Shatar Sabran, Ali Zolfaghari, (2009) Internationalization of higher education: Challenges, strategies, policies and programs. US-China Education Review, ISSN 1548-6613, USA, May 2009, Volume 6, No.5 (Serial No.54)

የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ የከፍተኛ ትምህርት ከአገሪቱ አጠቃላይ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጋር የተጣጣመ፣ በአካሄዱም ከዓለም አቀፍ እውነታ ጋር እኩል የሚራመድ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል:: በተጨማሪም የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል በአገራዊ ተቋማት መካከል ትብብርን ያጎለብታል፣ የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮችን ከሚያከናውኑ ተመሳሳይ የውጭ አገር አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል የሚል ሃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም ተቋማቶቻችን ወደ ዓለም አቀፋዊነት ገብተው እንዲወዳደሩ የሚያስችል በአዋጅ የተደነገገ አቅጣጫ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎችም ያከናወኗቸው መልካም ጅምር ሥራዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ተቋማት ከውጪ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ፕሮግራሞችን መክፈት መጀመራቸው፣ ዓለም አቀፍ ልምዶችን ለመቅሰም እንዲያስችላቸው ዓለም አቀፍ የአካዳሚክና የምርምር ኮንፈረንሶችን ማዘጋጀታቸው፣ ሞጁላር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ እና በብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የተገኙ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችና ስራዎቹ ዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቁና ተወዳዳሪነትን በሚያረጋግጡበት ደረጃ መዘጋጀታቸው፣ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ከውጭ አገር ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚያደርጉት ትስስርና ትብብር እየጎለበተ መምጣቱ ዋና ዋና ስኬቶቻችን ናቸው፡፡ እ.ኤ.አ በ2011 የዓለም አቀፍ የትምህርት ኢንስቲትዩት ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ እርዳታ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የተዘጋጀው የከፍተኛ ትምህርት ኮንፈረንስ ሪፖርት እንደሚያሳየው ከሀገራችን ነባር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ብዙዎቹ ከተለያዩ የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር አጋርነት ለመፍጠር ጥረት አድርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህንና ሌሎች ተቋማት በተፈለገውና ቀጣይነት ባለው ደረጃ አጋርነትን ፈጥረው ከዓለም አቀፋዊ ግንኙነትና አጋርነት ማግኘት ያለባቸውን ፋይዳ በማግኘት ረገድ ትልቅ ክፍተት መኖሩ ተመልክቷል፡፡እንዲሁም አሁን ያለንበት ደረጃ ከሌሎች ተመሳሳይ የፖለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ከሚያራምዱ ሀገራት አንጻር ሲታይ ገና ብዙ መስራት ይጠበቅብናል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ደረጃ መለኪያዎች ከሆኑት ውስጥ የመምህራንና ተማሪዎች እንቅስቃሴ (Mobility) አንዱ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የተማሪዎች ዓለም አቀፋዊ ዝውውር ሲታይ በውጭ ሀገራት የከፍተኛ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ቁጥርና በሀገራችን ውስጥ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ የውጭ ዜጎች ቁጥር ከሌሎች ታዳጊ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር በእጅጉ ዝቅተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዓለም አቀፍ የትምህርት ልውውጥ ረገድ የዓለም አቀፍ የትምህርት ኢንስቲትዩት የ2012 ሪፖርት እንደሚያሳየው ኬንያ በ2010 ወደ

ተለያዩ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ የላከቻቸው ተማሪዎች ቁጥር በቅድመ ምረቃ 2145፣ በድህረ ምረቃ 1216 እና ዲግሪ ያልሆኑት 80፣ በድምሩ 3441 ሲሆኑ በዚሁ ወቅት ኢትዮጵያ ደግሞ በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም 678፣ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም 497 እንደዚሁም ዲግሪ ባልሆኑ ፕሮግራሞች ደግሞ 37 ተማሪዎች ሲሆኑ በጠቅላላ 1212 ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ሀገራት የውጪ ተማሪዎችን ሊስቡ የሚችሉ ተፈላጊ ፕሮግራሞችን በመክፈት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነታቸውን በማረጋገጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አኳያ የውጪ ተማሪዎችን በመሳብ ረገድ (Inbound mobility rate or Inbound mobility) ለምሳሌ ቻይና 0.27306፣ የደቡብ ኮሪያ ሪፐብሊክ 1.77178፣ ጀርመን 7.04163፣ አውስትራሊያ 18.29552፣ ታይላንድ 0.8356፣ ህንድ 0.11034፣ ኔዘርላንድስ 7.24589፣ የዓለም 2.03422 እና የኢትዮጵያ ደግሞ ከቁጥር የማይገባ መጠን እንደሆነ UIS እ፣ኤ.አ በ2012 ያወጣው መረጃ ያሳያል፡፡

የአካዳሚክ መምህራን ልውውጥንም በሚመለከት ማሌዥያ 6684 ዓለም አቀፍ መምህራንን ወደ ሀገሯ አስገብታ በማሰራት ላይ ትገኛለች፡፡ በተጨማሪም እ.ኤ.አ በ2020 በምርምር ዩኒቨርሲቲዎቿ ውስጥ ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል 15% ዓለም አቀፍ መምህራን እንዲሆኑ በሰፊው አቅዳለች፡፡ በትምህርት ደረጃቸው፣ ባበረከቱት ዓለም አቀፍ አካዳሚክ አስተዋጽዖ እና ባላቸው መልካም ዝና ወደ ሀገራችን ገብተው በማስተማር ላይ ያሉ የውጭ መምህራን ቁጥር ከዚህ ጋር ስናነጻጽር እጅግ በጣም ዝቅተኛ (የ2006 ዓ.ም ስታትስቲካዊ መረጃ 7.6% ብቻ እንደሆኑ ያሳያል) ሆኖ እናገኛለን፡፡ እነዚህ በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚያስተምሩ የውጭ መምህራን አመጣጥ በዋናነት ከጥራት ጋር የተያያዘ ሳይሆን የመምህራን አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ስለዚህ ጥራትንና የልህቀት ግንባታን ያማከለ የውጭ መምህራን ድርሻን ማሳደግ ትኩረት የሚሻ ይሆናል፡፡

በቻይና ከአንዳንድ ሀገራት ልምድ በተለየ ሁኔታ እያንዳንዱ የቻይና ዩኒቨርሲቲዎች የዓለም አቀፋዊነት ልማት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ፣ የዓለም አቀፍ ጉዳይ መከታተያ ጽ/ቤቶች እንዲከፍቱ፣ ለዚህ ሥራ ብቻ የሚውል ዓመታዊ በጀት እንዲመደብላቸው እና እያንዳንዳቸው በውጭ ሀገር የምሩቃን ማህበር እንዲኖራቸው አድርጋለች፡፡ ለዚህም ለእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ በአማካይ 8 ሚሊየን ዩዋን ድረስ ገንዘብ እየመደበች ትገኛለች፡፡ በተጨማሪም የቻይና የውጭ ሀገር ትብብር ትምህርት በማቋቋም እና ዓመታዊ የቻይና ዓለም አቀፍ የትምህርት ኮንፈረንስንም በማዘጋጀት በየዓመቱ እስከ 500 የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ለፖሊሲ ግብዓቶች፣

ለአካዳሚክ እና መረጃ ልውውጥ፣ ለትስስርና ፕሮግራሞች ቀረጻ እየተጠቀመች ተሳትፏን እያጠናከረች ትገኛለች፡፡

የሃገራችን ከፍተኛ ትምህርት ዘርፉን ዓለም አቀፋዊነት ለማረጋገጥ በአገራችን ውስጥ ከተከናወኑ ጉልህ ተግባራት መካከል አንዱ ሥርዓተ-ትምህርቶችን የማስማማት እና የሞዱላር ሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ ላይ የተሠሩ ሥራዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ 165 የቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞችን የማስማማት ሥራ ተከናውኗል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሥርዓተ ትምህርቶች ዝግጅት ወጥነት እንዲኖረው ማድረግ ብቻ ሳይሆን የአውሮፓ የHigher Education Era እና የBologna Process ሂደቶች ያመጧቸውን እንደ Outcomes Based Learning and Assessment እና የአውሮፓዊያን Credit Accumulation and Transfer System ጽንሰ ሃሳብ በመተግበር የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊ ይዘቱን የጠበቀ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ዙሪያ በ2006 ዓ.ም ማዕከሉ ያካሄደው የዳሰሳ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው ተቋማቱ በተለያየ የትግበራ ደረጃ ላይ እንዳሉ ታውቋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ዕውቅና አሰጣጥና የጥራት ማረጋገጥ ሂደት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸው የጥራት ማረጋገጫ መርሆዎችና ስታንዳርዶች ጋር ለማጣጣም ከውጭ አገር የሚገኙና በአገር ውስጥ ካምፓሶችን እና ኮሌጆችን የሚከፍቱ ተቋማትን ጥራት ማረጋገጫ መመሪያ ጨምሮ ሌሎች በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ ኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርትን ዓለም አቀፋዊነት ለማጎልበት በበርካታ አገራት በመተግበር ላይ ያሉ እንደ Tuning Africa መርሃ ግብሮች ላይ በተወሰኑ ተቋማት አማካኝነት እየተሳተፈች ሲሆን ከተወሰኑ አገራት ጋር በመተባበር ሥርዓተ ትምህርቶችን ወደ አገር ውስጥ በማምጣት በፕሮጀክት ደረጃ እንዲተገበሩ የተደረገበት ሁኔታም አለ፡፡ በተጨማሪም በቅርቡ በአፍሪካ ሀገራት ደረጃ የጋራ የከፍተኛ ትምህርት የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ተግባራዊ ለማድረግ Arusia Conventionን በአባልነት ፈርማለች፡፡

ከአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ-ትምህርቶች ቀረፃና ትግበራ፣ ጥራትና አግባብነት ከማሻሻል ጋር ተያይዞ፤ በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም ከ143 በላይ የሚሆኑ አገራት የአገር አቀፍ የትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍን በማዘጋጀት፣ በመተግበር፣ አሊያም ለማዘጋጀት ዕቅድ ይዘው በተለያየ ደረጃ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ በዋናነት የአገራችን የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ከጥራት፣ አግባብነት፣ ፍትሃዊነት እና ተደራሽነት አንጻር ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይታመናል፡፡ የኢትዮጵያ አገር አቀፍ የትምህርትና ሥልጠና ብቃት

ማረጋገጫ ማዕቀፍ ጽንሰ ሃሳቡን የማዳበሩ ተግባር ተገባዶ ማዕቀፉን ለማስተግበር የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቷል፤ በቅርብ ጊዜም ጸድቆ እንደሚወጣ ይጠበቃል፡፡ የማዕቀፉ ተግባራዊ መሆን በርካታ አገራት የሚግባቡበት ቋንቋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፤ የተማሪዎችን ዓለም አቀፋዊነትና ዝውውርን በማሳደግ ረገድም ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በሁለተኛ የዕ.ትዕ. ዘመን ትኩረት ተሰጥቶት በግብ ደረጃ ሊያዝ ይገባል፡፡

የዓለም አቀፋዊነት መለኪያ ከሆኑት መካከል አንዱ በውጭ ሀገር ካምፓስ ከፍቶ ማስተማር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ እያደረገች ያለችው እንቅስቃሴ በመረጃ አስደግፎ መናገር ባይቻልም አመርቂ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ብዙዎቹ ተቋማቶቻችን የዓለም አቀፋዊነት ተጠቃሚ ለመሆን ውጭ ሀገር ካምፓሶችን ሲከፍቱም ሆነ ተመሳሳይ የውጭ ተቋማትም በሀገራችን ውስጥ ገብተው ካምፓሶችን ከፍተው ሲሰሩ እምብዛም አይታይም፡፡ ለማሳያ ያክል የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ከሚገኙ ተቋማት መካከል ጥቂቶቹ በደቡብ ሱዳንና በሱማሌ ላንድ ቅርንጫፍ ካምፓሶችን በመክፈት አበረታች ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ እንደዚሁም ከውጭም እንደ ደቡብ አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ (UNISA) ያሉ ድንበር ተሻጋሪ ዩኒቨርሲቲዎች በሀገራችን ቅርንጫፍ ከፍተው በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ከባቢያዊ ቅንጅት ለማዳበር የሚያስችልና በቀጣይ ዓለም አቀፋዊነትን ለማሳደግ የሚያስችል ጅምር ስለሆነ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ከዚህም አኳያ የመንግስት ተቋማት በጎረቤት አገሮች በቅርብ ግዜ ቅርንጫፍ ለመክፈት ሊያስቸግር ቢችልም በድንበር አካባቢ የሚገኙ ዩኒቨርስቲዎችን በማጠናከር የጎረቤት አገሮች ተማሪዎችን መሳብ ይቻላል፡፡

በሌላም በኩል የሌሎች ሀገራትን ልምድ ስንመለከት ግን ለምሳሌ ማሌዥያ አምስት ታዋቂ የውጭ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች በሀገሯ ውስጥ ካምፓስ እንዲከፍቱ አድርጋለች፡፡ ስለዚህ ይህ ዓይነቱ የዓለም አቀፋዊነት ስትራቴጂ ለአካዳሚክ ልውውጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያደረግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከዚህ ማግኘት የሚገባንን ጥቅም እንድናገኝ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሀገራችን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በራሳቸው ጥረት እያደረጉ ያሉ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጥራት ደረጃ አውጪ ድርጅቶች

ተገምግመው ያሉበትን ደረጃ የሚያውቁበት ጠንካራ ስርዓት አልተዘረጋም፡፡ ከዚህ አንጻር ዓለም አቀፍ ትስስሮችን ለማጎልበት አቅጣጫዎችን ቀርጾ መተግበር ያስፈልጋል፡፡
በመሆኑም የሚከተሉት ተግዳሮቶች በቀጣይ ሊፈቱ እንደሚገቡ በማመን በዚህ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

ዓለም አቀፋዊነት የአገራችንን ከፍተኛ ትምህርት ጥራት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው ተብራርቷል፡፡ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወቅት ከሌሎቹ አንጻር ሲታይ ለከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ ግብም ሆነ ስልት ሳይቀመጥለት ቀርቷል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎቻችን በሚጠበቅባቸው ደረጃ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ሁለ ገብ ተሳትፎ ለማድረግ በዓላማና በዕቅድ እየተንቀሳቀሱ ነበር ማለት ያስቸግራል፡፡ የተቋማቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ያላቸው ብቃትና ዝንባሌ እንደዚሁም በዓለም አቀፋዊነት ላይ ያላቸው አጠቃላይ ግንዛቤም አነሶ ይታያል፡፡ ከዚህ ጋር ተያያዞ ዩኒቨርሲቲዎች በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጥራት ደረጃ አውጪ ድርጅቶች በግልፅ ተገምግመው ያሉበትን ደረጃ የሚያውቁበት ሀገራዊ ስርዓትም አልተዘረጋም፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚንቀሳቀሱ ተቋማት ጋር በትምህርትና ሥልጠና እና በምርምር ዙሪያ ጠንካራ አጋርነት በመመስረት አቅማቸው የሚያድግበት ሁኔታ በበቂ ደረጃ አለመፈጠሩና የትምህርት ጥራቱ የውጪ ተማሪዎችን ለመሳብ ያለው አቅም ዝቅተኛ መሆን ዋና ዋና እጥረቶች ናቸው፡፡

በዚህም ምክንያት ተቋማቶቻችንና ከፍ ብሎም ሀገሪቷ ከከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ማግኘት የሚገባቸውን ቀደም ሲል የተዘረዘሩት ጥቅሞችና ዘርፈ ብዙ ግብዓቶችን በበቂ ደረጃ ማግኘት ሳይችሉ ቀርተዋል ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለመፈጸም የተቀመጡ ግቦችንና ለግቦቹ ማሳኪያ የተለዩ ስልቶችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በታቀደው ደረጃ እንዳይፈጸሙ የበኩሉን አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ይታመናል፡፡ ለምሳሌ ከተማሪዎች እና መምህራን ልውውጥ የሚገኘውን የትምህርት ተደራሽነት፣ አግባብነት፣ ጥራትና ፍትሃዊነትን ለመጨመር ይደረግ የነበረውን ጥረት፣ የመምህራን ልማታችንን ለማሳደግ የተጣሉትን ግቦች ስኬታማነታቸውን እና ውጤታቸውን ይገድባል፡፡ ተመራማሪ መምህራኖቻችን ከዓለም አቀፍ ተመራማሪዎች ጋር የሚሳተፉበት ለሀገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው የምርምር እና የቴክኖሎጂ ማመንጨት፣ ማላመድና ማሸጋገር ሥራዎች፣ ከተማሪዎች ሊገኝ የሚችለው ገቢ (የውጭ ምንዛሪ)፣ በርካታ ተማሪዎቻችን፣ መምህራኖቻችንና የዩኒቨርሲቲ አመራሮቻችን ሊኖራቸው የሚገባ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በዚህ ምክንያት በሚጠበቀው ደረጃ ሳንጠቀም ቀርተናል፡፡ በአጠቃላይ ለፖሊሲዎቻችንና ለልማት

ፕሮግራሞቻችን መሻሻልና መሳካት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ እውቀቶችንና ልምዶችን በሚገባ ሳንቀስም የዕቅድ ዘመኑ ተጠናቋል ማለት ይቻላል፡፡

ስለዚህ በቀጣይ የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች የውጭ ተማሪዎችን የሚስቡ ተፈላጊ ፕሮግራሞችን በመክፈት ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት እና በዓለም አቀፍ ትምህርት ነክ መድረኮች ላይ ዘርፈ ብዙ ተሳትፎ በማድረግ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፉ እውቅና እንዲያገኝና እንዲተገበር የማቀላጠፍና የማስተዋወቅ፣ ከትምህርት ጋር በተያያዘ የተማሪዎችና የአካዳሚክ ሠራተኞች ወደ ውጪና ወደ ውስጥ የሚደረገው እንቅስቃሴ፣ በትብብር በሚሰሩ ምርምሮች እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራት እንደዚሁም የእውቀት ማጎልበቻ መርሀ ግበሮች ዙሪያ መሠረታዊና ተጨባጭ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት የፕሮግራሞች ማስማማት ሥራዎችን በመስራትና በሌሎችም እንደ ዓለም አቀፍ የምርምርና ትምህርት ኮንፈረንሶች ላይ በንቃት በመሳተፍና ተመሳሳይ ኮንፈረንሶችን በማዘጋጀት የውጭ ዩኚቨርሲቲዎችን በማሳተፍ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ተወዳዳሪነታቸውን በመጨመር መልካም ገጽታቸውን መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩ ተግባራት እንደ ስትራቴጂ አካል ተወስደው ወደ ዓለም አቀፋዊነት ህብረት እንዲያስገቧቸው መንግስት ለተቋማቱ ስትራቴጂያዊ ዓላማ ማስፈጸሚያ በቂ በጀት መመደብ ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን እንደ ሌሎቹ ጉዳዮች ሁሉ ለከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፋዊነት ግብ ተቀርጾለት፣ አቅጣጫ ተለይቶለትና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ሊቀመጡለት ይገባል፡፡

## 3.4. የመምህራን ልማት

መምህራን በአንድ ሀገር የትምህርት እድገት ላይ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ክህሎትና እውቀት ያላቸው ዜጎችን የሚያፈራ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ እነዚህ ለሀገር እድገት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ዜጎች በተፈላጊው እውቀትና ክህሎት ታንጸው እንዲወጡ መምህራን የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የመምህራን አቅምና አቅርቦት በጎለበተ ቁጥር፤ እንዲሁም መምህራን ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ባስተማሩ ቁጥር ብቃትና ክህሎት ያላቸው ተመራቂዎች እንዲወጡ በማድረግ ለሀገር እድገት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ያስችላቸዋል፡፡ ስለዚህም መምህራን በየጊዜው እውቀትና ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው ይጠበቃል፡፡

መምህራን የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ለሀገር እድገትና ብልጽግና ከፍተኛ ድርሻ የሚያበረክቱ ከመሆናቸውም በላይ በጥናትና ምርምር በመሳተፍ ለህብረተሰቡ ችግር ፈቺም በመሆን ትልቅ ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች ተሳትፎ፣ ፍትሐዊነት፣ ምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የትምህርት ጥራት፣ ዓለም አቀፋዊነት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ውጤታማ ለማድረግ የመምህራን በተፈላጊው ጥራትና መጠን መገኘት አስፈላጊውና ዋነኛው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በሀገራችን መምህራንን በየጊዜው ማሰልጠንና ከቴክኖሎጂ ጋር ማስተዋወቅ አስፈላጊነቱ ታምኖበት መምህራንን የማልማት ሥራ በዕቅድ ተይዞ በስፋት እየተሠራ ይገኛል፡፡ ይህንን ባገናዘበ መልኩ መምህራንን የማልማት ስራ በአንድ ወቅት ብቻ ተሰርቶ የሚያበቃ ስላልሆነ በተከታታይ ሊሰራበት የሚገባ ዓብይ ጉዳይ ይሆናል፡፡

መምህራን በመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ካላቸው የሙያ ሚና ባሻገር የተቋማት አመራር ግንባታ ምንጭ በመሆናቸው የከፍተኛ ትምህርት ቁልፍ ምሰሶዎች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት የከፍተኛ ትምህርት ተልዕኮዎችን ለማሳካት ሲታሰብ የመምህራን አቅርቦትና ጥራት ልዩ ትኩረት የሚሻ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

የመጀመሪያው የዕ.ት.ዕ በትምህርት ዘርፍ ውስጥ የትኩረት አቅጣጫ ሲያስቀምጥ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ዋነኛው ትኩረት ነበር፡፡ በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ዋነኛ የትምህርት ጥራትና አግባብነት ማረጋገጥ ነበር፡፡ ይህም ትኩረት የመምህራን ልማትን አንዷ አንድ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ታሳቢ አድርጓል፡፡ ስለሆነም እቅዱ ሁለንተናዊ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ልማትን በመተግበር ብቁ የመምህራን አቅርቦት እንደሚረጋገጥ ያወሳል፡፡ በዚህ የትኩረት መስክ ስር በቂ የመምህራን አቅርቦት እና የሚቀርቡትም መምህራን ብቁ ሆነው እንዲወጡ ዋነኛው ስራችን እንደነበረ ያስቀምጣል፡፡ ይህንን የትኩረት አቅጣጫ እውን ለማድረግም ሶስት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠው ነበር፡፡

### 3.4.1. የመምህራን አቅርቦት

የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት በተመለከተ የቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ፕሮግራሞቻችን ጥራታቸውን ጠብቀው ለማስፋፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የመምህራን ልማት በ1ኛው የእትእ ዘመን ልዩ ትኩረት የተሰጠው ግብዓት ነበር፡፡ በከፍተኛ ትምህርት

መምህራን ልማት ላይ የመጀመሪያው ግብ የመምህራን አቅርቦት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በየዓመቱ እየጨመረ የሚመጣውን የቅበላ መጠን ሊያስተናግድ የሚችል በቂ ቁጥር ያለው መምህራን ማቅረብ በመጀመሪያው ዕ.ት.ዕ አንዱ ግብ ሲሆን ግቡ የመምህራ ቁጥርን በ2007 ዓ.ም 23000 እንደሚደርስ አስቀምጧል፡፡  ይህ የመምህራን ልማት ስራችን ዓለማቀፋዊ ስታንዳርድ ታሳቢ ያደረገና በሂደትም ያንኑ ማሟላት በሚያስቸል መልኩ በመጀመሪያው የዕ.ት.ዕ. ማጠናቀቂያ ወቅት ለሚኖሩን 467,445 ተማሪዎች  በ 1 ለ 19 ጥምርታ 23,000 ገደማ መምህራን እንዲኖሩን ግብ ተጥሎ ነበር፡፡ በአምስት ዓመታት የዕቅዱ የትግበራ ዘመንም በ2002 ዓ.ም 15707 የነበረውን የመምህራን ብዛት በ2006 ዓ.ም ወደ 21467 ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ ይህም ማለት ከግቡ አንጻር 1252 ተጨማሪ መምህራን ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይህም የሚያሳየው ትግበራው በተያዘለት አቅጣጫ መሰረት እየተሰራበት የነበረ መሆኑን የሚመለክት ነው፡፡

የ2006 ዓ.ም መረጃ እንደሚያሳየው አጠቃላይ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት መምህራን ብዛት 21467 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 1,848 (7.6%) የሚሆኑት የውጭ ሀገር ዜጎች ናቸው፡፡ በግሉ ዘርፍ ያሉት የመምህራን ብዛት ደግሞ 2051 ይሆናሉ፡፡ ስለሆነም በአጠቃላይ በ2006 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ብዛት 24,252 ደርሷል፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ የመንግስት ዩኒቨርስቲ መምህራን በግሉ ዘርፍም እያስተማሩ እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ የአጠቃላይ የመምህራን ብዛት ከትክክለኛው በተወሰነ ደረጃ ዝቅ ሊል እንደሚችል ይገመታል፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው በመደበኛ መርሃ ግብር 335,078 በተከታታይ ደግሞ 258,493 በአጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት 593,571 ደርሷል፡፡ የመምህር እና ተማሪዎች ጥምርታ ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ይህ ቁጥር የመምህራን ተማሪዎች ጥምርታውን 1:28 ያደርገዋል፡፡ ከዓለም አቀፍ ስታንዳርድ አኳያ (1:19) ጥምርታው ዝቅተኛ በመሆኑ የመምህራን አቅርቦቱን መጨመር ያስፈልጋል፡፡ በ2006 ዓ.ም ያለው የመምህራን ብዛት ከመደበኛ ተማሪዎች ቁጥር አንጻር ስናየው ግን ጥምርታው 1:16 ያህል ብቻ ይሆናል፡፡ የሀገር ውስጥ መምህራንና የመደበኛ ተማሪዎች ጥምርታ ደግሞ ይጨምራል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥምርታ የአንደኛ ዲግሪ ያላቸው እንዲሁም በትምህርት ላይ ያሉትን መምህራን ጨምሮ የተሰላ በመሆኑ የመምህራን አቅርቦቱን ከፍ ያለ እንዲመስል አድርጎታል፡፡ በስራ ላይ ያሉትን መምህራን ብቻ ታሳቢ ካደረገ ግን የመምህራን እና ተማሪዎች ጥምርታው ከተገለጸው ምጣኔ በታች ይሆናል፡፡  ስለዚህ ባለው የመምህራን ብዛት የተማሪዎች ተሳትፎ ለማሳደግ ዕድል ሰጥቷል፡፡

ሠንጠረዥ.6 የተማሪ መምህር ጥምርታ (ምጣኔ)

| ብዛት | 2002 ዓ.ም | 2003 ዓ.ም | 2004 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | ጭማሪ በመቶኛ (ከ2002-2006 ዓ.ም) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪዎች ተሳትፎ | 420,387 | 447,693 | 494,110 | 553,848 | 593,574 | 41.2% |
| የመምህራን ብዛት | 15,707 | 17,402 | 20,822 | 23,905 | 24,252 | 54.4% |
| የተማሪ መምህር ምጣኔ | 1:27 | 1:26 | 1:24 | 1:24 | 1፡25 | |

ምንጭ፡ Education Statistics Annual Abstract 2006 E.C, MoE

ከመምህራን አቅርቦት አኳያ ሌላው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ የሴት መምህራን ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑ ነው፡፡ የሴት መምህራን ድርሻ በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 11.4% በ2006 ዓ.ም ወደ 11.7% ያደገ ቢሆንም በ4ኛው ትምህርት ሴክተር ልማት ዕቅድ መገባደጃ ወደ 20% ለማድረስ ከተጣለው ግብ አኳያ ክፍተት መኖሩን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የሴት መምህራን ተሳትፎ ድርሻን ለማሳደግ ከፍተኛ ግብ አስቀምጦ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

የዩኒቨርሲቲዎቻችን ዓመታዊ የተማሪ ቅበላ አቅም በከፍተኛ ሁኔታ በማደጉ እና ከአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ፍላጎት ጋር ተዳምሮ የመምህራን አቅርቦት ፍላጎትን ጨምሮታል፡፡ ለወደፊቱም ወደ ዩኒቨርሲቲ ሊገቡ የሚችሉ የተማሪዎች ቁጥር ሲያድግ የመምህራን ፍላጎትም በየዓመቱ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምንም እንኳ መንግስት በቅርቡ ለመምህራን ያደረገው የደመወዝ ማሻሻያ ብዙ መምህራንን በማስተማር ስራ ላይ እንዲያተኩሩና ተረጋግተው እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ስራቸውን ሊለቁ የሚችሉ መምህራን ሊኖሩ ስለሚችሉ በ2012 ዓ.ም ከሚያስፈልገው 33,970 ጠቅላላ መምህራን በተጨማሪ የእያንዳንዱን የትምህርት መስክ ታሳቢ ያደረገ 5% የመምህራን ቁጥር በመጠባበቂያ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ተጨማሪ 1698 መምህራንን በማሰልጠን በጠቅላላው 35,668 መምህራን እንዲኖሩን ታሳቢ አድርጎ ማልማት ያስፈልጋል፡፡

በአገራችን የተማሪዎች ተሳትፎና የዩኒቨርስቲዎች ቁጥር ከማደጉ ጋር ተያይዞ ያጋጠመውን የአግር ውስጥ መምህራን እጥረት ለመፍታት በርካታ የውጭ አገር መምህራን በጊዜያዊነት ተቀጥረው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የውጭ ሀገር መምህራን

ተሳትፎ ዕድገት በማሳየቱ በ2006 ዓ.ም የውጭ አገር መምህራን በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውጭ ዜጎች ብዛት በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 978 በ2006 ዓ.ም ወደ 1848 ከፍ ያለ ሲሆን ይህም የ88.9% እድገት አሳይቷል፡፡ የሀገር ውስጥ መምህራን ብዛት ግን በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 13074 በ2006 ዓ.ም ወደ 19797ያደገ ሲሆን ጭማሬው በመቶኛ ሲሰላ 52.1% ደርሷል፡፡ በመሆኑም መንግስት የውጭ ሀገር መምህራን በሰፊው ወደ ሀገራችን እየገቡ በትምህርት ስርዓቱ ላይ ትልቅ ለውጥ እንዲያመጡ የሚያደርገው ጥረት ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የመምህራን አቅርቦቱ ላይ የወንድ መምህራን ብዛት ከ2002 ዓ.ም ከነበረው በ53.8% ያደገ ሲሆን የሴት መምህራን ቁጥር ደግሞ በተጠቀሰው ጊዜ በ58.7% እድገት አሳይቷል፡፡ ይህም የሴት መምህራን ተሳትፎን በመጨመር ዙሪያ የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም ከወንድ መምህራን በበለጠ ጭማሬ የተሻለ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚሁም ኢትዮጵዊያን ምሁራን ከሥራቸው ጋር ግንኙት ባለው መልክ ወደ ውጪ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች ሄደው ልምድ የሚቀስሙበትና የሚቆዩበት ሁኔታ ውስን ልምዶች ቢኖሩም በተቀናጀ መንገድ እየተሰራበት አይደለም፡፡ ስለዚህ የመምህራን ልውውጥ እንደ ሥርዓት በሀገራችን ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በተጠናከረ ደረጃ ላይ አይገኝም፡፡ ተሳትፎ ከአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ቁጥር አንጻር ሲታይ 7.6% ደርሷል፡፡

**ሠንጠረዥ 7፡-የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር መምህራን ብዛት**

| ዓ.ም | ኢትዮጵያውያን | | | | የውጭ ዜጎች | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | የሴቶች ድርሻ በመቶኛ | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 2002 | 13,074 | 1,652 | 11.22 | 14,729 | 842 | 138 | 978 | 13,917 | 1,790 | 15,707 |
| 2003 | 15,267 | 1,481 | 8.84 | 16,748 | 531 | 123 | 654 | 15,798 | 1,604 | 17,402 |
| 2004 | 18,217 | 1,855 | 9.24 | 20,072 | 616 | 135 | 750 | 18,832 | 1,990 | 20,822 |
| 2005 | 19,838 | 2,283 | 10.32 | 22,121 | 1,648 | 246 | 1,884 | 21,376 | 2,529 | 23,905 |
| 2006 | 19,797 | 2,607 | 11.64 | 22,404 | 1,614 | 234 | 1,848 | 21,411 | 2,841 | 24,252 |
| ጭማሪ 2002-2006 ዓ.ም | 6,723 (51.4%) | 955 (57.8%) | | 7,675 (52.1%) | 772 (91.7%) | 96 (69.5%) | 870 (88.9%) | 7,494 (53.8%) | 1,051 (58.7%) | 8,545 (54.4%) |

ምንጭ፡- *Education Statistics Annual Abstract 2006 E.C*, MoE

የተሳትፎው ዓላማ የመምህራን ልውውጥን እሳቤ ያደረገ ሳይሆን ጊዜያዊ የአገር ውስጥ መምህራን እጥረትን ለማቃለል ስለሆነ በሂደት ልህቀትን መፍጠር ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሲገነቡ ፍትሐዊ ስርጭትን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚከናወን ስለሆነ ሁሉም የሀገራችን ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በየአካባቢያቸው የትምህርቱ እድል ባለመኖሩ ምክንያት ሳይማሩ የቆዩ ዜጎችን ተሳትፎ ለማሳደግ አይነተኛ አማራጭ ነው፡፡ ይህም ትምህርታቸውን በመደበኛ መርሀ ግብር መማር ለማይችሉ ዜጎች በክረምት፤ በማታና በርቀት ሊማሩ የሚችሉበትን ሁኔታ ያሰፋላቸዋል፡፡ በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች በፍትሐዊነት እየተስፋፉ ሲሆን በነዚህ ተቋማት የሚማሩት ዜጎች ቁጥርም እንዲሁ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል፡፡ በመደበኛ ፕሮግራም የሚመደቡ ተማሪዎችም በሁሉም የሀገራችን ክፍል ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች ገብተው የሚማሩ ሲሆን የምደባ ስርዓቱም ብዝሀነትን ያማከለ አሰራርን የተከተለ ነው፡፡ ስለሆነም ከየትኛውም የሀገራችን ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች በምርጫቸውና ባስመዘገቡት ውጤት መሰረት ብዝሀነትን ጠብቆ በእኩል እድል ተጠቃሚነት ይመደባሉ፡፡

በመምህራን በኩልም በመንግስት ወጪ (ስፖንሰርነት) የሁለተኛ ዲግሪ ተምረው የሚመረቁ መምህራን ሲመደቡ በፍትሐዊነት በሁሉም ተቋማት እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡ ይህም ብዙሐነት ተጠብቆ መምህራን በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ተመድበው እንዲሰሩ አስችሏቸዋል፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ መምህራን ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ተዛውረው ለመስራት ያላቸውን ፍላጎት ያሳያሉ፡፡ በቤተሰብና በሌሎች ግላዊ ምክንያት ዝውውር የሚጠይቁ መምህራን እንዳሉ ሁሉ በአላስፈላጊና ብዝሐነትን በሚቃረን መልኩ በዝውውር ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ሄደው ለመስራት ፍላጎት ያላቸው መምህራን ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የሚመደቡ የትምህርት አመራሮች በትውልድ አካባቢያቸው የሚመደቡ ሲሆን መምህራንም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለውን የግል ፍላጎታቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በተለያየ ደረጃ ያሉት ሌሎች የመካከለኛና ዝቅተኛ አመራሮችም ቢሆኑ በአብዛኛው የአካባቢው ተወላጅ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ መምህራን በትውልድ አካባቢያቸው ማስተማርን ይመርጣሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የመምህራን ብዝሐነት ስብጥርን ሊቀይረው ስለሚችል ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ከመርህ አንጻር ታይተው ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

### 3.4.2. የመምህራን ጥራት

በመጀመሪያው እትእ ያስቀመጥነው ግብ የመምህራንን አቅርቦት ለማሻሻል ብቻ ሳይሆን ጥራታቸውን ማሳደግ ላይም ያተኮረ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት የአንደኛ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ድግሪ ያላቸው መምህራን ያስቀመጥነው ግብ 0፡75፡25 ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር በ2002 የነበረው ስብጥር ( ) በ2006 ወደ ( ) አድጓል፡፡ የ2ኛውን እትእ ስናዘጋጅ የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር ግብ ለማስቀመጥ እንደ መነሻ መወሰድ ያለበት የባለፈው አፈጻጸም ብቻ ሳይሆን የአለም አቀፍ ተሞክሮም ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል ለሁለተኛው እትእ ስለሚኖረው የመምህራን ጥራትን ሲታሰብ መምህራን ከሚኖራቸው የትምህርት/የሙያ ደረጃ እና ሙያዊ ስነምግባር አኳያ መዳሰስ አስፈላጊነትን ትኩረት በማድረግ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ከመምህራን ብቃትም አንፃር ብዙ መሻሻል የታየ ቢሆንም አሁንም ከሚፈለገው እና ከስታንዳርድ አኳያ ብዙ ይቀረናል፡፡ የዓለም ዓቀፍ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ጥራት መደበኛ መለኪያ ከአጠቃላይ መምህራን የሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው ድርሻ መጠን ነው፡፡ በዚህ መለኪያ በተለይ በምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የሚጠበቀው የሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ድርሻ 50% እንደሆነ ዓለም አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ስታንዳርድ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ላቅ ያለ ምርምር በማካሄድ ለቴክኖሎጂ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ተጨባጭ አቅም ይኖራቸዋል፡፡ በ2005 ዓ.ም ከነበሩን 23,905 መምህራን መካከል የ PhD ወይም ሶስተኛ ዲግሪ የነበራቸው 12.5% ገደማ ሲሆኑ በ2007 ዓ.ም ግን ይህ አሃዝ 15 እንደደረሰ የትምህርት ሚኒስቴር መረጃ ያሳያል፡፡ ይህም ቢሆን በአንዳንድ በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉ ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ2010 ማሌዥያ የነበራት የPhD መምህራን ብዛት ከአጠቃላይ የመምህራን ድርሻ ውስጥ 47.3% ይሸፍናል፡፡[9] የደበቡ አፍሪካው ኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ 59%፣ ጋና ዩኒቨርሲቲ 41%፣ የኬኒያው ኬኒያታ ዩኒቨርሲቲ 34% ሲሆን በሀገራችን ደግሞ የተሻለ ደረጃ ያለው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 26% ላይ ነው፡፡ ስለሆነም በሀገራችን ባሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የ3ኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ምጣኔ እጅግ መሻሻል እንዳለበት ያሳያል፡፡

[9] The National Higher Education Action Plan,2011-2015, Malaysia

ሌሎች ሀገሮች የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ብቻ ሳይሆን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ማገባደጃ ይደረሳል ተብሎ ከታሰበው የመምህራን ስብጥር (0፡75፡25) ለመድረስም በፍጥነት መጓዝ ይኖርብናል (Growth and Transformation Plan, 2010-2015, FDRE)፡፡ በአፈፃፀምም የመምህራኑን ቁጥር 24252 ማድረስ የተቻለ ቢሆንም ስብጥሩን ወደ ታቀደው ለማምጣት አልተቻለም፡፡ በ2005 ዓ.ም ማጠናቀቂያ የነበረው 38% የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 50% የሁለተኛ ዲግሪና 12% የሶስተኛ ዲግሪ በ2007 ዓ.ም 27፡58፡15 የደረሰ ሲሆን ግቡን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት ተጨማሪ ጥረት እንደሚጠይቅ ያመላክተናል፡፡ ከትምህርት መስክ አንጻር ስናየው ደግሞ በአቅርቦትም ይሁን በጥራት ደረጃ የኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ መምህራን ልማት ልዩ ትኩረት ይሻል፡፡ በ2006 ዓ.ም ከዩኒቨርሲቲዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በዚህ መስክ የአንድ ነባር ዩኒቨርሲቲ ካሉት 1,310 ያህል መምህራን ውስጥ 145 (11.1%) የ3ኛ ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ ገና በጣም አዲስ ከሆኑት አንዱን ዩኒቨርሲቲ ብናይ ደግሞ ካሉት 134 መምህራን መካከል 11 (0.8%) ብቻ የሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ይገኙበታል፡፡

በመምህራን አቅርቦት ዙሪያ የሚታየውን እጥረት ለመቅረፍ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የ2ኛና 3ኛ ዲግሪ የሚማሩ መምህራን ቢኖሩም  በቀጣይ ይህ የሚሻሻል ቢሆንም እንኳን በዚሁ ወቅት ያለደረጃቸው ገብተው የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር አሁንም አሳሳቢ ነው፡፡ በተለይም የመጀመሪያ ዲግሪ ይዘው በረዳት ምሩቃን ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር ካሉት መምህራን ውስጥ በ2007 ዓ.ም 38% ያህሉን ይሸፍናሉ፡፡ የረዳት ምሩቃን ድርሻ በ2002 ዓ.ም ከነበረበት ደረጃ የተሻለ ቢሆንም በቀጣይ ተጨማሪ ርብርብ ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም መምህራን ከሚያስምሩት አንድ ደረጃ ከፍ ያለ የትምህርት ደረጃ እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ ብዙ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ይህ ሁኔታ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ገዘፍ ብሎ የሚታይ ሲሆን ሀገሪቱ ለመስኩ የሰጠችውን ትኩረት ሊያሳካ በሚያስችል መልኩ የመምህራን ትምህርት ደረጃን በከፍተኛ ሁኔታ ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

ይህን ትልቅ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት የሁለተኛ ዲግሪ ቅበላን በማስፋፋት ተፈላጊውን የሰው ኃይል የመፍጠር ስራ በስፋት ሲተገበር ቆይቷል፡፡ በተቻለ መጠንም በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን የሚከታተሉ መምህራን ቁጥርም እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከላይ በተቀሱት መንገዶች ብቻ ችግሩን መቅረፍ ስላልተቻለ (በተለይም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ) የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃንን በመምህርነት ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ሲቀጥሩ ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህን ረዳት ምሩቃንን በሁለተኛ ዲግሪ ማሰልጠን የታሰበውን ያህል ባለመሄዱ ምክንያት ያለደረጃቸው የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር ከፍ ከማለቱም በላይ የመምህራን በትምህርት ደረጃ ያለው ስብጥር 27፡58፡15 (መጀመሪያ

ዲግሪ፣ ማስተርስ ዲግሪና 3ኛ ዲግሪ) እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ስለሆነም በአንድ ወቅት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህራንን በሰፊው የመቅጠር ስራ መከናወኑ እየጨመረ የመጣውን የትምህርት ሽፋንን ሊሸከም የሚችል የአካዳሚክ ስታፍ መፍጠር ላይ ትልቅ እምርታ ያሳየ ቢሆንም የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅና በየደረጃው የሚጠበቀው የመምህራን ስብጥር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ ከብዙ ነገሮች አኳያ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ አሁን ያለንበት ወቅት በትምህርት ተቋማት እና በተማሪዎች መካከል ውድድር እጅግ ወሳኝ የሆነበት፣ እንዲሁም ከግሎባላይዜሽን እና ከአለማቀፍ የንግድ እና የአገልግሎት ስምምነት የተነሳ የትምህርቱ ዓለም በውድድር የተቃኘ በመሆኑ የትምህርት ተቋማት ስለውድድር እንዲያስቡ ይገደዳሉ፡፡ በመሆኑም የትምህርት ጥራት ለተወዳዳሪነት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስድ ይሆናል፡፡ ጥራት ያላቸው ተቋማት የታላላቅ ባለድርሻ አካላትን እይታ ይስባሉ፡፡ ለምሳሌ በስፖንሰር አድራጊዎች ወጪያቸው የሚሸፈንላቸው ተማሪዎችን (ከሃገር ውስጥም ሆነ ከውጪ) በሚያስምሩበት እንዲሁም ምርምሮችን በሚያካሂዱበት ወቅት ሌሎች በርካታ የእርዳታ ድርጅቶች ተነሳሽትን ያሳድጋል፡፡

**ሠንጠረዥ 8.** የመምህራን ብዛት በትምህርት ደረጃ

| ዓ.ም | የአካዳሚክ ሰራተኞች ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመጀመሪያ ዲግሪ | የህክምና ዲግሪ (MD) | 2ኛ ዲግሪ | 3ኛ ዲግሪ (PhD) | ሌሎች ተመጣጣኝ ደረጃዎች | ድምር |
| 2004 | 7,435 | 1,871 | 8,975 | 1,577 | 121 | 19,982 |
| | (46.6%) | | (44.9%) | (8.5%) | | |
| 2005 | 6,993 | 1,665 | 11,443 | 2,590 | 263 | 22,968 |
| | (37.7%) | | (49.8%) | (12.5%) | | |
| 2006 | 6993 | 1665 | 11443 | 2590 | 2529 | 22968 |
| ዕድገት በመቶኛ | - 5.9 | -11 | 27.5 | 64.2 | 117.4 | 14.8 |

*ምንጭ፡- Education Statistics Annual Abstract 2005 E.C, MoE*

ከነባሮቹ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 72 ፕሮፌሰሮች፣ 203 ተባባሪ ፕሮፌሰሮች እና 552 ረዳት ፕሮፌሰሮች የነበሩት ሲሆን በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚጨመሩትን ታሳቢ ሳናደርግ እነዚህ በድምሩ 827 መምህራን በመተባበር እያንዳንዱ ሶስት አባላት ያሉት ቡድን ቢያቋቁምና በዓመት አንድ የሶስተኛ ዲግሪ ምሩቅ ቢያፈሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፒ.ኤች.ዲ የማስመረቅ አቅም በዓመት 276 ሊደርስ ይችላል፡፡ የሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች አቅምም በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን ያድጋል፡፡ ይህ የማስመረቅ አቅም የውጭ የትምህርት ዕድል ካልታከለበት ብቻውን የዩኒቨርሲቲዎችን የመምህራን ፍላጎትም ሆነ በጠቋሚ ጥናቱ (በሠንጠረዥ 8) ላይ የተመለከተው ሃገራዊ የሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው ባለሙያዎች ፍላጎት ማሟላት ከባድና ፈታኝ ስራ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር ለማሻሻል አቅጣጫዎች ተቀይሰው ሊተገበሩ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጎን ለጎን ቢያንስ ተገቢው የስብጥር ደረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ መምህራኖቻችን በትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች እና በሙያዊ ስነምግባር እንዲታነጹ አጫጭር የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላም በኩል የመምህራንን ጥራት ለማሻሻል የትምህርት ደረጃቸውን ማሳደግ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ በከፍተኛ ዲፕሎማ መርሃ ግብር የሚሰጠው የመምህራን የማስተማር ክህሎት ማሳደጊያ አሰራር ያሉበትን ችግሮች በመቅረፍ ውጤታማነቱን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን የመምህርነትን ባህሪና ስነ ምግባር ተላብሰው ተማሪዎችን የአካዳሚክ እውቀት ብቻ ሳይሆን በመልካም ስነ ምግባር ታንጸው እንዲወጡ የሚያደርጉት ጥረት የሚበረታታ ነው፡፡ መምህራን የአለባበስ ሁኔታቸው፡ ለተማሪዎች የመልካም አርዓያነታቸው እና በመሳሰሉት ዙሪያ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆነው በኃላፊነት እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ መምህራን ከሙያቸው የማይጠበቁ ስነ ምግባሮችን ሲያንጸባርቁ ይስተዋላሉ፡፡ አንዳንድ መምህራን ሃይማኖትን፣ የአካባቢ ተወላጅነትን፤ ጾታን፤ ገንዘብን፤ ሱሰኝነትን፣ የአለባበስ ሁኔታን እና የፖለቲካ አመለካከትን ተገን በማድረግ የሙያውን ስነ ምግባር አያከብሩም፡፡ በተለይም ተማሪዎች በጥረታቸው የጥሩ ውጤት ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ እየተገባቸው ሴት ተማሪዎችን ጾታዊ ትንኮሳ በማድረግ፣ የአካባቢያቸው ተወላጅ የሆኑ ተማሪዎችን በሀገር ልጅነት፣ ገንዘብ ያላቸውን ገንዘብ በመቀበል፣ እነሱ የሚከተሉትን ሃይማኖት የሚከተሉትን፣ ተመሳሳይ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን እንዲሁም የተመሳሳይ ሱስ ተገዥ ለሆኑ ተማሪዎች ያልሰሩትን ውጤት ሲሰጡ የተገኙ መምህራንም አልታጡም፡፡ አንዳንድ መምህራን ደግሞ የመምህርነት ሙያ የማይጠይቀውንና የተወገዘውን አለባበስ በመጠቀም መጥፎ

አርዓያነታቸውን ለተማሪዎች ሲያካፍሉ ይታያሉ፡፡ የመምህርነት ሙያ ሙያው የሚፈቅደው ሙያዊ አለባበስ ያለው እንደሆነ እየታወቀ መምህራኑም አይጠቀሙበትም፣ አመራሩም ክትትሉን ችላ ብሎታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ድርጊቶች ተፈላጊውን ክህሎትና እውቀት ጨብጠው የሚወጡ ተመራቂዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ ለትምህርት ስርዓታችንና ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ትልቅ መሰናክል ነው፡፡ ሁኔታው በመልካም ስነ ምግባር የታነጸ ትውልድ ከመፍጠር አኳያ የተጣለብንን ኃላፊነት እንዳንወጣ ስለሚያደርገን ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩን የተማሪዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች አለባበስ ስርዓት ወጥቶላቸዋል፡፡ ለምሳሌ በታንዛኒያ የዳሬሰላምና የአርድሂ ዩኒቨርሲቲዎች ለተማሪዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች የተፈቀዱና የተከለከሉ የአለባበስ ህጎች ተዘጋጅተውና ተቀርጸው እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡ በሀገራችንም ይህ ተሞክሮ ቢወሰድ የተማሪዎችና የመምህራን የአለባበስ ስርዓትን ማስተካከል ይቻላል፡፡

በመሆኑም የሚከተሉት ተግዳሮቶች በቀጣይ ሊፈቱ እንደሚገቡ ስለታመነባቸው በዚህ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህም፡- የመመረቅ ምጣኔን ለመቀነስ የተወሰዱ እርምጃዎች አመርቂ አለመሆን፣ የመምህራን የማስተማር ክህሎት በሚፈለገው መጠን አለመድረሱ፣ የመምህር ተማሪ ጥምርታ ከፍተኛ መሆን፣ የተማሪዎችና የመመህራን ስነምግባር ችግር መኖር፣ የመመረቂያ ጊዜን በታለመለት ጊዜ አለመጠናቀቅ (ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች)፣ ከፍተኛ የኮርስ ጫና መኖሩ፣ የቴ/ሙ/ስ/ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡበት ግልጽ የሽግግር ስርዓት አለመኖሩ፣ ጠንካራ የምሩቃን ጥናት (strong tracer study) አለመኖር ፣ የስራ ተወዳዳሪነትና የተፈላጊነት ደረጃ ማነሱ፣ የፕሮግራም አግባብነትና የስራ ገበያው ፍላጎት አለመጣጣም፣ በድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም የመቀበል አቅምም ከተጣለው ግብ አኳያ ዝቅ ማለት የሚጠበቀው የሰው ኃይል ማሟላቱ ላይ ያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ በመስፋፋት ላይ ላሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በስታንዳርዱ መሰረት የሚጠበቁትን መምህራን ዕጥረት ማስከተሉ፣ የትምህርት ግብዓት (ላቦራቶሪ፣ ላይብራሪ፣ ወርክ ሾፕ፣ የሰው ኃይል ወዘተ) በተፈለገው ደረጃ አለማሟላት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግንባታዎች ወቅታቸውን ጠብቀው ያለመጠናቀቅ፣ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች (ሴቶች፣ ታዳጊ ክልሎች፣የገጠር አካባቢዎችን፣ ልዩ ፍላጎት ወዘተ) ከታችኛው እርከን እስከ መሰናዶ በሚደርሱበት አግባብ ተጠናክሮ የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስርዓት አለመጠናከሩ፣ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች መንግስት በልዩ ድጋፍ ቅበላ እየተደረገ ያለ ቢሆንም ከገቡ በኋላ የሚደረገው የማብቃት ድጋፍ አነስተኛ መሆኑ፣ በቅድመ ምረቃ ፕሮግራምም ሆነ በድህረ ምረቃ

ፕሮግራም በከፍተኛ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት አነስተኛ መሆን ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

### 3.4. የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር

ምርምር ለአዳዲስ ፈጠራዎች ምንጭነትና ቀጣይነት ላለው የአገር ልማት መሰረታዊ መሳሪያ በመሆኑ በማንኛውም የዕድገት ደረጃ በሚገኝ አገር ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ አገራችንም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የምታደርገውን ጉዞ እውን ለማድረግ ትችል ዘንድ ቁልፍ ሚና ለሚጫወቱት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምርምርን ዋነኛ ተልዕኳቸው እንዲያደርጉ በአገሪቱ ትምህርትና ፖሊሲና ስልጠና የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ተቀምጧል[10]፡፡

በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገሪቱን የሰለጠነ የሰው ሃይል ከማፍራት ባሻገር የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ፍላጎቶች መሰረት ያደረገ ምርምር በማድረግ የምርምር ውጤቶችን መሰረት ያደረጉ ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለማውጣት የሚያስችሉ ምክረ ሃሳቦችን በማመንጨት እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳት፣ በማላመድና በማሸጋገር በአገሪቱ የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት እንዲቻል ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

አገራችን የጀመረችውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት በዘላቂነት ለማስቀጠል እንድትችል በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ቴክኖሎጂን የማፈላለግ፣ የመማር፣ የማላመድ፣ የማመንጨትና የመጠቀም እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የምርምር መሰረተ ልማትን ማጠናከር እና የምርምር አቅምን በመገንባት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ምርምር ማካሄድ የሚሉት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተጣሉ ግቦች ነበሩ፡፡በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚደረገው ምርምር ችግር ፈቺ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ በማተኮር አገራችን ወደፊት ልትደርስ ከአሰበችው የእድገት ደረጃ ለመድረስ የሚያስፈልጋትን ቴክኖሎጂ የመለየት፣ የማፈላለግ፣ የማላመድ፣ የመፍጠር እና የመጠቀም ተልዕኮ መወጣት እንዲችሉ ሀገራዊ የምርምር ፖሊሲ ማዕቀፍ በማውጣት የምርምሮችን አግባብነት መከታተል፣ የቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎችን ማቋቋም፣ ተቋማቱ የራሳቸውን የምርምር ፖሊሲ ማውጣት፣ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት የመፍጠር፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች የምርምርና ፈጠራ ውጤቶች ማዕከላት እንዲኖራቸው

[10] ETP,1994,proclamation 650/2009,

የመደገፍ፣ ምርምር በፋይናንስ እጥረት እንዳይስተጓጎል ተቋማቱ የምርምርና ፈጠራ ፈንድ በማቋቋም ከተለያዩ ምንጮች ሃብት ለማግኘት ገቢ ማማንጨት የሚያስችሏቸው የንግድ ተቋማት የመፍጠር በዕቅድ ዘመኑ በዋና ዋና የማሳኪያ ስልትነት የተቀመጡ ነበሩ፡፡

ከዚህ አንፃር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካባቢያቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ማዕከል ያደረጉ የምርምር የትኩረት መስኮችን ለይተው የጥናትና ምርምር ስራዎችን እያከናወኑ ቢሆንም ለከፍተኛ የምርምር ስራዎች የሚሆኑ መሰረተ ልማቶችን ገንብተውና አደራጅተው በአገር አቀፍ ደረጃ በተለዩ ጉዳዮች ላይ ምርምር በማድረግ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጡ ስራዎችን አከናውነዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተቋማቱ ውስጥ በምርምር የሚሳተፉ መምህራን ቁጥርም አነስተኛ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በዕቅድ ዘመኑ ሁለት የቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች ተቋቁመዋል፤ አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ የምርምር ፖሊሲ አዘጋጅተው በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መሪነት በትምህርት ሚኒስቴር ተባባሪነት የሚመራ ሀገራዊ የጋራ መድረክ ተቋቁሞ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በአገሪቱ በመገንባት ላይ በሚገኙ ታላላቅ የልማት ፕሮጀክቶች (የህዳሴው ግድብ፣ የስኳርና የማደባሪያ ፋብሪካዎች ግንባታዎች) የሚሳተፉበት ሁኔታ ተጀምሯል፡፡ እንዲሁም ተቋማት ከአካባቢያቸው ቀረቤታ አንፃር በሚሰሩ ፕሮጀክቶች ላይ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማመቻቸት የልምድና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር እየተደረገ ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ያላቸው ተቋማትም የፈንድ ማፈላለጊያ ማዕከላትን በማቋቋም ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ መመቻቸቱ በጥንካሬ የሚወሰዱ ሲሆን ሀገራዊ የምርምር ማዕቀፉ ባለመጠናቀቁ የምርምሮችን አግባብነት፣ ጥራትና ውጤታማነት እንዲሁም በተቋማቱ የተዘጋጁ የምርምር ፖሊሲዎችን ውጤታማነት ለመገምገም ግን አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ባለፈው ዕቅድ አፈፃፀም የተገኙ ልምዶችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን ሊደረስባቸው የሚችሉ ግቦችንና የማስፈፀሚያ ስልቶችን በማስቀመጥ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 3.4.1. የምርምር አቅም

አገሪቱ የምትፈልገውን የልማት ዕቅድ ለማሳካት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን ሳይንሳዊ አመራር የሚሰጥ፣ የወቅቱን የምርምር መረጃዎችና ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት የሚማሩ፣ የሚያፈላልጉና የሚያላምዱ ከፍተኛ ባለሙያዎች (ተማራማሪዎች) ያስፈልጋሉ፡፡ ስለዚህም ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ ተመራማሪዎችን በማፍራት ከሀገሪቱ ፈጣን እድገት ጋር መራመድ የሚችል የላቀ የምርምርና የቴክኖሎጂ  አቅምና ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመጀመሪያው የእ.ት.እ የዩኒቨርሲቲዎችን የምርምር አቅም ለማሳደግ በርካታ ስራዎች ተሰርተዎል፡፡

#### 3.4.1.1. የሰው ሀይል አቅም

አሁን ካለው የተቋማት ነባራዊ ሁኔታ መረዳት እንደተቻለው  በምርምር ላይ የሚሳተፉ መምህራን ቁጥር አነስተኛ (ከ10% የማይበልጥ) ነው፡፡ በ2007 ዓ.ም በተቋማት ውስጥ በማስተማር ከሚገኙ መምህራን ውስጥ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ብዛት 58% እንዲሁም  ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው 15% መሆኑን ለመረዳት ተችሏል[11]፡፡ ይህ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ማገባደጃ 75% እና 25% ለማድረስ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር ሲታይ ክፍተት መኖሩን ያሳያል[12]፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በዓለም አቀፍ ደረጃም የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሊኖረው ከሚገባው 3ኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ቁጥር 50% ስታንዳርድ አንፃር ሲታይ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡በመሆኑም በተቋማቱ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የምርምር አቅም ማነስ በመኖሩ የምርምር ስራዎች በብዛትም ሆነ በጥራት የሚፈለገውን ያህል እንዳልሆነ ይጠቁማል፡፡
አመታዊ የ PhD የማስመረቅ አቅም የሃገራዊ የምርምር አቅም አንዱ መለኪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡የሃገራችን ህዝብ ብዛት በ2005 ዓ.ም 85 ሚሊዮን አካባቢ ደርሷል በሚል ታሳቢ ከተቀመጠው ግምት[13] አንፃር በዚሁ ዓመት በአገሪቱ ባሉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሶስተኛ ዲግሪ በPhD  95 ገደማ ምሩቃን ስለነበር ከአጠቃላዩ የህዝብ ብዛት ምጣኔ አንፃር ሲሰላ  አንድ ሚሊዮን ህዝብ 1 PhD ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይህ አሃዝ መካከለኛ ገቢ ካላቸው እና በፈጣን ዕድገት ውስጥ ከሚገኙ አገሮች ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ደቡብ አፍሪካ ከአንድ ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ 47 PhD ምሩቃን፣ ደቡብ

---

[11] MoE(2013/14). Education Annual Abstract
[12]MoE(2010). ESDP VI

[13] OPHCC (1994 Census)

ኮሪያ ከአንድ ሚለዮን ህዝብ ውስጥ በአማካይ 172 PhD፣ ኬንያም ከአንድ ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ ከ 4 እስከ 5 ያደረሰች ሲሆን ሌሎች በፈጣን እድገት ላይ የሚገኙ አገራት በPhD የማስመረቅ አቅማቸውን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ላይ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከ1998-2006 ዓ.ም ( የዘመኑ አቆጣጠር የሚጣራ) ባሉት ዓመታት ቻይና ወደ 40%፣ ህንድ ወደ 8.5% እንዲሁም ኮሪያ ወደ 7.1% አቅማቸውን ያሳደጉ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ[14]፡፡

ለሀገራችን የሶስተኛ ድግሪ ያላቸው ምሩቃን አነስተኛ መሆን እንደ ዋና ምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል በአገሪቱ የነበሩት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቁጥር አነስተኛ መሆኑ አንዱ ነው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሶስተኛ ዲግሪ ደረጃ የማስመረቅ አቅም የነበራቸው ተቋማት አዲስ አበባና ሐረማያ ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ነበሩ፡፡ዓመታዊ የቅበላ አቅማቸውም በየጊዜው እያደገ የመጣ ቢሆንም አሁንም ከሚጠበቀው በታች ናቸው፡፡ በየአመቱ የሚወጡ የPhD ምሩቃን ቁጥር በማሳደግ ብቻውን ግን ሃገራዊ የምርምር አቅም መገንባት ማለት ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ አሁን ባለው የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አብዛኛው የ3ኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን በርካታ ጊዜያቸውን በምርምር ላይ ስለማያሳልፉ ለወደፊቱ ይህንን ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል ስልት መከተል ይጠበቃል፡፡ በሌሎች ሀገሮች ለምሳሌ በታንዛኒያ የድህረ ዶክትሬት ዲግሪ (post doctoral research program) ምርምር በማዘጋጀት የ3ኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራንን በምርምር ላይ ያተኮረ ስራ እንዲሰሩ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህም በሀገራችን ይህንን ድህረ ዶክትሬት ምርምር ፕሮግራምን (post doctoral research program) ተቋማዊ በሆነ መልኩ መጀመርና የምርምር የልህቀት ዩኒቨርሲቲዎችን አቅም ማሳደግ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡
ከ2003--2005 ዓ.ም የበነበሩት ጊዜያት በአጠቃላይ 162 ምሩቃን ብቻ ያስመረቁ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የምርምር አቅም ከሚገመገምባቸው ሌሎች መንገዶች አንዱ ከአንድ ሺህ ተቀጣሪዎች (ሠራተኞች) መካከል ያለው የተመራማሪዎች ቁጥር ነው፡፡በዚህ መሠረት እ.ኤ.አ ከ2008 እስከ 2011 ያደጉትና በማደግ ላይ ያሉትን የተለያዩ ሀገራትን መረጃ ሲነጻጸር ክፍተቱን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ናይጀሪያ በ2.42፣ ቻይና 2.4፣ ግብፅ 3.89፣ ጀርመን 12.25፣ ፊንላንድ 23.11፣ ኢንዶኔዥያ 0.4፣ ብራዚል 2.46፣ ደቡብ አፍሪካ 2.8፣ ደቡብ ኮሪያ 14.7፣ ቱኒዚያ 10.25፣ ኬኒያ 0.27፣ ማሌዥያ 6 እና ሞሮኮ 3.52 ሲሆኑ ኢትዮጵያ ደግሞ ከአንድ ሺህ ሠራተኞች መካከል 0.07 ተመራማሪ ብቻ ያላት መሆኑን ሳያል፡፡

[14] UNESCO, 2012

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የየሀገራቱ የሴት ተመራማሪዎች ምጣኔ ሲታይ ደግሞ ናይጀሪያ በ23.4%፣ ግብፅ 41%፣ ጀርመን 20%፣ ደቡብ አፍሪካ 39%፣ ቱኒዚያ 51.2%፣ ኬኒያ 17.8%፣ ማሌዥያ 45.8% እና ህንድ 14.8% ሲሆኑ ኢትዮጵያ 7.89% ብቻ ነው፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚያስተምሩ ሴት መምህራን ውስጥ በምርምር ላይ የሚሳተፉ ሴቶች ድርሻ ከ2% በታች ብቻ መሆኑን በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል በ2006 ዓ.ም የተደረገ ጥናት ያሳያል፡፡

### 3.4.1.2 የምርምር በጀት

የብዙ አገሮች ምርምር ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠውና ጠቀም ያለ በጀት የሚመደብለት መሆኑን ነው፡፡ በተባበሩት መንግስታት እ.አ.አ. ከ2008 እስከ 2011 የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው ሀገራት እንደየኢኮኖሚያቸውና የሥልጠኔ ደረጃቸው ከጥቅል ሀገራዊ ሀብት (GDP) ውስጥ ለምርምርና ልማት የሚመድቡት የበጀት መጠን ይለያያል፡፡ ለምሳሌ፡- ቻይና 1.84%፣ ግብፅ 0.43%፣ ብራዚል 1.16%፣ ደቡብ አፍሪካ 0.87%፣ ደቡብ ኮሪያ 3.74%፣ ማሌዥያ 1.07%፣ ህንድ 0.76% ኢትዮጵያ ደግሞ በ0.24% የሚመድቡ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በጀት የምርምር አቅምን የሚወስን ቁልፍ መለኪያ ነው፡፡ መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ማስፋፋት ከፍተኛ ወጪ እያወጣ ቢሆንም ለምርምር የሚመድበው በጀት ግን በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለአብነትም የ2004 ዓ.ም መረጃ እንደሚያሳየው ለዩኒቨርሲቲዎች ከተመደበው በጀት ውስጥ የምርምር ድርሻ 0.97% ነበር፡፡ ስለሆንም በሀገራችን ለምርምር የሚመደበውን በጀት ምጣኔ ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የምርምር ውጤትን መሰረት አድርጎ የሚመደብ በጀት የምርምር ጥራትና የምርምሩን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ለመጨመር ወሳኝ ወይም ጠቃሚ ማበረታቻ በመሆኑ በርካታ አገሮች ተጠቅመውበታል[15]፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያተኮሩ የምርምር ስራዎች እንዲሰሩ ለማበረታታት እና በውጤታማነት ላይ የተመሰረተ ምርምር እንዲሰራ ውድድርን መሰረት ያደረገ የበጀት አመዳደብ ስልት በመቀየስና በመተግበር የተቋማትን ውጤታማነት ማሳደግ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ከውጭ አገር ተቋማት ጋር ባላቸው ግንኙነትና ትብብር በሚያገኙት ገንዘብ የምርምር ስራዎችን የሚያከናውኑ ቢሆንም ሃገራዊ ፋይዳቸው ለማሻሻል የምርምር ፖሊሲን አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋልን ይጠይቃል፡፡

[15] Ashcroft (2004).13 New Higher Education Institutions for Ethiopia:

### 3.4.1.3. የምርምር መሰረተ ልማት

ከአደረጃጀት ፣ከሰው ሀይል እና ከበጀት ባሻገር መሰረተ ልማት ወሳኝ የምርምር አቅም የሚወስን ጉዳይ ነው፡፡ከሚፈለገው የምርምር፣ ቴክኖሎጂን የማላመድና የማሸጋገር ተግባር አንፃር አሁን በተቋማቱ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ከፍተኛ የሆነ ሳይንሳዊ ምርመርና ፈጠራን ለማከናወን የሚያስችል የተሟላ የመሰረተ ልማት ሁኔታ ተፍጥሯል ማለት አይቻልም፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች ለምርምር አስቻይ ሁኔታ በሚፈጥሩ የመስክ እና የቤተ-ሙከራ ግብዓቶችና መሳሪዎች ገና በተሟላ ደረጃ አልተደራጁም ፤ በተሰሩ ምርምሮች ዙሪያም በዘመናዊ መልክ በሚገባ የተደራጁ የመረጃ ስርዓቶች የሉም[16]፡፡ ስለዚህም ተቋማት ከተልኳቸው አንፃር ተገቢ መሰረተልማቶችን ያሟሉ ከፍተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ላቦራቶሪዎችንና ወረክሾፖችን ማደራጀትን ትኩረት ሊሰጡት ያስፈልጋል፡፡

### 3.4.2. የምርምር ጥራትና አግባብነት

የሃገራችን የምርምር ዓላማ በዋናነት ችግር ፈችነትና የሃገሪቱን ልማትናፍጥነት ማስቀጠል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ከዚህ አንፃር ዩኒቨርሲቲዎች እንደ ያካባቢያቸው ሁኔታ የምርምር የትኩረት መስኮች ለይተዋል፡፡በዚህ መዕቀፍም እንቅስቃሴ ጀምረዋል፡፡ ነገር ግን በሳይንስ፣ቴክኖሎጅ እና ፈጠራ ፖሊሲያችን የዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ውጤቶች የቴክኖሎጅ አቅም ከመፍጠር አኳያ ግን ገና ብዙ ርቀት መ□ዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እስካሁን በነበረው አካሄድ ችግር ፈቺ ምርምር ለመመራት የሚስችልን የመርመር አጀንዳ አቀራረፅ፣የፋይናነስና የማበረታቻ እና የክትትል ስርዓት በተሟላ መገንባት ችለናል ብለን መደምደም አንችልም፡፡

ምርምር እውቀትንና ፈጠራን ከማመንጨት ባሻገር ትምህርትን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም እንዲሁም ተመራማሪ ምሩቃንን ለማፍራት ይጠቅማል፡፡ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር ማዕከላት በመሆናቸው[17] የሚያከናውኑት የመማር ማስተማር ሂደት ከምርምሩ ጋር ቁርኝት በመፍጠር ፈጠራንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን የሚያበረታታ እንዲሁም በወቅታዊ መረጃዎች እና ችግሮች ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ መሰረት ተቋማቱ በደንቦቻቸው ላይ አንድ መምህር 25% ጊዜውን በምርምር ላይ ማዋል እንደሚገባው ቢያስቀምጡም በትግበራው ላይ ግን ክፍተቶች አሉ[18]፡፡ አብዛኞቹ መምህራን በምርምር ስራ ላይ የማይሳተፉ ሲሆን ተማሪዎችም

[16] Ashcroft (2004).13 New Higher Education Institutions for Ethiopia

[17] Ashcroft (2004).13 New Higher Education Institutions for Ethiopia:

[18] [18] ***HERQA Publication Serieses***

የምርምር ክህሎታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ እድሎች በሚፈለገው ደረጃ እንደማይመቻቹላቸው፣ የመማር ማስተማር ሂደቱም በተለመደው የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ላይ ያተኮረ መሆኑን የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ[19]፡፡

በሌላ በኩል በመምህራኑ የሚደረጉ ምርምሮች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ መምህራኑ የአካዳሚክ ደረጃቸውን ለማሳደግ (ለPromotion) ዓላማ የሚሰሩት እንጂ የመማር ማስተማሩን ተግባር ለመደገፍና የተማሪዎችን የምርምር ክህሎት በማሳደግ ተተኪ ተመራማሪዎችን ለማፍራት ታስቦ የሚደረጉ አይደሉም፡፡ ለዚህ ችግር እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል የመምህራኑ የአቅምና የፍላጎት ውስንነት፣ የመምህራን የማስተማር ጫና፣ ለምርምር የሚመደብ በጀት ማነስ፣ በየተቋማቱ የሚደረገው የክትትልና ድጋፍ ማነስ የሚሉት ይገኙበታል[20]፡፡

የሌሎች አገሮች የምርምር ባህል የሚያሳየው የመማር ማስተማሩን ስራ ከመደገፍ ባሻገር ተቋማት ደረጃቸውን ከኮሌጅ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያሳድጉበት አንዱ መንገድ ምርምር ነው፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር ኮሌጅ ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማደግ የሚችለው በሀገሪቱ የትምህርት ጥራት ቁጥጥር ኤጀንሲ ለሚሰሩ ምርምሮች መጠንና የማስተማር ብቃት ያስቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ሲያሟላ ብቻ ነው[21]፡፡ በመሆኑም የምርምርና የመማር ማስተማር መስተጋብርን የሚያዳብሩ ስልቶች መቀየስ ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳንድ የሀገራችን ተቋማት የምርምር ዩኒቨርሲቲን ለመገንባት ራዕይ ይዘው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ ለራዕያቸውም እውንነት ግን የምምህራን የምርምር ተሳትፎ እና ውጤታቸውን በተጨባጭ ማሳደግ ይኖርባቸዋል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሃገራችን የምርምር ውጤታማነት ቁልፍ መለኪያ ችግር ፈቺነት ነው፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን የምርምር ሳይንሳዊ ጥራት የሚለካበት መንገድ የምርምር ህትመት ነው፡፡ይህ ማለት በተላይ በዩኒቨርሲቲዎች የሚሰሩ ምርምሮች ሳይንሳዊ አካሄድ የተከተሉና በሌላው ዓለም የምርምር ማህበረሰብ ጥራታቸው የተመሰከረላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ጥራት ባላቸው የህትመት ጆርናሎች የምርምር ውጤት ሳይንሳዊ ግልጽነት መፍጠር ማለት ነው፡፡ የታተመ የምርምር ውጤት ችግር ፈቺ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ የችግር ፈቺ የምርምር ውጤት ህትመት ማበረታታት ይኖርብናል፡፡ በምርምር ላይ የላቁ አገሮች የምርምር ውጤታቸውን ለመለካት የሚጠቀሙበት መንገድ ሲሆን ይህንን የፈጠሩት እውቀት በህትመት አማካይነት ከዓለም

---

[19] ውዱ መለሰ (2013).Research-Teaching Link in Higher Education Institutions of Ethiopia
[20] ውዱ መለሰ (2013).Research-Teaching Link in Higher Education Institutions of Ethiopia
[21] Ashcroft (2004).13 New Higher Education Institutions for Ethiopia

ማህበረሰብ ጋር በመጋራት በሳይንስ ሀገራዊ ገጽታቸውን ያበለጽጋሉ፡፡በዚህ ሂደትም የፈጠራ ባለቤት በመሆን ለሃገራቸው ገቢ ያስገኛሉ፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የምርምር ስራዎች በሚፈለገው አግባብነትና ጥራት ስለመሆኑ በመለኪያነት ሊወሰዱ ከሚችሉት መካከል በአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ባገኙ መፅሄቶች ላይ ታትመው መውጣት መቻላቸው እና የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚው ደርሰው በሚያስገኙት ጥቅም ወይንም ፋይዳ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያዊያን ተመራማሪዎች የሰሩት የምርምር ውጤቶች ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን ያስመሰከሩበት በዓለም አቀፍ ታዋቂ ጆርናል ላይ ያሳተሙት ጽሑፍ ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ቢመጣም ከብዙ አገሮች ሲነፃፀር አሁንም ገና አንስተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ኤልሲቨር የተባለ ዓለም አቀፍ አሳታሚ ድርጅት (Publishing Company) ባወጣው መረጃ መሠረት ከ1951 እስከ 1984 ዓ.ም በየዓመቱ ከ30 እና 40 የማይበልጡ የኢትዮጵያዊያን ተመራማሪዎች ጽሑፎች በዓለም አቀፍ ጆርናሎች የታተሙ ስለመሆናቸው ያሳያል፡፡ ሆኖም ግን በ2005 ዓ.ም በአንድ ዓመት ውስጥ ከ3000 በላይ የምርምር ሥራዎችን ማሳተም የተቻለ በመሆኑ አበረታች ለውጥ የታየ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር ሲወዳደር አሁንም ገና ብዙ ይቀረዋል፡፡ ለምሳሌ፡-ግብፅ በአንድ ዓመት (እ.ኤ.አ.በ2013) ብቻ 12,000 ህትመቶች ያሳተመች ሲሆን ኢትዮጵያ ግን በህዝብ ቁጥራቸው ከኛ በጣም የሚያንሱት ኬኒያ እና ጋና ከሚያሳትሙትም ያነሰ ነው፡፡ ከአግባብነት አንፃር በኢትዩጵያ የተደረጉ ምርምሮችም በአብዛኛው በህክምናና በግብርና ዘርፎች የተደረጉ የምርምር ስራዎች ሲሆኑ በኢንጅነሪንግ ዘርፍ የወጡ የምርምር ስራዎች በጣም አነስተኛ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በዝቅተኛ ወጪ የሚደረጉ ምርምሮች ጥራት በሚፈለገው ደረጃ ስለማይሆን የምርምር ውጤቶች በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር አቀፍ ጆርናሎች ታትመው የመውጣት አቅማቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አንዳንድ የዩኒቨርሲቲ መምህራን የምርምር ስራዎቻቸውን ታዋቂና ተቀባይነት በሌላቸው (predatore journal) በመባል በሚታወቁ የውጪ አገር ጆርናሎች ላይ ያሳትማሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጆርናሎች ለንግድ ዓላማ በሚሰሩ አሳታሚዎች የሚታተሙ በመሆናቸው ከፍተኛ የጥራትና የተአማኒነት ችግሮች ያሉባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ በእነዚህ ዓይነት ጆርናሎች ላይ የምርምር ስራቸውን በማሳተም ለደረጃ እድገት ጥያቄ የሚያቀርቡ መምህራንም በመኖራቸው የአፈፃፀም ችግር እያጋጠመ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የህትመት ጆርናል አንስተኛ ስታንዳርድ (minimum standard ) ከማውጣት አኳያ ትኩረት ይሻል፡፡

### 3.4.3 የምርምር ውጤቶች ተደራሽነትና ስርፀት

ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎችን መጠን አንስተኛ  ቢሆኑም እነሱም ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡በዩኒቨርሲቲ የሚሰሩ ምርምሮች ለተጠቃሚው ደርሰው ለሚፈለገው አገልግሎት ውለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዲያስገኙ ከማድረግ አንጻር ሃገራዊም ሆነ ዩኒቨርሲቲ አቀፍ የተሟላ ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ ምርምሮች ያስገኙት ፋይዳም ተገምግሞ ደረጃው አልታወቀም፡፡ በመሆኑም በተቋማት የሚደረጉ የምርምር ውጤቶች ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ፣ ስትራቴጂዎችን ለማውጣት እንዲሁም ለውሳኔ ሰጪ አካላት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ተጨባጭ መረጃዎች ሆነው ሲያገለግሉ አይታይም፡፡ በዩኒቨርሲቲዎችና ኢንዱስትሪዎች መካከል ያለው ትስስርም ከሚጠበቀው አንፃር ብዙ አልተጓዘም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚው በአግባቡ መድረስ ካለመቻላቸውም ባሻገር ለባለድርሻ አካላት ሊያበረክቱ ስለሚችሉት ፋይዳ ማስገንዘብ ላይ እጥረት የተነሳም ጭምር ነው፡፡ በአንድ አንድ ተቋማት ለምሳሌ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ በድህር ምረቃ ፕሮግራሞች የተሰሩ 4000 የሚሆኑ የምርምር ውጤቶች በዩኒቨርሲቲው ድህረ ገፅ ላይ አስቀምጧል::[22] ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርምር ውጤቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መንገዶችንም መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የማህበረስብ አገልግሎት ጽንሰ ሃሳብ በተለያዩ አገላለጾች ይቀመጣል፡፡ለምሳሌ University community engagement, social responsiveness of universities,university community relationship, university industry partnership ወ.ዘ.ተ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ተግባሩ የሀገራዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተኮር ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ትግበራን በማፋጠን የሚፈለገውን ዓላማ ለማሳካት ለልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚሰጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ  ድጋፍ/አገልግሎት ነው፡፡ ይህ የተለያዩ ሃሳቦችን በማመንጨትና በማሸጋገር ማህበረሰቡን ቀጥተኛ ተጠቃሚ ማድረግም ይጨምራል[23]፡፡ በመሆኑም የማህበረሰብ አገልግሎት በኢትዮጵያ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችም ከተሰጧቸው ሶስቱ ተልዕኮዎች አንዱ ነው፡፡

[22] AAU Press, Publications and Dissemination

[23] Michgan State University Guidebook(2000)

ከላይ እንደተገለጸው በዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጠው የማህበረሰብ አገልግሎት ዋና ዓላማው ዩኒቨርስቲዎችና የአካባቢው ማህበረሰብ ያላቸዉን ሀብት (እውቀት፣ ገንዘብ፣ ጉልበት፣ ቁሳቁስ፣ ወዘተ) በማቀናጀት የእውቀት፣ የክህሎት እና ቴክኖሎጂ ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ በተቋሙ ተልዕኮ እና በማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ማምጣት ነው፡፡ ስለዚህም በሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠውን የማህበረሰብ አገልግሎት ማጠናከር ለዕቅድ ዘመኑ የተቀመጠ ግብ ነበር ፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎት በአካባቢ ማህበረሰብ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ፋይዳ የሚያመጣ ሲሆን ማህበረሰቡ በተቋማት ላይ ያላቸውን እምነት በመጨመር ጠንካራ አጋርነት እንዲኖር ከማድረግ በተጨማሪ ተማሪዎች በተግባር የተደገፈ እውቀት እና ክህሎት፤ችግርን የመለየት እና የመፍታት ችሎታን እንዲሁም ስራ የመፍጠር ዕድልን እንዲያዳብሩ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ከዚህ አንፃር በተቋማት ከተሰጡ ማህበራዊ አገልግሎቶች መካከል የታችኛውን እርከን የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ለት/ቤቶች ድጋፎችን የመስጠት፣ በጥናት የተገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለአካባቢው ማህበረሰብ የማሸጋገር፣ የህግ የማማከር እንዲሁም የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎት ዉጤታማ መሆን የሚችለው በጋራ ራዕይ እና የባለቤትነት ስሜት ሲከናወን በመሆኑ በተቋማት የሚሰጡ የማህበረሰብ አገልግሎቶች፣ የዩኒቨርሲቲ የኢንዱስትሪ አጋርነቶች፣ ከልማት ማህበራትና የአካባቢው መንግስት ጋር የሚደረግ ትብብር፣ስልጠናና ተከታታይ ትምህርት እና የማማከር አገልግሎቶቶች አሳታፊ እቅዶችን በማዘጋጀት እንደ አስፈላጊነቱም ስምምነቶችን በመፈራረም፣ ሂደቶችን እና ተጽዕኖዎችን በጋራ በመከታተልና በመገምገም ማከናወን ይገባዋል፡፡ ሆኖም ግን አሁን በተቋማት የሚሰጠው የማህበረሰብ አገልግሎት የግንዛቤ፣ የአደረጃጀት፣ የበጀትና የቀጣይነት ችግሮች ያሉበት፣ ወጥ በሆነ መልኩ በደንብና በመመሪያ ተደግፎ የማይመራ፣ ተቋማቱ ከተሰጣቸው ተልዕኮዎች አንፃር ዝቅተኛ ትኩረት የተሰጡት መሆኑን በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል በተቋማት ላይ ያደረገው የዳሰሳ ጥናት አሳይቷል[24]፡፡

በዚሁ ጥናት መሰረት የማህበረሰብ አገልግሎት ያለውን ሀገራዊ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት መንግስት ለዩኒቨርሲቲዎች ከሰጣቸው ተልዕኮዎች አንዱ በማድረግ በአዋጅ እና በተለያዩ ጊዜያት

[24] ESC (2014) Assessment of University Outreach in Ethiopa

በወጡ እቅዶች የተቀመጠ ቢሆንም አተገባበሩ ግን ክፍተት ያለበት ነው[25]፡፡ከሌሎች የተቋማት ተልዕኮዎች (መማር ማስተማርና ምርምር) ጋር ሲወዳደርም ዝቅተኛ ቦታ የተሰጠው መሆኑ፣ መምህራኑ ደረጃቸውን ለማሳደግ ከሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ባሻገር የማህበረሰብ አገልግሎት ጠቀሜታ እንዳለው በውል ያለመረዳት ችግሮች በተጨማሪ የመምህራን የደረጃ እድገት በዋናኛነት የሚያተኩረው በምርምሩና ማስተማሩ ላይ መሆኑ በዋነኛት የሚጠቀሱ ክፍተቶች ናቸው፡፡ ከአመለካከት አኳያ የማህበረሰብ አገልግሎት የጠንካራ መምህርነት ሳይንሳዊ ተግባር ተደርጎ የማይታይበት ሁኔታ አለ፡፡

በተቋማቱ የሚሰጡ የማህበረሰብ አገልግሎቶች በአብዛኛው አጭር እድሜ ያላቸው በፕሮጀክት መልክ የሚከናወኑና የዩኒቨርሲቲው ፕረግራሞች አካል ባለመሆናቸው ምክንያት ወጣ ገባነት ይታዩባቸዋል፡፡ የበጀት እጥረት ሲያጋጥም የሚቋረጡ ይሆናሉ፡፡በመሆኑም የአገልግሎቱ ቀጣይነት ችግር ያለበት እንደሆነ ጥናቱ አመልክቷል፡፡

በጥናቱ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በተቋማቱ ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ የማህበረሰብ አገልግሎት የተለያየ አደረጃጀት ያለው መሆኑን ከመገንዘብ በተጨማሪ ትኩረት ተሰጥቶት በብቁና በቂ የሰው ሃይል አልተደራጀም፣ የማህበረሰብ አገልግሎትን በአግባቡ ማደራጀትና መምራት የሚችሉ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በብዛት አይመደቡም፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በተቋማቱ ለማህበረሰብ አገልግሎት የሚመደበው በጀት ዝቅተኛ በመሆኑ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ከመገደቡም በተጨማሪ ለዚሁ ተልእኮ የሚመደበው በጀት አንስተኛ ከመሆነ ባሻገር የተመደበውንም በጀት በአግባቡ የማስተዳደር ችግሮች አሉበት፡፡

በመሆኑም የሚከተሉት ተግዳሮቶች በቀጣይ ሊፈቱ እንደሚገቡ የታመነበት ስለሆነ በዚህ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህም፡- የምርምር አቅም ማነስ፣ የምርምርና ማስተማር ቁርኝት በተገቢው ሁኔታ አለመተግበር፣ የምርምር በጀት ማነስ፣ የምርምር መሰረተ ልማት በበቂ ደረጃ አለመኖር፣ የምርምር አግባብነትና የጥራት ችግር መኖር፣ ጠንካራ የምርምርና የቴግኖሎጂ ሽሽግግር አለመኖር፣ በማህበረሰብ አገልግሎት ላይ የተዛባ ግንዛቤ መኖሩ፣ የአደረጃጀት ችግሮች መኖራቸው እና የማህበረሰብ አገልግሎት ቀጣይነት ላይ ታስቦ አለመሰራቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 3.5. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር፣ አደረጃጀትና አሰራር

በዓለማችን በትምህርት ዘርፍ የላቀ ደረጃ የደረሱ የበርካታ ታላላቅ ሃገሮች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እድገትን ስናጤን ሰኬታቸው ከነበሯቸው የአመራር አካላት ብስለትና የአሰራር ዘመናዊነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንደሆነ ይታያል፡፡ ብቃት ያለው የአመራርናአስተዳደር በሌለበት ሁኔታ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የትምህርት ጥራት፣ችግር ፈቺ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ማረጋገጥ አይቻልም ፡፡ የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራርና አስተዳደር ብቃት ለማሳደግ የተወሰዱ እርምጃዎችና የተገኙ ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከሚፈለገው ደረጃ አንጻር ግን ገና ብዙ ሥራዎች መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡

በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት አደረጃጀት የተቋማት አመራር ሲባል የዩኒቨርሲቲዎች ሥራ አመራር ቦርድን በማካተት ከፕሬዚዳንት እስከ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ያለውን የሚያጠቃልል ነው፡፡ እነዚህ የአመራር አካላት ተቋማቱ በአዋጅ የተሰጣቸውን ተልእኮ መውጣት እንዲችሉ በየደረጃው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመጠቀም ለተቋሙ ራዕይ መሳካት የሚያስችል አመራር ይሰጣሉ፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በከፍተኛ ሁኔታ መስፋፋት በተቋማቱ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅእኖ ያለው ሲሆን በተለይም የተቋማትን አመራር አሰራር እና አስተዳደር በከፍተኛ ሁኔታ ይፈታተናል፡፡ በተጨማሪም በተቋማቱ የሚከናወኑ የትምህርትን ጥራት እና አግባብነትን የማስጠበቅ፣ የምርምር እና የማህበረሰብአገልግሎት እና የፋይናንስ አገልግሎት በተቋማቱ አመራሮች ውሳኔ እና ክትትል የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡ ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሀገራችን እድገት የሚያበረክቱትን ሚና በአግባቡ እንዲወጡ በተገቢው የአመራር እውቀት እና ክህሎት የተገነባ ውጤታማ አመራር አስፈላጊ ነው፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር፣ አደረጃጀትና አሰራር በተመለከተ በመጀመሪያው የዕ.ት.ዕ እና በአራተኛው የትምህርት ሴክተር የእድገት ፕሮግራም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው የአመራርና አስተዳዳር ተቋማዊ ነፃነትንና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ አግባብና ስኬትን ማምጣት በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ለማድረግ በተያዘው እቅድ የተማሪዎች እና የመምህራን በአስተዳደራዊ አገልግሎት ያላቸው እርካታ ማሻሻል፣ሴቶች በከፍተኛ ትምህርት አመራር ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፣ የስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ሰትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት፣ የትምህርት አመራር የመረጃ ስርዓት በአገር አቀፍ እና በተቋም ደረጃ ማጠናከር፣የእቅድ አዘገጃጀት ክህሎትን እና የአመራር አቅምን በአገር አቀፍ እና በተቋማት ደረጃ ማሻሻል እና የተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረሞችን በመመስረት የምክክርና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማመቻቸት ሊከናወኑ የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፡፡

ከዚህ አኳያ ሀገራዊ ልማት የማቀላጠፍና የማሳካት ዓላማውን እውን ለማድረግ፤ ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ ተገቢነት እና ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት የተቋማት የማስፈፀም ዓቅም ግንባታ ቁልፍ መሳሪያ መሆኑን ታምኖበት ተቋማዊ ለውጥ በመቅረፅና በመተግበር ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገበት ቆይቷል፡፡ በዚህ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች አደረጃጀታቸውንና አሰራራቸውን እንዲሁም በተቻለ መጠን የማህበረሰባቸውን አመለካከት የመገንባት ዓላማቸውን ለማሳካት ወደሚያስችላቸው አቅጣጫ ለመቃኘት በተደረገው ጥረት በርካታ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በማድረግ፣ የውጤት ተኮር አሰራር ስርዓት በመጠቀም እንዲሁም የካይዘንን አሰራር ትግበራን በመጀመር ተቋማቱ ወጤታማነታቸውንና ቅልጥፍናቸውን ለማሻሻል ያደረጉትና እያደረጉት ያሉት ጥረቶች እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ባለፉት ዓመታት በተሰራው ሰፊ ስራ ምክንያት የተቋማዊ ለውጥ ምክር ቤት፣ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚደንቶች ፣ የለውጥ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና የአይ.ሲ.ቲ ዳይሬክተሮች ፎረሞች ተቋቁመው በየጊዜው ምክክርና ልምድ ልውውጥ በማድረግ ውጤታማ ተግባራት የተከናወኑ በመሆኑ ለቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ተግባር ነው፡፡

በአጠቃላይ የሀገራችንን ከፍተኛ ትምህርት ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሸጋግሩ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አደረጃጀት ተቋማቱ የተጣለባቸውን የሀገራችንን እድገት ማስቀጠል የሚያስችል የሰው ሀይል ማፍራት በሚያስችል መልኩ መደራጃት እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች በተለያየ መልኩ የራሳቸውን አደረጃጀት በማዘጋጀት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በአመራር ደረጃዎች መካከል ያለው የስልጣን ክፍፍል ከላይኛው አመራር እስከ ታችኛው አመራር ድረስ ተግበራትን በአግባቡ ማከናወን በሚያስችል መልኩ ወጥነት ያለው ያልተማከለ የሥራ ክፍፍል አለ ማለት አይቻልም፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የሚመራው የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አደረጃጀት ካለው የተቋማት መስፋፊት እና በተቋማቱ የሚከናወኑ የአካዳሚክ፣የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎትን ማከናወን በሚያስችል መልኩ መደራጀት አለበት፡፡

ከላይ የተገለፁት የተሰሩ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው የአመራር አቅምናአመለካከት ግን ቁልፍ ማናቆ ሆኖ ይታያል፡፡ከላይ እንደተጠቀሰው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር ማለት ቦርድን በማካተት ከፕሬዚዳንት እስከ ትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ያለውን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ ውሳኔዎችን በመስጠት አጠቃላይ አመራር የሚሰጡ አካላት ቦርድ፤ሴኔት እና አካዳሚክ ኮሚሽን ሲሆኑ በየደረጃው በአመራር ቦታ ላይ በመሆን በስራቸው ለሚገኙ አካላት አመራር የሚሰጡ ደግሞ ፕሬዜዳንት፣ ም/ፕሬዜዳንት፣ ዳይሬክተሮች፣ የኮሌጅ ዲኖች እና የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች በተቋማት አመራር ይካተታሉ፡፡ በተጨማሪም በየደረጃው ያለው የድጋፍ ሰጭ አመራርንም ያካትታል፡፡ የእነዚህን የአመራር አካላት የመሪነት እውቀት፣ ክህሎት እና አቅም መሻሻል ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡

ከአቅም ግንባታ አኳያ መጀመሪያ መጠቀስ ያለበት የተቋማት አመራር(መምህራንም) ጭምር በአገራችን ፖሊሲናስትራቴጂ ዙርያ የተሰጡ ስልጠናዎችናየተፈጠረው ግንዛቤ ዋናው ነው፡፡እነዚህ ስልጠናዎች የዩኒቨርሲቲ አመራሮች ሃገራዊ አድማስ ኖሯቸው የተቋማት እንቅስቃሴዎች ለመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጆዎች በማናበብ ለመምራት የሚስችል እውቀትናአመለካከት የገነቡባቸው አጋጣሚዎች ስለሆኑ በሚቀጥለው እ.ት.እ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

ከፖሊሲው ግንዛቤ በሻገር የእቅድ አዘገጃጀት ክህሎትን እና የአመራር አቅምን በሀገር አቀፍ እና በተቋማት ደረጃ ማሻሻል በተመለከተ የአመራሩን አቅም ለመገንባት በተለያዩ የመሪነት ክህሎቶች ላይ በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል አስተባባሪነት በ LMCD/ ULMCD ፕሮጀክቶች 528 ወንዶችና 92 ሴቶች በድምሩ 620 ለሚሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራሮች የአቅም ግንባታ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በተጨማሪም በተለያዩ ሀገራት የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ በማደረግ የአመራር አቅማቸውን እንዲያዳብሩ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ከዘርፉ አመራር ውስብስብነት እና ከሚጠይቀው ከፍተኛ የአመራር ክህሎትና እውቀት አንፃር በአመራሩ ላይ የሚታዩ ቁልፍ ችግሮች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ የመጀመሪያው የአመራሩ የክህሎት፣ የእውቀት እና የአቅም ችግር ሲሆን ይህም አመራሩ ስትራቴጃዊ አመራር እንዳይሰጥ በእቅድ ዝግጅት እና ትውውቅ፣ ፈፃሚን በማብቃት፤እቅድን በመተግበር፣ በመገምገም እና የቀጣይ አቅጣጫን በማስቀመጥ የተቋሙን ራእይ ለማሳከት በሚደርገው ተግባር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያስከትላል፡፡

በአጠቃላይ የየተቋሙ ከፍተኛ አመራሮችና በየደረጃው ያሉ የመካከለኛና የታችኛው የአስተዳደር ክፍል አመራሮች በአመራር ቦታ ላይ ሲቀመጡ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅች፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ አቅጣጫዎችና ልዩ ልዩ የውስጥ መመሪያዎችና ደንቦች ዙሪያ በአብዛኛው በቂ

ግንዛቤ አለመያዛቸው እንደክፍተት መያዝ አለበት፡፡ የአመራር አቅም ማነስ ችግር በዋናነት የሚመነጨው ቴክኒካዊ ክህሎት ማጣት፣ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አዘገጃጀት ችግር፣ የመረጃ አሰባሰብ፣ ትንተና፣ ትንበያና የትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት ያለማወቅ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡[26]

በሁለተኛ ደረጃ በአመራሩ የሚስተዋለው የአመለካከት ችግር ሲሆን አብዛኛው አመራር የተቋሙን ራዕይ መሳከት የሚችል አመለካከት በመያዝ አመራር የሚሰጡ እንዳሉ ሁሉ አንዳንድ አመራሮች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትን በማራመድ ፤የተለያዩ ከአመራር የማይጠበቁ ስነ-ምግባር በማሳየት የተቋሙን የአመራር ስርዓት ውጤታማነትን የሚፈታተኑ አመራሮችን አመለካከት ማሻሻል የሚያስችል ተከታታይነት ያለው ስራ በእቅድ ተይዞ መሰራት እንዳለበት ያመላክታል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአመራር ምደባ ስርዓት ሌላው ቁልፍ ችግር ሲሆን ከዚህ አኳያ አንዳንድ የአመራር ምደባ  በብቃት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ በቀጣይ በብቃት ላይ የተመሰረተ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር ምልመላና ምደባ በዕቅድ ተይዞ መሰራት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም አመራሩ ቁልፍ በሆኑ አካዳሚያዊ እና የምርምር ተግባራት ላይ እንዲያተኩር የተማሪዎች አገልግሎት (የምግብ አገልግሎት) በሌሎች አማራጭ መንገዶች መምራት የሚቻልበት ስርዓት ቀስ በቀስ በሂደት መዘርጋት አለባቸው፡፡ የአመራር እድገትን በተመለከተ የአመራር ቋት ከማዘጋጀት ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት  አመራሮች ከታችኛው ደረጃ በእድገት ወደ ላይኛው የአመራር ደረጃ የሚያድጉበት ስርዓት መዘርጋት እና የመተካካት እቅድ (succession plan) ተዘጋጅቶ መተግበር ይኖርበታል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር ግምገማን በተመለከተም የአመራሩን አቅም በትክክል መለካት እና እውቅና መስጠት የሚያስችል የግምገማ ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

በሀገራችን ሴቶች በከፍተኛ ትምህርት አመራር ላይ ያላቸው ተሳትፎ እንዲያድግ የተቀመጡ ግቦች ስኬታማ ነበሩ ማለት አይቻልም፡፡ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሴቶች የከፍተኛ አመራር ተሳትፎ በ2002 ዓ.ም በቁጥር 3 የነበረ ሲሆን ይህንኑ መነሻ በማድረግ በ2007 ዓ.ም ወደ 16 ለማድረስ በዕቅድ ተይዟል፡፡ ነገር ግን እስከ 2005 ዓ.ም  (ማብቂያ ድረስ ሴቶች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የበላይ አመራር ቦታ ላይ አንድ ብቻ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር ውስጥ ያለው የሴቶች ድርሻ ከተጣለው ግብ አኳያ እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይም በመካከለኛና የታችኛው የተቋማት አመራር እርከን ውስጥም የሴቶች ተሳትፎ 5% ብቻ መሆኑንና ከሴት መምህራን ድርሻ (10.6%) አንጻር

---

[26] Oulai, D., *et al*. (2011). Analysis of Capacity Development Planning and Management in Ethiopia. International institution for planning. UNESCO, France, Paris

ሲታይ አነስተኛ መሆኑን በ2006 ዓ.ም በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል የተደረገው የዳሰሳ ጥናት አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም በ2006 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲ ሴት መምህርን እና አመራሮችን ለዩ ድጋፍ እና የስርዓተ ፆታ እኩልነት ሁኔታ ለመዳሰስ የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው የከፍተኛ ትምህርት አመራር የሴቶች ተሳትፎ ችግሮች እንዳሉባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡[27] ለምሳሌ በአመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ እጅግ ዝቅ ያለ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ በጥናቱ ከተካተቱ 13 ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ካሉ 830 አመራሮች ውስጥ የሴቶቹ ቁጥር 38 (5%) ሲሆን ከ38ቱ ውስጥ በከፍተኛ አመራር ደረጃ ሴቶች አለመኖራቸው፣ በመካከለኛ ደረጃ 25 እንደዚሁም በዝቅተኛው ደረጃ 13 ብቻ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡

ስለዚህ ሴቶች በከፍተኛ ትምህርት አመራር ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግን በተመለከተ የተቀመጠው ግብ አነስተኛ በመሆኑ በቀጣይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሴቶች ወደ አመራር እንዲመጡ የኮታ ዘዴን በመጠቀም እና ልዩ የአመራር አቅም ግንባታ ሥርአትን በመዘርጋት የሚበረታቱበትን ሂደት በምልመላ እና ምደባ ሂደቱ በህግ ተወስኖ መቀመጥ አለበት፡፡ በተጨማሪም ለሴት አመራሮች ልዩ የአቅም ግንባታ ስርዓት ተዘርግቶ መተግበር አለበት፡፡ በአመራር ላይ ያሉትን ሴቶች ለማቆየት እና ለማበረታታት የሚያስችሉ የገንዘብ እና የቁሳቁስ (የመኖሪያ ቤት እና የትራንስፖርት አገልግሎት) የማበረታቻ ስርዓት መዘረጋት አለበት፡

የተቋማት አሰራር የተቋማት አጠቃላይ አስተዳደር እና ስራ አመራርን ያካትታል፡፡ የዩኒቨርሲቲዎች አስተዳደር እና ስራ አመራር ዘመናዊ የአስተዳደር እና የአሰራር ስርዓት ግንባታን ከሚፈለገው ደረጃ ያልደረሰ በመሆኑ ተማሪዎች እና መምህራን በአሰራሩ ላይ ቅሬታ ሲያቀርቡ እና በተጨማሪም ሰላማዊ የመማር ማስተማር እንዳይኖር የራሱን አስተዋፅኦ ሲያበረክት ይታያል፡፡ ስለሆንም የተቋማት አሰራር ስርዓት ዘመናዊ እና ውጤታማ የማድረግ ተግባር በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡

የተማሪዎች እና የመምህራን በአስተዳደራዊ አገልግሎት ያላቸው እርካታ ማሻሻል በተመለከተ መሰረታዊ የስራ ሂደት (BPR)፣ ውጤት ተኮር የአፈጻጸም አመራር (BSC)፣ ካይዘን እና የኢንፎርሚሽን ቴክኖሎጅን በመጠቀም ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተማሪዎች እና የመምህራን አስተዳደራዊ አገልግሎት እርካታ በመጠኑም ቢሆን ማሻሻል የተቻለ ቢሆንም

[27] HESC(2014),Assessment Female Faculty and leadership.Affirmative action and gender equality in new public universities in Ethiopia.Dr.Anouka van erdewijk and Dr Franz Wong.

በሚፈለገው ደረጃ ያልደረሰ በመሆኑ  ለቀጣይ ሁኔታውን ለማሻሻል ግቦችና ስልቶች ተቀርጸው ሊተገበሩ ይገባል፡፡ ስለሆነም መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ፣ የውጤት ተኮር ስርዓት እና የካይዘን ሥርዓት በሁሉም ተቋማት እንዲተገበር በማድረግ ውጤታማና ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት ሀገሪቱ የምትፈልገውን የሰው ሀይል በብዛት፣ በዓይነትና በጥራት የማፍራት አቅማቸውን በዘላቂነት ለመገንባት የተጀመረውን አካሄድ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

የስርዓተ-ፆታን መሰረት የደረገ ሰትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት በተመለከተ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሰትራቴጅክ እቅድ ዝግጅትን እና ትግበራ የክትትል አሰራር በተሟላ ያልተዘረጋ በመሆኑ ሰትራቴጅክ እቅድ ስርዓተ-ፆታን ማከተቱን ማረጋገጥ አልተቻለም ስለሆነም በቀጣይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሰትራቴጅክ እቅድ ዝግጅትን የክትትል እና የግምገማ ስራ ግብና ስልት ተቀርፆ ሊተገበር ይገባል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር ያለው የትምህርት ስራ አመራር መረጃ ሥርዓት እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን የጠራ እቅድ ለማዘጋጀትና አፈፃፀምን ለመከታተል የራሱ ሚና ተጫውቷል፡፡ ነገር ግን በሚፈለገው ደረጃ ያልደረሰ በመሆኑ ማጠናከር እና በሀገርና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃም የትምህርት ስራ አመራር መረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ወቅታዊነትና ተአማኒነት ያለው መረጃ ለተለያዩ አገልግሎቶች ለማዋል የሚያስችል እንዲሆን መሰራት ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ደንቦችና አሰራሮች በከፍተኛ ትምህርት እና በሌሎች ሀገር አቀፍ ደንቦችንና መመሪያዎች ማዕቀፍ ውስጥ በተለይ የግድ መለያየት በሌለባቸው መስኮች ላይ ወጥነት ባለው መልኩ እንዲቃኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 3.5.1. የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስ ሥርዓት

መንግስት በአጠቃላይ ለትምህርት ሴክተሩ ከፍተኛውን ቦታ በመስጠት በየዓመቱ እጅግ ግዙፍ በጀት እየመደበ የትምህርት ልማቱን በማፋጠን ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት በሀገራችን የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቁጥር ከነበረበት ደረጃ በጥቂት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በብዙ እጥፍ አድጓል፡፡ በመሆኑም መንግስት ለዚህ ዘርፍ መስፋፋትና መጠናከር በየዓመቱ የሚመደበው በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል፡፡ ለምሳሌ፡- በ1993 ዓ.ም 436.8 ሚሊዮን የነበረውን ዓመታዊ በጀት በ2001 ዓ.ም ወደ 3.9 ቢሊየን ያሳደገበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ወቅት የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ዓመታዊ አማካይ የበጀት እድገት ከ32.6 ወደ 88.2 በመቶ እጅግ ከፍተኛ በሚባል ደረጃ አድጓል፤ ለሴክተሩ ከሚመደበው በጀትም 26.9 በመቶ ድርሻ

እንዳለው ተመልክቷል[28]፡፡ ይህ አሃዝ (26.9 በመቶ) የዓለም ባንክ መምሪያ ካስቀመጠው ደረጃ ከ15 እስከ 20 በመቶ ጋር ሲነጻጸር ከፍ ብሎ የሚገኝ ሲሆን ይህም መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ያሳያል፡፡

በእርግጥ መረጃዎች እንደሚያሳዩት አጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ በጀቱ ሲታይ ከዓመት ወደ ዓመት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ያሄደበት ሁኔታ በትክክል ታይቷል፡፡[29] ከዚህም በተጨማሪ መንግስት ለከፍተኛው ትምህርት በሰጠው ልዩ ትኩረት በ2007 ዓ.ም ከፌዴራል የመንግስት በጀት ውስጥ 14 በመቶ ለዚህ ዘርፍ አውሏል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በየዓመቱ ከ12 እስከ 15 በመቶ የሚደርስ የፌዴራል መንግስት በጀትን ለከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ይመድብ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለዘርፉ ማስፋፊያም የተመደበውን በጀት ስንመለከት በ2003 ዓ.ም ከነበረው 12.3 ቢሊየን ብር በ2007 ዓ.ም ወደ 24.56 ቢሊየን ብር ከፍ በማድረግ ቁርጠኝነቱን አሳይቷል፡፡ ይህም ለከፍተኛ ትምህርት ማስፋፊያ የተመደበው በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ በእጥፍ ያሳደገበት ሁኔታ እንዳለ ለማየት ተችሏል፡፡

አዳዲስ ተቋማትን መክፈትም ሆነ ነባሮቹን የማስፋፋት ሥራ ሁሉ እየተከናወነ ያለው በዋናነት ከመንግሥት ካዝና በሚመደበው በጀት ነው፡፡ በዚህ መሠረት መንግስት በከፍተኛ ትምህርቱ ዘርፍ ሁለንተናዊ ዕድገት ለማምጣት ከመንግስት ወጪ እስከ 25% እየመደበ ከማስተማር በተጨማሪ የተለያዩ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት የሚመድበው በየጊዜው እየጨመረ ቢሆንም ከተማሪዎች ቅበላ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ለነፍስ ወከፍ ተማሪ የሚወጣው ወጪ ግን ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው፡፡ ከሰሃራ በታች ያሉት የአፍሪካ ሀገራት የአንድ ተማሪ ዓመታዊ ወጪ በአማካይ 1500 ዶላር ሲሆን በአጎራባች ሀገራት ደግሞ ለምሳሌ፡- በታንዛኒያ 3236 ዶላር፣ በኬኒያ 1800 ዶላር እና በኡጋንዳ 800 ዶላር ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ልምዶች እንደሚያሳዩት አሁን ባለው ሁኔታ አንድ ሀገር በየዓመቱ ለተማሪ የሚያወጣው ወጪ ከ1000 ዶላር በታች ከሆነ የከፍተኛ ትምህርትን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለመስጠት አዳጋች እንደሚሆን ያሳያል፡፡

የካፒታል ወጪን ሳይጨምር ሀገሪቷ በየዓመቱ ለእያንዳንዱ ተማሪ ለመማር ማስተማር ስራ (መደበኛ በጀት) የሚታወጣው ገንዘብ (Recurrent expenditure per student) 922 ዶላር እንደ

[28] Kennedy Munyua, W. and Sewale Abate, (2013). Revenue Diversification and Resource Utilization in Ethiopian Universities. In Damtew Teffera, (Edt). Funding Higher Education in Sab-Saharan Africa. Palgrave Macmillan

[29] Kennedy Munyua, W. and Sewale Abate, (2013). Revenue Diversification and Resource Utilization in Ethiopian Universities. In Damtew Teffera, (Edt). Funding Higher Education in Sab-Saharan Africa. Palgrave Macmillan

ደረሰ መረጃዎች ያሳያሉ):: ይህ ደግሞ አፍሪካ በወቅቱ በየዓመቱ ከምትመድበው 2000 ዶላር በጣም ያነሰ ሆኖ ይገኛል:: እንዲህም ሆኖ ሳለ የሀገራችን ልምድ ሲታይ በየዓመቱ ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚመደበው መደበኛ በጀት (recurrent expenditure) ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ሄዷል:: ይህ የመቀነሱ ሁኔታ ደግሞ አግባብነትና ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት አሉታዊ ተጽዕኖው የጎላ ይሆናል::

የበጀት አመዳደቡ ውጤታማነትንና ቀልጣፋነትን በሚያረጋግጥ አኳኋን የሚፈፀምበት አቅጣጫ የተቀመጠ ቢሆንም በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለመሆን ገና ብዙ ይቀረዋል:: በሌላ በኩል እስካሁን ድረስ በተማሪዎች ወጪ መጋራት የሚሸፈነው ከወጣባቸው አጠቃላይ የትምህርት ወጪ ውስጥ 15% ብቻ በመሆኑና የትምህርት ወጪው በላይ የሚሸፈነው በመንግስት በመሆኑ ከሌሎች ሀገራት አንፃር ሲታይ በሂደት አዋጭነቱ እየታየ ቀስ በቀስ ማስተካከልን ይጠይቃል:: አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በበርካታ ሀገሮች የተማሪዎች ወጪ መጋራት ከመደበኛ ወጪዉ 20% እና ከዚያ በላይ ሲሆን ባደጉ አገሮች ይህ አሃዝ ከ40-50%፣ ይደርሳል:: በታዳጊ አገሮች ደግሞ የተማሪዎች የወጪ ድርሻ ከ10-20% ነው::የከፍተኛ ትምህርት በጀት በመንግስት ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥር ከመሆኑ በሻገር የበጀት አመዳደቡ ስርዓት ሙሉበሙሉ ውጤታማ ነው ተብሎ ለወሰድ አይችልም::

በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዙ አገሮች የከፍተኛ ትምህርት በጀት አመዳደብን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የጥቅል በጀት ቀመር እየተተገበረ ይገኛል። በዚህ መሠረት በአገራችን የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የጥቅል በጀት ቀመርን ተግባራዊ ለማድረግ ቀመሩ የሀገራችንን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቷል። የማስተግበሪያ ስልቶችም ተነድፈውና የPolicy brief ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ቀርቦ በቂ ውይይት ተደርጎበታል። የበጀት ቀመሩ በውጤት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ስለሆነ በዋናነት ለማስተማርና ለትምህርት ተዛማጅ ለሆኑ ተግባራት ብቻ የሚውለውን በጀት ከግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ሲሆን ፅንሰ ሃሳቡም ውጤት ተኮር አፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የበጀት ቀመር ከጥቅል በጀት ጋር ይቀናጃል የሚል መነሻ ሃሳብም አለው። ሆኖም ግን የጥቅል በጀት ቀመሩ በተለያዩ ምክንያቶች እስከ ዛሬ ድረስ ሳይተገበር ቆይቷል።[30] ስለሆነም ከውጤታማነቱና አስፈላጊነቱ አንጻር ውሳኔ አግኝቶ መተግበር ያስፈልጋል።

---

[30] Mogus Yigezu, (2013). Funding Higher Education in Ethiopia: modalities, challenges, opportunities and prospects. In Damtew Teffera, (Edt). Funding Higher Education in Sab-Saharan Africa. Palgrave Macmillan

### 3.5.2. የበጀት ውጤታማነት

መንግሥት ከራሱም ይሁን በተለያየ መንገድ ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ብሎ የሚያገኘውን ገንዘብ እና ሌሎች ግብዓቶችን ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ መጠቀም መቻል ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ውስን ሀብቶች የትምህርት ተሳትፎን በማሳደግ፣ የትምህርት ብክነትን በመቀነስ፣ ያለአግባብ ያለሥራ የሚቀመጡ የሰው ሀብት እና ፋሲሊቲዎች አጠቃቀምን በማሳደግ፣ የተማሪ አገልግሎቶችን ለድርጅቶች በመስጠት ፣ በትምህርት ላይ ጫና የሚያሳድሩ ጉዳዮችን በመቀነስ ለመማር ማስተማሩ ሥራ በቂ ጊዜን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ አግባብነት በሌላቸው ምክንያት የተራዘሙ የትምህርት ፕሮግራሞች የጊዜ እርዝማኔን በማሳጠር ወጪ መቀነስና ተሳትፎን ማሳደግም አንዱ ትከረት የሚሻ ጉዳይ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአስተዳደር ዘርፍ ሠራተኞችን ከአካዳሚክ ዘርፍ የሰው ሀይል ጋር ያላቸውን ምጣኔ በመቀነስ ለአስተዳደር ሥራ የሚወጣውን ወጪ በመቀነስ፣ ወዘተ ውጤታማ ሥራን መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ጉዳይ አስመልክቶ በአገራችን ካሉት የተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎችን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል፡፡ በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል እየተሰበሰበ ካለው መረጃ በአንድ ነባር ዩኒቨርሲቲ በ2005 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የነበረው የአካዳሚክ ሠራተኞች ቁጥር 1192 ሲሆኑ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቁጥር ደግሞ 2245 በምጣኔ ወደ 1፡2 የሚጠጋ፣ በአንድ አዲስ ዩኒቨርሲቲ 196 የአካዳሚክ ሠራተኞች ሲኖሩ የድጋፍ ሠራተኞች ቁጥር 206 በምጣኔ ወደ 1፡1፣ እንደዚሁም በአንድ የመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ ባለው ዩኒቨርሲቲ፣ 698 የአካዳሚ ሠራተኞች ሲኖሩ 522 የድጋፍ ሠራተኞች አሉ፡፡ በሌላ ነባር ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በ2002/3 ዓ.ም ወደ 2,743 አካዳሚክ ሠራተኞች ሲኖሩት 5,566 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ነበሩት፤ ይህም በምጣኔ ወይም በጥምርታ ሲታይ 1፡2 ብቻ ይሆናል፡፡ ይህ ጥምርታ በአካዳሚክና በድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ወጥነትና ሚዛናዊነት የሌለው ምጣኔ መኖሩን ሲያመላክት ከፍተኛ የአስተዳደር ሥራዎች እንዲበዙ እንደሚያደርግና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቅልጥፍና አነስተኛ መሆኑንና የሰው ሀይል አስተዳደር ጫና የሚጨምር ሁኔታ መኖሩ ለመገመት አያዳግትም፡፡ ስለሆነም ከመማር ማስተማሩ አንጻር የፋይናንስ ውጤታማነትን ለማሳደግ ያለውን የሰው ሀብት በአግባቡ እና በቀልጣፋ ውጤታማነት መጠቀም መቻልና የአካዳሚክ ሠራተኞችና የድጋፍ ሰጪ ወይም አስተዳደር ሠራተኞችን እንደ ስራው ባህርይ ቁጥር ማመጣጠን ተገቢ ይሆናል፡፡

### 3.5.3. የበጀት ምንጮች

አቅምን ታሳቢ ያደረገ የተማሪዎች የወጪ መጋራት ድርሻን ማሳደግ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋማቶቻችን የራሳቸውን ገቢ በማመንጨት ወጪያቸውን በከፊል መሸፈን እንዲችሉ ከአመራርና አሰራር ብቃት በተጨማሪ የተሻለ የገቢ ማመንጫ ፖሊሲና ሥርዓት ሊኖራቸው እንደሚገባ ነው፡፡ ስለሆነም ወደፊት የሚታሰበው ተጨማሪ የማስፋፋት ተግባራትን ለማሳካት ውጤታማና ቀልጣፋ የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት ብቻ ሳይሆን የበጀት ምንጭንም ማስፋት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የፋይናንስ ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የፋይናንስ ምንጭን ማበራከት፣ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀምን ማሻሻል ቁልፍ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መሆን አለባቸው፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስ ተቋማቱ የሚያከናውኑት የመማር ማስተማር፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት፣ የተለያዩ ህንጻዎች ግንባታ፣ የአጋርነት፣ ዓለም አቀፋዊነት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የትምህርት ተሳትፎ እና የትምህርት ጥራት ፍላጎትን ለማሳደግ፣ ወዘተ ሥራ ጋር ተያይዞ የሚጠይቀው በጀት እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር መንግሥት የከፍተኛ ትምህርቱን ዘርፍ ልማት ለማፋጠን ከራሱ ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ የተለያዩ የገንዘብ ምንጮችን በማፈላለግና በመጠቀም የታለመውን ግብ ለማሳካት ቁርጠኛ አቋም ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት ተቋማት ራሳቸው የሚያመነጩትን የውስጥ ገቢ፣ በተለያየ መንገድ ከትምህርት ልማት አጋሮች የሚገኘውን እርዳታ፣ ከእያንዳንዱ ተማሪ የሚሰበሰበው የትምህርት ክፍያና የወጪ መጋራት (15 በመቶ) ገንዘብ ወጪን ለመሸፈን የሚጠቀሙባቸው የገቢ ምንጮች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ሌሎች ተጨማሪ ምንጮችን በስፋት መጠቀም ካልተቻለ በስተቀር እጅግ በጣም እየጨመረ የሚሄደውን ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ የተማሪዎች ቁጥር፣ የተማሪዎች አገልግሎት እና ከነጻ ገበያ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የትምህርት ግብዓት የዋጋ ጭማሪ አስፈላጊውን በጀት በሚፈለገው ደረጃ የመሸፈኑ ጉዳይ ፈታኝ እንደሚያደርጉት ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን ያለው የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስ ሥርዓት ተቋማት በላቀ ደረጃ የገቢ ምንጮቻቸውን በማስፋፋት ከሙሉ የመንግሥት ጥገኝነት ለመላቀቅ በከፊል ራሳቸውን በበጀት እንዲደጉሙና መንግሰትን እንዲደግፉ ለማድረግ የሚያበረታታ ስርዓት መገንባት ያስፈልጋል፡፡

የተለያዩ ሀገራት የከፍተኛ ትምህርትን ወጪ ለመሸፈን የተለያዩ የፋይናንስ ምንጮችን በማበራከት ይጠቀማሉ፡፡ ታንዛኒያ የወጪ መጋራትን፣ አዲስ የፈጠራ ዘዴ (New innovative model) በማለት ለምሳሌ፡- ገበያ ሞዴል (Market model)፣ የትምህርት ዲያስፖራ ቦንድ (Diaspora education bond)፣ የትምህርት ቦንድ (Education bond) ስትጠቀም፣ ቦትስዋናም የወጪ መጋራትን፣ የግል ትምህርት ተቋማትን፣ የተለያዩ የማህበረሰብ አካላት (Philanthropy) (ማህበራትን፣ ቤተክርስቲያንን፣ የህጻናት እርዳታ ድርጅቶችን፣ ግለሰቦችን፣ ወዘተ) የፋይናንስ አካል በማድረግ፣ የተለያዩ ቀረጦችን ለምሳሌ፡- የቱሪዝም፣ የአልኮል፣ የሙያ እና ሥልጠና ፈንድን በልዩ ሁኔታ ለከፍተኛ ትምህርት ብቻ በማሰብ የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለዘርፉ ታውላለች፡፡[31]የውስጥ ገቢን ማበራከት በተመለከተ ተቋማት መንግስት ከሚመድበው በጀት በተጨማሪ የተለያዩ ኢንተርፕራይዞችን በመመስረት፤ የምርምር እና የማማከር ተግባራት ለሌሎች ተቋማት በመስጠት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለአብነትም አጫጭር ስልጠናዎችን በመጠቀም የውስጥ ገቢን በማሳደግ ከመንግስት ከሚመደበው በጀት ውስጥ የተወሰነውን ለመሸፈን በእቅድ ተይዞ መከናወን አለበት፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን የወጪ መጋራት አስመልክቶ ወጪውን የሚጋሩት ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የትምህርት ባለድርሻ አካላት በሙሉ ሲሆኑ ይህንንም ውጤታማ ለማድረግ ሀገራቱ አስተማማኝ የብድር ሥርዓት (Loan scheme) ዘርግተው እየሰሩበት ይገኛሉ፡፡ የብድር ሥርዓቱ ደግሞ ለሁለቱም ማለትም ለመንግሥት እና ለግል የትምህርት ተቋማት የሚመቻች እንደሆነ መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ የተማሪዎች የወጪ መጋራት ለሁሉም በአንድ መንገድ እንዳልሆነም ልምዶች ያሳያሉ፡፡ ተማሪዎች ከመጡበት የቤተሰብ የገቢ መጠን ላይ ተመስርቶ፣ እንደ የመክፈል አቅማቸው፣ የኢኮኖሚ ደረጃቸው፣ የተማሪዎች የትምህርት አፈጻጸም ደረጃ እና የሚማሩት የትምህርት መስክ ዓይነት፣ ወዘተ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የወጪ መጋራቱ ድርሻ ከአንድ ወይም ከትንሽ እስከ መቶ ፐርሰንት የሚሸፍኑ ይሆናል፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሀገራችን የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል በአማካይ 43.9 በመቶ እና ከጠቅላላ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች መካከል ደግሞ 55.4 በመቶው የትምህርት ወጪያቸውን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ መደበኛ ባልሆኑ መርሃ ግብሮች ውስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች የራሳቸውን ወጭ ይሸፍናሉ፡፡ ከመደበኛ ተማሪዎች ውስጥም የዩኒቨርስቲ የምግብ አገልግሎት የማይጠቀሙ በቤተሰብ ድጎማ ከውጭ የሚመገቡ ተማሪዎች በየጊዜው ቁጥራቸው እየበዛ እንደሄደ ይስተዋላል፡፡ ምናልባት እነዚህ

---

[31] Victoria Damane and PatrickMolutsi, (2013). Crisis of a Rich State. In Damtew Teffera, (Edt). Funding Higher Education in Sab-Saharan Africa. Palgrave Macmillan

ተማሪዎች የትምህርት ወጪያቸውን በተሻለ ደረጃ የመጋራት አቅም እንዳላቸው ሁኔታው ያመለክታል፡፡

በ1986 ዓ.ም የተዘጋጀው የሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ እንደሚያሳየው በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ገብተው የሚማሩ ተማሪዎች የወጪ መጋራትን በአገልግሎትና በገንዘብ መልክ እንደሚከፍሉ ጠቅሶ የክፍያ መጠኑ ቀስ በቀስ በሂደት እየጨመረ እንደሚሄድ ብራራል፡፡ ይሁን እንጂ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም ሲተገበር ግን በአገልግሎት መክፈል ካለባቸው ተማሪዎች በስተቀር በሁሉም ተማሪዎች መካከል ልዩነት (Differentiated cost sharing scheme) ሳይኖር በወጥነት ተማሪዎች ከትምህርት ጋር ተያያዥ ከሆነው ወጪ ውስጥ 15 በመቶ እንደሚከፍሉ መረጃው ያሳያል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በየዓመቱ መሰብሰብ ካለበት የወጪ መጋራት ውስጥም ከ1 በመቶ የማይበልጥ ገንዘብ ብቻ እየተሰበሰበ ይገኛል፡፡ ይህም የወጪ አሰባሰብ ሥርዓቱ ውጤታማነት አነስተኛ መሆኑን ያመላክታል፡፡

እንደዚሁም የወጪ መጋራት ሥርዓቱ ተጨማሪ ጉዳዮችን ለምሳሌ፡- የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት (Inclusive education) የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት ከባለሙያዎች ሃሳብ ሲሰነዘር ይታያል፡፡ ምክንያቱም ደግሞ የአካል ጉዳተኞች በተለይም ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች አስተርጓሚ በመቅጠር እየከፈሉ ስለሚማሩ ተጨማሪ ወጪ ስላለባቸው ወጪው ከሌሎቹ ሁኔታው ከተመቻቸላቸው ተማሪዎች ጋር እኩል ስለማይሆን ነው፡፡የወጭ መጋራትን በተመለከተ የአመላለስ ሂደትን ለማሻሻል የሚያስችል ስልት መቀየስ እና መተግበር ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከወጭ መጋራት በተጨማሪ የሴት እና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተሳትፎ እና የመመረቅ ምጣኔ ለመሻሻል እንዲረዳ የገቢ አቅማቸውን መሰረት ያደረገ የብድር እና የድጎማ አገልግሎት የማቅረብ ስራ ሊተገበር ይገባል፡፡

በመሆኑም የሚከተሉት ተግዳሮቶች በቀጣይ ሊፈቱ እንደሚገቡ ታምኖበት በዚህ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህም፡ የአመራሩ የመሪነት እውቀት ክህሎት እና አቅም በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ የሴት አመራሮች ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ መሆን፣ የከፍተኛ ትምህርት አሰራር ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆኑ፣ የከፍተኛ ትምህርት የሚመራው ዘርፍ እና የዩኒቨርሲቲዎች አደረጃጀት በአግባቡ ያልተደራጀ መሆኑ፣ የበጀት አጠቃቀም ውጤታማ አለመሆን (በአግባቡ ጥቅም ላይ አለማዋል) በዋናነት የተወሰዱ ናቸው፡፡

## 4. የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዕቅድ፣

ቀደም ሲል የኢትዮጲያ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ለልማቱ ወሳኝ ሚና የሚጫወት መሆኑን በመገንዘብ ፈጣን እድገት ያስመዘገበውን የከፍተኛ ትምህር ልማት እርምጃዎች እና እስከ አሁን ድረስ የተሰሩ ስራዎች ቀርበዋል፡፡ ከህዳሴው ጉዞ አንጻር የዘርፉ ዋና ዋና ክፍተቶችም ተለይተዋል፡፡ መንግስት ካስቀመጠውና ለመጨበጥ እየተንደረደረ ካለው ራዕይ አንጻር በታለመው የእድገት የዕድገት ጉዞ ባሉ አገሮች የሚገኙትን የከፍተኛ ትምህርት ልማት ካሉበት ሁኔታ አኳያ ሃገራችን የደረሰችበት ደረጃ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ዘመን የከፍተኛ ዘርፍ በዋናነት ስድስት ስትራቴጂያዊ ፕሮግራሞች ተለይተዋል፡፡ እነዚህም ዩኒቨርሲቲዎችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ የትምህርት ፍትሃዊነትን ማሳደግ፣ የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ማጎልበት፣ የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና ማህበረሰብ አገልግሎትን ማሳደግ፣ የተቋም አመራር፣ አሰራርና አደረጃጀትን ማሻሻል ናቸው፡፡፣

እነዚህን ዓላማዎች ታሳቢ በማድረግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ማለትም በ2012 ዓ.ም በየፕሮግራሞቹ እንዲፈጸሙ የሚጠበቁ ግቦች እና ለማሳካት የሚያስችሉ ማስፈጸሚያ አቅጣጫዎችም ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

### 4.1. የዩኒቨርሲቲዎች ማስፋፋት እና ማጠናከር

#### 4.1.1. የፕሮግራሙ ግቦችና ዓላማዎች

የዚህ ፕሮግራም ዋና ግብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ተሳትፎ የማስተናገድ አቅም በማስፋፋት የአገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትና ተሳትፎ ለማሳደግ ነው፡፡

በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ያለውን የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት ለማስተናገድ እንዲቻል ዩኒቨርሲቲዎች ብዛትና የተማሪዎች ተሳትፎ አቅም መጨመር በየዓመቱ በየደረጃው የሚጠበቁ የተማሪዎች ብዛት ያገናዘበ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ስኬት ፕሮግራሙ በ2ኛው የዕ.ት.ዕ ዘመን ክልላዊ ፍትሃዊነታቸውን ማዕከል በማድረግ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን የመገንባት እና ነባር የመንግስት እና የግል ዩኒቨርሲቲዎችን የማጠናከርና የማጎልበት እንዲሁም የአገራዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ የቅድመ ምረቃና የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞችና ተማሪዎች ተሳትፎና ስኬት ማሳደግን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የፕሮግራሙ ዓላማዎች፣የማስፈጸሚያ አቅጣጫዎች እና ዋና ዋና ተግባራት ከነውጤት አመላካቻቸውና ፈጻሚ አካላት በዝርዝር ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ . የፕሮግራሙ ዓላማ፣ የውጤት አመላካች፣ መነሻና ዒላማ**

| **የፕሮግራም ዓላማዎች** | **የውጤት አመልካች** | **መነሻ (2007)** | **ዒላማ (2012)** |
|---|---|---|---|
| 1. ክልላዊ ፍትሃዊነት ማዕከል ያደረገ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን መገንባትና አደረጃጀታቸውን ማሟላት | የአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር | 33 | 44(11 አዳዲስ) |
| | የአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የተማሪዎች ተሳትፎ ድርሻ | | 15% |
| 2. ነባር የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን ማጎልበትና ማጠናከር | የነባር ዩኒቨርሲቲዎች ዓመታዊ የመደበኛ ድህረምረቃ ተማሪዎች ተሳትፎ ድርሻ | | 10% |
| | የነባር ዩኒቨርሲቲዎች ዓመታዊ የተማሪዎች የተሳትፎ ድርሻ | 67.7% (316261) | 85% |
| | የነባር ዩኒቨርሲቲዎች አማካይ የተማሪዎች የተሳትፎ ዕድገት | 3.46 | 5% |
| 3.የግል ከፍተኛ ት/ተቋማትን ማጠናከር | የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች ተሳትፎ አቅም | 9.42% | 15% |
| | የግል ነባር ዩኒቨርሲቲዎች የመደበኛ ተማሪዎች የተሳትፎ አቅም ዕድገት | -- | 2% |
| | የግል ዩኒቨርሲቲዎች በድህረ ምረቃ የመደበኛ ተማሪዎች የተሳትፎ አቅም ድርሻ | | 15% |
| 4. የሀገራዊ የቅበላ/ተሳትፎ አቅም | የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ጥቅል ተሳትፎ አቅም በመቶኛ | 9.42 | 15% |
| | የመንግስት ተቋማት በመደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ጥቅል የተሳትፎ መጠን | 387,565 | 597,685 |
| | የመንግስት ተቋማት የመደበኛ የሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎች ጥቅል ተሳትፎ መጠን | 28,140 (2005) | 56,000 |
| | የመንግስት ተቋማት የመደበኛ የሶስተኛ ድግሪ ተማሪዎች ጥቅል ተሳትፎ መጠን | 3,169 (2005) | 6,500 |
| | የሶስተኛ ድግሪ ተማሪዎች ተሳትፎ ከአጠቃላይ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | 10% | 15% |

### 4.1.2. የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች ፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ፈጻሚ አካላት

**ሠንጠረዥ 9 የፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ፈጻሚ አካላት**

| የማስፈፀሚያ አቅጣጫ | ዋና ዋና ተግባራት | የውጤት አመልካች | ዒላማ | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|
| 1፡ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን መገንባት፣ ማደራጀትና ስራ ማስጀምር | **ዋና ተግባር -1፡** የአካዳሚክ ፕሮግራም ቀረጻ (ዝግጅት)ና ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት | የአካዳሚክ ፕሮግራም ፍኖተ-ካርታ ያላቸው አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ድርሻ በመቶኛ | 100 % | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር -2፡-** የተማሪዎች የተሳትፎ አቅም የረጅም ጊዜ ዕቅድ (ፕላን) | የቅበላ አቅም ፍኖተ-ካርታ ያላቸው ዩኒቨርሲቲዎች ድርሻ (በፐርሰንት) | 100 % | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር -3፡-** አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን መገንባትና በቁሳቁስ ማደራጀት | የተደራጁ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ብዛት | 11 | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር -4፡-** የአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የሰው ሀይል አደረጃጀትና አሰራር ማደራጀት | የሰው ኃይልና ተቋማዊ ልማት ዕቅዳቸው የጸደቀላቸው እና የተገበሩ ዩኒቨርሲቲዎች ድርሻ | 100 % | ዩኒቨርሲቲዎች |
| 2፡- ነባር ዩኒቨርሲቲዎች በመሰረተ-ልማትና በሰው ኃይል ማጠናከርና የቅበላ አቅማቸው ማሳደግ | **ዋና ተግባር -1፡-** የነባር ትምህርት ፕሮግራሞችን ተፈላጊነት (አግባብነት) መዳሰስና እነሱን በጥራት ለመስጠት የሚያስችል አቅም መኖሩን መፈተሽ | በየዩኒቨርሲቲው የፕሮግራም ዳሰሳ ሪፖርት (ብዛት በቁጥር) | 33 | ዩኒቨርሲቲዎች |
| | **ዋና ተግባር -2፡-** የዩኒቨርሲቲዎች የተማራዎች ተሳትፎ አቅም ለማሳደግ የመሰረተ-ልማትና የሰው ኃይል ማጠናከሪያ ፍኖተ ካርታ ዝግጅትና ትግበራ | በመሰረተ-ልማትና በሰው ኃይል የተጠናከሩ ዩኒቨርሲቲዎች ብዛት በፐርሰንት | 100 | ትምህርት ሚኒስቴር፣ ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ |
| 3፡- የግል ከፍ/ት/ተቋማትን ማጠናከር | **ዋና ተግባር -1፡-** የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የተማሪዎች ቅበላ/ተሳትፎ መጠን ለማሳደግ ተግዳሮቶችን፣ ዕድሎችን ና አቅጣጫዎችን መለየት | የዳሰሳ ሪፖርት ብዛት | 1 | ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል |
| | **ዋና ተግባር -2፡-** የግል ከፍ/ት/ተቋማት እና የመንግስት ከፍተኛ ት/ተቋማት በአጋርነት የሚሰሩበትን ማዕቀፍ ማዘጋጀት | የአጋርነት ማጎልበቻ ማዕቀፍ ሰነድ ብዛት | 1 | ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል |
| | **ዋና ተግባር -3፡-** የግል ከፍ/ት/ተቋማትን አመራር አቅም ግንባታ መደገፍ | በመንግስት ድጋፍ የሰለጠኑ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከፍተኛ አመራር ብዛት | 10 % | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ፣ ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | **ዋና ተግባር** -4፡- የግል ከፍተኛ ትምህርት መምህራን የትምህርት ደረጃ ለማሳደግ እንዲችሉ ማበረታታት | የሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ለመከታተል ካመለከቱ መምህራን እድሉን ያገኙት ድርሻ(% ) | 25 % | |
| 4፡ በተለያዩ ዘዴዎች/መንገዶች ወደ ከፍተኛ ት/ ፕሮግራም የሚሳተፉ ተማሪዎች ቁጥር ማሳደግ | **ዋና ተግባር** -1፡ ወደ ከፍተኛ ት/ ፕሮግራም መግቢያ ዘዴዎች/መንገዶች ዓይነት | በስራ ላይ ስልጠና ዘዴ የከፍተኛ ት/ ፕሮግራም መግቢያ ማስጀመር | 1 | ዩኒቨርሲቲዎች |
| | **ዋና ተግባር** -2፡ ከሁለተኛ ደረጃ (መሰናዶ ) ትምህርት ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚኖረውን የተማሪዎችን ሽግግር ለማሳደግ በዩኒቨርሲቲ ትምህርት ትስስር | ዩኒቨርሲቲው በሚገኝበት ዞን ትብብር የተደረገላቸው ሞዴል የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት በፐርሰንት | 50 | ዩኒቨርሲቲዎች |
| 5፡ አዳዲስ የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብሮችን ማዘጋጀትና | **ዋና ተግባር** 1፡- የመምህራን አቅርቦት ስልቶችን በመጨመር ጥራትን ማሻሻል | 3ኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ብዛት በፐርሰንት | 30 % | ዩኒቨርሲቲዎች |
| | **ዋና ተግባር** 2፡- ለድህረምረቃ ፕሮግራም የሚመደብ በጀት | የድህረምረቃ ምርምር በጀት መጠን ጭማሪ በፐርሰንት | 25 % | ዩኒቨርሲቲዎች |

| የማስፈፀሚያ አቅጣጫ | ዋና ዋና ተግባራት | የውጤት አመልካች | ዒላማ | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|
| | **ዋና ተግባር 3፡-** ሀገራዊና አለምአቀፋዊ አጋርነት በመፍጠር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብሮችን ማጠናከር | የትብብር ድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ብዛት | 1 | ዩኒቨርሲቲዎች |
| | **ዋና ተግባር 4፡** የድህረምረቃ ፕሮግራሞችን የማጠናቀቂያ ጊዜ ርዝመት ብሄራዊ መመሪያ ማዘጋጀት እና ተፈጻሚነቱን ክትትልና ግምገማ ማድረግ | የጸደቀ የድህረምረቃ ፕሮግራሞችን የማጠናቀቂያ ጊዜ ዕርዝመት ብሄራዊ መመሪያ | 1 | የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ |

## 4.2. የከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊነትን ማሳደግ

### 4.2.1. ግቦችና ዓላማዎች

ይህ ፕሮግራም ሁለት ዋና ዋና ግቦች አሉት፡፡ የመጀመሪያ ግብ የሴት ተማሪዎች ፣ የታዳጊ ክልሎች ተማሪዎች፣ አካል ጉዳተኞችና ሌሎች ልዩ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ለማሳደግ ያለመ ነው፡፡ ሁለተኛው ግብ ደግሞ ሴቶች በመምህርነት፣ በምርምርና በአመራር ያላቸውን ተሳትፎና ስኬታማነት ማጎልበት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በዚህ ፕሮግራም የዜጎችን የትምህርት አገልግሎት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የከፍተኛ ትምህርት ሴት ተማሪዎችን፣ ከታዳጊ ክልል የመጡትንና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን ተሳትፎና በትምህርታቸው የመዝለቅ ስኬት የተመለከቱትንና የሴት መምህራንን ከወንዶቹ አንጻር ያላቸውን ቁጥር፣ በምርምር እና ከቦርድ ጀምሮ በዩኒቨርሲቲዎች አመራር ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና ስኬት ለማሳደግ ትኩረት ያደረጉ ዓላማዎችንና ተግባራትን ይመለከታል፡፡

ሠንጠረዥ 10. የፕሮግራሙ ዓላማ፣ የውጤት አመላካች፣ መነሻና ዒላማ

| የፕሮግራም ዓላማ | የውጤት አመላካች | መነሻ(2007) | ዒላማ |
|---|---|---|---|
| 1. የከፍተኛ ት/ ሴቶች ተማሪዎችን ተሳትፎ እና ውጤታማነት መጨመር | በቅድመ-ምረቃ ፕሮግራም የሴቶች ተማሪዎች ተሳትፎ ድርሻ በመቶኛ | 32% | 45% |
| | በሁለተኛ ድግሪ ፕሮግራም የሴቶች ተማሪዎች ተሳትፎ ድርሻ በመቶኛ | 22% | 35% |
| | በሶስተኛ ድግሪ ፕሮግራም የሴቶች ተማሪዎች ተሳትፎ ድርሻ በመቶኛ | 11.5% (2007) | 20% |
| 2. ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችና ከታዳጊ ክልል የሚመጡ ተማሪዎችን ተደራሽነትና ውጤታማነት ማሳደግ | ልዩ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎች ብዛት | 1.9%* | 2000 |
| | ልዩ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎች የመመረቅ (የማጠናቀቅ) መጠን በመቶኛ | -- | 95% |
| | የሴት ተማሪዎችን የመመረቅ መጠን በመቶኛ | | 95% |
| | ከታዳጊ ክልል ከሚመጡ ተማሪዎች የሚያጠናቅቁ | --- | 95% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተማሪዎች መጠን በፐርሰንት | | |
| 3. የሴት መምህራን የማስተማር እና የምርምር ተሳትፎ እና ውጤታማነት ማሳደግ | የሴት መምህራን ድርሻ በፐርሰንት | 12% | 30% (25%) |
| | የሴት መምህራን በምርምር ያላቸው ተሳትፎ ድርሻ በፐርሰንት | 2% | 20% |
| 4. የሴቶች በዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ አመራርነት ያላቸው ተሳትፎ እና ውጤታማነት ማሻሻል | የሴቶች በዩኒቨርሲቲ ስራ አመራር ቦርድ ያላቸው ተሳትፎ ድርሻ በመቶኛ | 14% | 33% |
| | በእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራርነት የሚኖረው አነስተኛ የሴቶች ተሳትፎ መጠን | 0 | 1 |
| | በእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ መካከለኛ አመራርነት የሚኖረው አነስተኛ የሴቶች ተሳትፎ መጠን | 5% (2013/14) | 30% |

* የመሰናዶ ትምህርት ነው፤

4.2.2. የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ፈጻሚ አካላት

ሠንጠረዥ 11. የፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት፣ እና ፈጻሚ አካላት

| የማስፈጸሚያ አቅጣጫዎች | ዋና ዋና ተግባራት | የውጤት አመላካች | ዒላማ | ፈፃሚ |
|---|---|---|---|---|
| 1. ሴት ተማሪዎችን በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ደረጃዎች እንዲሳተፉ እና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ልዩ ድጋፍ ማድረግ፡፡ | **ዋና ተግባር 1፡-** በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚገኙ ሴት ተማሪዎች ልዩ የሆነ የትምህርት ድጋፍ አገልግሎት በክረምት እና በቅዳሜና እሁድ መስጠት | በልዩ የትምህርተ ድጋፍ አገልግሎት የሚሳተፉ ተቋማት በፐርሰንት (የተደገፉ ሴት ተማሪዎች ብዛት) | 100% | ዩኒቨርሲቲዎች |
| | **ዋና ተግባር 2፡-** የትምህርት ቤቶችን መምህራንና ፤የአመራር አቅምን ማጠናከር | ከትምህርት ቤቶች ጋር ተቋማ ግንኙነት የፈጠሩ ዩኒቨርሲቲዎች ብዛት በፐርሰንት (የተጠናከሩ መምህራንና አመራር አባላት ብዛት) | 100% | ዩኒቨርሲቲዎች |
| | **ዋና ተግባር 3፡-** የልዩ ቅበላ ፖሊሲውን በመደበኛ ሁኔታ መከለስ | በየዓመቱ የተሻሻሉ ጥቅም ላይ የዋሉ መመሪያዎች ብዛት | 1 | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር 4፡-** በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ሴት ተማሪዎች ተቋማዊ እና ቀጣይ የሆነ ልዩ የትምህርት፤የኢኮኖሚ እና የስነ-ልቦና ድጋፍ ማድረግ | የድጋፍ አገልግሎት መስጫ መመሪያ ሰነድ ያላቸው ተቋማት በፐርሰንት | 100% | ዩኒቨርሲቲዎች |
| | **ዋና ተግባር 5፡-** በሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች ለሴቶች የተለየ ነፃ የትምህርት እድል ስርዓት ማዘጋጀት | የሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ ነፃ የትምህርት እድል የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች (በሰነድ በተደገፈ መረጃ የተረጋገጠ በፐርሰንት) | 100% | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ፣ ዩኒቨርሲቲዎች |
| 2፡- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው እና ከታዳጊ ክልሎች ለመጡ ተማሪዎች በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ደረጃዎች ላይ ብቁ እና | **ዋና ተግባር 1.** ልዩ ድጋፍ ለሚስፈልጋቸው ተማሪዎች የቅበላ ፖሊሲውን በመደበኛ ሁኔታ መከለስ | በየዓመቱ የተሻሻሉ ና ጥቅም ላይ የዋሉ መመሪያዎች ብዛት | 1 | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር 2፡-** የተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎችን በልዩ ፍላጎት ትምህርት የብቃት ማእከል እንዲሆኑ ድጋፍ ማድረግ | የተቋቋሙ እና ስራ የጀመሩ ማዕከላት ብዛት | 3 | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር 3፡-** ለአካላዊ ጉዳት ለተዳረጉና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች የሚሆን ግንባታና መሰረተልማት ማጠናከር | የፀደቀ እና የተተገበረ ፖሊሲ | 1 | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ልዩ ድጋፍ ማድረግ፡፡ | **ዋና ተግባር 4:- ልዩ ድጋፍ ለሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ተቋማዊ እና ቀጣይነት ያለው ልዩ በትምህርት፤በኢኮኖሚ እና በስነ-ልቦና ድጋፍ ማድረግ** | የልዩ ድጋፍ ስርዓት የዘረጉ ተቋማት በፐርሰነት | 100% | ዩኒቨርሲቲዎች |
| **3፡-የሴቶችን የማስተማር ና የምርምር ተሳትፎ እና ብቃት ማሻሻል** | **ዋና ተግባር 1፡- የሴት መምህራን የምልመላ እና የአቅም ግንባታ ፖሊሲ ማዘጋጀት እና መተግበር** | የፀደቀ እና የተተገበረ ፖሊሲ | 1 | ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር 2፡- የሴት መምህራንን የምርምር ተሳትፎ እና ውጤታማነት የሚሳድግ ልዩ የአቅም ግንባታ ስርዓት ማዘጋጀት እና መተግበር** | ልዩ የአቅም ግንባታ ስርዓት ያላቸው ተቋማት ብዛት በፐርሰንት | 100% | ዩኒቨርሲቲዎች |
| **4፡- በሁሉም ደረጃዎች የሴቶችን የአመራርና የአስተዳደር ተሳትፎና ብቃት ማሳደግ** | **ዋና ተግባር 1፡- ዩኒቨርሲቲዎች ቦርድ እና ከፍተኛ አመራር ስብጥር ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ከፍ የሚደርግ ሃገራዊ መመሪያ ማዘጋጀት እና መተግበር** | የፀደቀ የቦርድ እና የከፍተኛ አመራር ስብጥር ማደራጃ መመሪያ | 1 | በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ |
| | **ዋና ተግባር 2፡- ሴቶች በአመራርና በአስተዳደር የሚደርጉትን ተሳትፎና ውጤታማነት የሚያዳብር ልዩ ፕሮግራም መቅረፅና መተግበር** | የሴቶችን የአመራር አቅም የሚገነባ ልዩ ፕሮግራም የተገበሩ ተቋማት በመቶኛ | 100% | ዩኒቨርሲቲዎች |

### 4.3. የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ማሳደግ

#### 4.3.1. ግቦችና ዓላማዎች

